
ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን
፲፩ኛ እትም
አዘጋጅ
ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሊቃውንት ጉባኤ ፀባል
ሚያዚያ ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
አዲስ አበባ


ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን
የመጽሐፉ አዘጋጅ ቅኔ ተምሮ በመምህርነት
የተመረቀባት አዲስ አበባ የታዕካ ነገሥት በአታ
ለማርያም ቤተ ክርስቲያን።
አዘጋጅ
ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሊቃውንት ጉባኤ ፀባል
በርታ ማተሚያ ቤት

ያለ መጽሐፉ አዘጋጅ ፈቃድ በሙሉም ሆነ በከፊል
ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው ::

ማውጫ

ተ.ቁ. አርእስት ገጽ

፩. መግቢያ....................................1

፪. መቅድም....................................4

፫. ክፍል ፩ ....................................9

፬. የቤተ ክርስቲያን አተካከልና አሠራር....................9

፭. የቤተ ክርስቲያን ሥራ ፈቃድ ....................9

፮. የቤተ ክርስቲያን ዐቅድ(ፕላን) ....................10

፯. ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን ....................16

፰. የጽላት አቀራረፅ....................16

፱. ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን (የቤተ
ክርስቲያን መብራት)....................17

፲. ሥርዓተ መቅደስ ወዓውደ ምሕረት ....................18

፲፩. ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሔድ
የሚደረግ ጥንቃቄ ....................19

፲፪. ቤተ ክርስቲያን የመሳለም ሥርዓት ....................20

፲፫. ክፍል ፪ ....................22

፲፬. ሥርዓተ ጥምቀት....................22

ተ.ቁ. አርእስት ገጽ

፲፭. የጥምቀት አመሠራረት ....................22

፲፮. ከመጠመቅ በፊት የሚያስፈልጉ ነገሮች ....................23

፲፯. ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ....................24

፲፰. የጥምቀት ሥርዐት ....................25

፲፱. የጥምቀት አፈጻጸም ....................29

፳. በጥምቀት የሚገኝ ክብር ....................31

፳፩. የሥርዐተ ጥምቀት ትርጉም....................32

፪፪. ክፍል ፫ ....................34

፳፫. ሥርዐተ ሜሮን ....................34

፳፬. የሜሮን አመሠራረት ....................34

፳፭. የሜሮን አቀባብ ሥርዐት ....................35

፳፮. በሜሮን የሚገኝ ጸጋ ....................37

፳፯. የሥርዐተ ሜሮን ትርጉም ....................37

፳፰. ክፍል ፬ ....................37

፳፱. ሥርዐተ ቍርባን ....................37

፴. የመሥዋዕትና የቍርባን አመሠራረት....................37

፴፩. መሥዋዕተ ኦሪት....................38

ተ.ቁ. አርእስት ገጽ

፴፪. መሥዋዕተ ወንጌል ....................39

፴፫. ለቁርባን የሚደረግ ጥንቃቄ ....................41

፴፬. ለመሥዋዕት የሚገባ ስንዴ ....................42

፴፭. ለመሥዋዕት የሚገባ ወይን ....................42

፴፮. በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ ካህናትና
ምእመናን የሚቆሙበት ቦታ ....................43

፴፯. መቀደሻ አልባሳት ....................43

፴፰. ሥርዐተ ቅዳሴ ....................44

፴፱. ለመቍረብ የሚያበቃና የማያበቃ ሁኔታ....................50

፵. የቍርባን ሥርዐት ....................51

፵፩. ከቍርባን በኃላ የሚደረግ ጥንቃቄ ....................52

፵፪. የሥርዐተ ቅዳሴ አፈጻጸም ....................52

፵፫. የሥርዐተ ቍርባን ትርጉም ....................53

፵፬. ክፍል ፭ ....................62

፵፭. ሥርዐተ ንስሐ ....................62

፵፮. የንስሐ አመሠራረት....................62

፵፯. የንስሐ የኑዛዜ ሥርዐት ....................64

ተ.ቁ. ርእስት ገጽ


፵፰. የንስሐና ኑዛዜ የሚገኝ ጸጋ ........................65
፵፱. የንስሐና ኑዛዜ አፈጻጸም ........................65
፶. ክፍል ፮ ........................66
፶፩. ሥርዓተ ክህነት ........................66
፶፪. የክህነት አመሠራረት ........................66
፶፫. የክህነት ሥልጣን ........................68
፶፬. የክህነት ተግባር ........................68
፶፭. ሢመተ ክህነት ........................69
፶፮. የፖትርያርክ ወይም የሊቀ ጳጳሳት
አሹዋሹዋም ሥርዓት ........................69
፶፯. የኤጲስ ቆጳሳት ሢመተ ክህነት ሥርዓት ........71
፶፰. ጉባኤ ኤጲስ ቆጳሳት(ሲኖዶስ) ........................81
፶፱. የሢመተ ቀሳውስት ሥርዓት ........................82
፷. ለቅስና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች................82
፷፩. ሢመተ ቅስና ........................84
፷፪. የቀሳውስት ተግባርና ሥልጣን ........................84
፷፫. ትእዛዘ ቀሳውስት ........................85
፷፬. ቀሳውስት ከሹመት የሚሻሩበት ሥርዓት ........86


ተ.ቁ. ርእስት ገጽ


፷፭. የሢመተ ዲያቆናት ሥርዐት ............88
፷፮. ለዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች ............88
፷፯. ሢመተ ዲቁና ........................89
፷፰. የዲያቆናት ሕይወትና ሥርዐት ........................90
፷፱. ዲያቆን ከማዕርጉ የሚሻርበት ምክንያት ........92
፸. የንፍቀ ዲያቆን ሢመት ሥርዐት ........................93
፸፩.ለንፍቀ ዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች......93
፸፪. ሥርዐተ ሢመተ ንፍቀ ዲያቆናት..................94
፸፫. የንፍቀ ዲያቆናት ሥራ ........................94
፸፬. ንፍቀ ዲያቆን የሚሻርበት ምክንያት ............95
፸፭. ለአናጎንስጢስ ሢመት የሚያበቃ ሁኔታ..........95
፸፮. ሥርዐተ ሢመተ አናጕንስጢስ ........................95
፸፯. የአናጕንስጢስ ሥራ ........................96
፸፰. አናጕንስጢስ የሚሻርበት ምክንያት ............96
፸፱. ሥርዐተ አናጕስጢስ ........................97
፹. የመዘምራን ሢመት ሥርዐት ........................97
፹፩. ሥርዐተ ሢመተ መዘምራን ........................97


ተ.ቁ. ርእስት ገጽ


፹፪. የመዘምራን ሥራ ........................97
፹፫. ሥርዐተ መዘምራን ........................97
፹፬. የዐጸውተ ኆዋኅው ሢመት ሥርዐት ............98
፹፭. የዐጸውተ ኆዋኅው ሥራ ........................98
፹፮. ሥርዐተ ዐጸውተ ኆዋኅው ........................98
፹፯. የዲያቆናውያት ሢመት ሥርዐት ............98
፹፰. ሥርዐተ ሢመተ ዲያቆናውያት ............99
፹፱. የዲያቆናውያት ሥራ ........................99
፺. የክህነት ዓላማና ጥቅም ........................100
፺፩. የሥርዐተ ክህነት ትርጉም ........................101
፺፪. ክፍል ፯ ........................106
፺፫. ሥርዐተ ጋብቻ ........................106
፺፬. የጋብቻ አመሠራረት ........................106
፺፭. የጋብቻ ተፈላጊነት ........................111
፺፮. ማጨት ........................112
፺፯. ሥጋዊ ዝምድና ........................113
፺፰. የጋብቻ ዝምድና ........................114
፺፱. መንፈሳዊ ዝምድና ........................114


ተ.ቁ. ርእስት ገጽ


፻. ቃል ኪዳን /ቀለበት ማሠር/ ........................115
፻፩. ሥርዐተ ተክሊል ........................117
፻፪. ምሥጢረ ተክሊል ........................118
፻፫. በምሥጢረ ተክሊል የሚገኝ ክብርና ጸጋ ......119
፻፬. ከጋብቻ በኋላ የባልና ሚስት አኑዋኑዋር ......120
፻፭. ፍቺ እንዳልተፈቀደ ........................124
፻፮. ፍቺና ሁለተኛ ጋብቻ........................127
፻፯. ሦስተኛ ጋብቻ ........................129
፻፰. የሥርዐተ ተክሊል አፈጻጸም ........................130
፻፱. የሥርዐተ ተክሊል ትርጉም ........................131
፻፲. ክፍል ፰ ........................137
፻፲፩. ሥርዐተ ቀንዲል /ቅብዐ ዘይት/ ................137
፻፲፪. የቀንዲል አመሠራረት ........................137
፻፲፫. ምሥጢረ ቀንዲል ........................138
፻፲፬. የቀንዲል ዓላማና ጥቅም ........................139
፻፲፭. ሥርዐተ ቀንዲል ........................139
፻፲፮. ጥቅሶችና ትርጉማቸው ........................141

# መግቢያ

መጽሐፍ የሚዳሰሰው ለአንባቢ አንድ ዓይነት ጥቅማና ዓላማ ያለው ትምህርት እንዲሰጥ መሆኑ ግልጽ ነው።

የቀድሞዎቹም ሆነ የዛሬዎቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ልጆች ፡-

፩. ስለ እምነት (ሃይማኖት)
፪. ስለ ምግባረ ሠናይና ትሩፋት
፫. ስለ ሕግጋትና ትእዛዛት
፬. ስለ ባህልና ሥርዐት
፭. ስለ ምእዳንና ትምህርት
፮. ስለ ቅዱሳን ቃል ኪዳን መቀበልና ስለ እግዚአብሔር ምሕረት
፯. ስለ መዝሙርና ማሕሌት
፰. ስለ ሞትና ሕይወት
፱. ስለ ሠይጣን ፈተናና ስለ ቅዱሳን ትዕግሥት
፲. ስለ ንስሐና ሥርየተ ኃጢአት ከብሉያትና ከሐዲሳት ከመጻሕፍተ ሊቃውንትና መጻሕፍተ መነኮሳት ከሌሎችም ልዩ ልዩ የታሪክና የድርሳናት መጻሕፍት በመጥቀስና በመቀመም እያዘጋጁ በማስረጃ እያጠናከሩ አያሌ መጻሕፍትን በመጻፍና በመተርጎም ቤተ ክርስቲያናችንን ቤተ መጻሕፍት፣ ሀገራችንን ሀገረ መጽሐፍ አድርገዋቸው ኑረዋል።

እነዚህም መጻሕፍት ለሃይማኖት ማጥኒያ፣ ለስነ ምግባር መማሪያ፣ ለአእምሮ ማዳበሪያ፣ ለትምህርት ማስፋፊያ ሁነው ኑረዋል፤ ይኖራሉ።



የዚህ መጽሐፍም ዓላማ ጥልቅና ምጡቅ የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐት ለመማርና ለማስተማር ለማወቅ ና ሥርዓቱን ለመፈጸም ለሚችሉ ሁሉ የሚረዳ ነው።

ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁንም በሲኖዶስ በፍትሐ ነገሥት በሌሎችም የሥርዓት መጻሕፍት በሰፊው ተጽፎዋል። ይሁን እንጂ ካህናትና ምእመናን በቅርብ አንብበው የሚረዱት በአስተዋጽኦ የተዘጋጁና የታተመ መጽሐፍ ስለሌለ አንባብያን ሁሉ ያለ ችግር በቀላሉ የሚያገኙትና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናቸውን የሚያጠኑበት መጽሐፍ እንዲኖራቸው በማሰብ ነው።

አንባቢው ምሥጢሩንና ጥቅሙን፣ ሥርዓቱንና አፈጻጸሙን ከነማስረጃው ማግኘትና መረዳት እንዲችል ትምህርቱ ከነጥቅሱ በተራ ቀርቡዋል።

መጽሐፍ የሚያስተምረው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ምሥጢር በቅድሚያ አመሠራረቱን፣ መነሻውን፣ ከዚያም አመጣጡንና ታሪኩን፣ አሠራሩና አፈጻጸሙን እንዲሁም የሥርዓቱን ትርጉም ይገልጣል።

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1984 ዓ.ም. ታትሞ ነበር ። ነገር ግን የመጀመሪያው እትም መጽሐፍ ለካህናትና ለምእመናን ሳይዳረስ ስለ አለቀ አሁን ለሁለተኛ ጊዜ ተጨምሮበት፣ ተስፋፍቶና ትርጉሙ ተገልጾ ታተመ ።



የቤተ ክርስቲያን ሥርዐተ ባሕር ስለሆነ፣ ሁሉን ቀድቶ በጽሑፍ ላይ ለማዋል ጥራዝ ማብዛትና አንባቢን ማሰልቸት መስሎ ስለታየኝ ለጊዜው አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ እንዲገለጡ ማድረጌን በመጀመሪያው መጽሐፍ ገልጬያለሁ ፤ በሁለተኛው መጽሐፍ ከአንደኛው መጽሐፍ የቀረውን ሥርዓት እንደማቀርብም አሳውቄ ነበር። ይሁንና በዚህ በሁለተኛው መጽሐፍ የቀረውን ሥርዓት ከማቅረብ ይልቅ ያንኑ በአንደኛው መጽሐፍ የወጣውን የጎደለውን ሞልቶ፣ የጠመመውን አቃንቶ ትርጉም ሰጥቶ ማዘጋጀት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ስለሆነ በዚሁ መሠረት ቀሪውን ሥርዓተ ለ፫ኛው መጽሐፍ አቆይቶ ያንኑ በማስፋፋትና አንድ አንድ የቀሩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓታትን በማከል ትርጉም ተሰጥቶት ተዘጋጅቷል።

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ

# ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

## መቅድም

ሥርዐት ማለት "ሠርዐ ሠራ" ከሚለው የግዕዝግሥ የወጣ የምዕላድነት ዘር ያለው ስም ነው። ትርጉሙ ሕግ ፥ደንብ ፥ አሠራር ፥ መርሐ ግብር ማለት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ማለትም ሁለት ትርጉም ያለው በዘርፍና በባለቤትነት የተቀመጠ ስም ነው ። እንደኛው ትርጉም የክርስቲያን ቤት፤ የክርስቲያን መሰብሰቢያ ፤ የክርስቲያን መገናኛ ማለት ነው ። ይህም ማለት ክርስቲያኖች በአንድነት በመሰብሰብ የሚጸልዩበት ፥ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት ፥ የሚሰግዱበት ፥ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቦታና የጸሎት ቤት ማለት ነው /ኢሳ. 56፡7 ፤ኤር. 7፡10-11፤ ማቴ. 21፡13 ፤ ማር. 11፡17 ፤ሉቃ. 19፡46/።

ሁለተኛው ትርጉም የክርስቲያን ወገን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሚጠራበት ስም ነው ። ቤተ እሥራኤል ፥ "ቤተ ያዕቆብ ፥ ቤተ አሮን" ሲል የእሥራኤል ወገን ፥የያዕቆብ ወገን ፥ የአሮን ወገን ማለት እንደሆነ ቤተ ክርስቲያን ማለትም የክርስቲያን ወገን ማለት ነውና /መዝ.117፡3፤ 113፡1፤ ማቴ. 16፡18 ፤ 18፡7፤ የሐ.ሥ. 18፡22 ፤ 20፡28/።

በአጠቃላይ አነጋገር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወይ ም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሲባል ግን



የቤተ ክርስቲያን ሕግ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና የቤተ ክርስቲያን የአሠራር መርሐ ግብር ማለት ነው ።

የሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጥልቅና ምጡቅ የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በመጠኑም ቢሆን ፥ ለመማርና ለማስተማር ለማወቅና ሥርዓቱን ለመፈጸም ለሚችሉ ሁሉ የሚረዳ ነው።

## የሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ምንጮች

1. መጻሕፍተ ብሉያት
2. መጻሕፍተ ሐዲሳት
3. የሐዋርያት ሲኖዶስ
4. ሥርዐተ ጽዮን
5. አብጥሊስ
6. ትእዛዝ
7. ዲድስቅልያ
8. ፍትሕ መንፈሳዊ
9. የ3 ጉባኤያት (የኒቅያ ፥ የቁስጥንጥንያ ፥ የኤፌሶን ውሳኔዎች)
10. ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን
11. ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን በየጊዜው የተነሡት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የጻፏቸው ልዩ ልዩ የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው

ለሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ ሥርዓተ ደብተራ ኦሪት ፤ ሥርዓተ መቅደስ ኦሪት፥ ሥርዓተ ክህነት ኦሪትና የመሳሰለው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት መሆኑ ግልጽ ነው። የደብተራ ኦሪት ፥ የመቅደስ ኦሪት አሠራር ምሳሌነት ለ- አሠራር ለቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አሠራር ምሳሌነት አ ለው።ደብተራ ኦሪት፤መቅደሰ ኦሪት በ3 ክፍል ይሠራ እንደነበር ሁሉ ቤተ



ክርስቲያንም ቅኔ ማሕሌት ፥ ቅድስት ፥ መቅደስ በሚል በ3 ክፍል ትሠራለች / ዘፀ.36 ፡ 1 ነገ. 6፥1-ፍ/ ።

በደብተራ ኦሪት ፥በመቅደስ ኦሪ በግብር አምላካዊ አሥሩ ትእዛዛት የተጻፉበት ጽላት ኪዳን፥ ታቦተ ሕግ ይቀመጥበት እንደነበረ ሁሉ በቤተ ክርስቲያንም ይኸው ሕጉ የተጻፈበት ጽላት፥ ታቦት መሥዋዕት ይኖራል ። መሥዋዕት ይቀርብበታል ።

በብሉይ ኪዳን ይሠዋ የነበረው መሥዋዕት ቢያልፍም፥ የመሥዋዕት አቀራረቡ ቢለወጥም በብሉይ ኪዳን በልዩ ልዩ አቀራረቡ ሥርዓት መሥዋዕት ይሠዋ እንደነበር ይታወቃል ። ዛሬም በቤተ ክርስቲያን አማናዊ ው መሥዋዕት ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ይሠዋል።

በደብተራ ኦሪት የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዓተ እንደነበረ ሁሉ ዛሬ ም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ሕማሙን ፥ ሞቱን ፥ ትንሣኤውን ፥ ዕርገቱን የተከተለ የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዓት አለ ይህም "ሥርዓተ ቅዳሴ ፥ ሥርዓተ ቁርባን" እየተባለ ይጠራል።

በሐዲስ ኪዳን ያለው ሥርዓተ ቁርባን እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ከነማስረጃው በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንማራለን።

በኦሪት አይሁድ አሕዛብን በማጥመቅ የሕገ ኦሪት አማኞች የሚያደርጉበት ጥምቀተ አይሁድ እንደነበረ ይታወቃል /ማቴ.23፡15/።



በሐዲስም "ለተቀበሉት፥ በስሙ ለሚያምኑት የእግዚ አብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጣቸው" /ዮሐ. 1፡12/ በተባለው መሠረት የሰው ልጆች በመጠመቅ የእግ ዚአብሔርን ልጅነት የሚያገኙበት የልጅነት ጥምቀት የሚፈጸምበት ሥርዐት አለ።ይህም "ሥርዐተ ጥምቀት" ይባላል። ሥርዐተ ጥምቀት እንዴት እንደሚፈጸም እንማራለን። ለዚህም የሥርዐት ትምህርት መነሻ የሚሆኑን ብሉያትና ሐዲሳት ፥ ቀኖና ቤተክርስቲያንና ሲኖዶስ ቢሆኑም በበለጠ መጽሐፈ ክርስትና የተባለው የሥርዐተ ጸሎቱ መፈጸሚያ መጽሐፍ ይረዳል።

በብሉይ ኪዳን ካህናት ሲሾሙ ፥ ነገሥታት ሲነግሡ ፥ አዳዲስ ንዋያተ ቅድሳት ወደ ቤተ መቅደስ ሲገቡ የሚቀቡት ቅብዕ ቅዱስ ነበር ።

በሐዲስ ኪዳንም አዲስ አማኒ ሲጠመቅ ፥ አዲስ ጽላት ሲቀረጽ ፥ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ሲባረክ ፤አዲስ ንዋየ ቅድሳት ሲገባ ፥ ካህናት ሲሾሙ ፥ ለመጣቶች ሥርዓተ ተክሊል ሲፈጸም የሚቀቡት ቅብዕ ቅዱስ እንደአለ ግልጽ ነው። ይህም ቅብዕ ሜሮን ይባላል። ቅብዐ ሜሮን የሚፈጸምበት ወይም የሚቀባበት ሥርዓት አለ ። ይህም ሥርዓተ ሜሮን ይባላል ። ሥርዓተ ሜሮን እንዴት እንደሚፈጸም አቀባቡ እንዴት እንደሆነ ሥርዓቱን እናጠናለን ።

ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ የተነሡ በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት የነበሩ የእግዚአብሔር ወገኖች ሁሉ እግዚአብ ሔርን ሲበድሉ ፥ ከእግዚአብሔር ሲጣሉና መዓት ሲታዘዝባቸው ከእግዚአብሔር የሚታረቁበት ፥ ከመቅሰፍቱና ከመዓቱ የሚያመልጡበት ምሥጢረ ንስሐ እንደነበረ ይታወቃል።

በሐዲስ ኪዳን "በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል" ተብሎ ከጌታ ለካህናት በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተለዩትን ምእመናን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቁበት ሥርዐተ ንስሐ አሁንም ይሠራበታል።

የንስሐው አገባብና የቀኖናው አሰጣጥ እንዴት እንደ ሆነ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንማራለን።

ንስሐ የሚገባው እግዚአብሔርን ይቅርታ በመጠየቅ ሲሆን ለካህኑ በመንገርና ከካህኑ ቀኖና በመቀበል ነው። የቀኖናው አሰጣጥ "አንቀጸ ንስሐ" በሚለው መጽሐፍ ተገልጦአል ።

ክህነትም ከአዳም እስከ ክርስቶስ በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት ከእግዚአብሔር ሲሰጥ የኖረ የአገልግሎት ሥልጣን ሲሆን የክህነቱ አሹዋሹዋም ሥርዓት ነበረው ። በኦሪት ክህነት የሚሰጥ ለሌዊ ወገን ብቻ ነበር። በወንጌል ግን የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ጥሪ ላለው ሁሉ ተምሮና በቅቶ ከተገኘ ይሰጣል ።

ክህነት በሐዲስ ኪዳን እንዴት እንደሚሰጥ ሥርዓት አለው ፤ ሥርዓቱም በሲኖዶስ ፥ በፍትሐ መንፈሳዊ ፥ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በሰፊው ተገልጦዋል። የሚመተ ክህነት ሥርዓተ ጸሎት የሚፈጸምበትም መጽሐፍ "መጽሐፈ ሢመት" ይባላል።

ሌላው ሥርዓተ ተክሊል ወይም ጋብቻ ነው።ጋብቻም ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት በሕግም ያለ ሕግም በተለያየ መልኩ ሲፈጸም እስከ ክርስቶስ ደርሱዋል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለአዳምና ለሔርዋን የታዘዘው ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ብቻ የተወሰነ ስለነበረ ይህንኑ በማጽናት "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ" በማለት በአዘዘው መሠረት አንድ ድንግል ወንድና አንዲት ድንግል ሴት በመንፈስ ቅዱስ የሚዋሐዱበት የጋብቻ ሥርዓት ተመሥርቶዋል ። ይህም ሥርዓት "ሥርዓተ ተክሊል ይባላል ።ሥርዓተ ተክሊል በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተሠራ ሲሆን ሥርዓተ ጸሎቱ የሚፈጸምበት መጽሐፍ መጽሐፈ ተክሊል" ይ ባላል።

የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሚያ ከሆኑ ሥርዓታት አንዱ ሥርዓተ ቀንዲል መሆኑ ይታወቃል። ይህም ለበሽተኞች የሚቀባ ቅ ብዐ ዘይት ነው ። ሐዋርያት ይሠሩበት የነበረ ሥርዓት እንደሆነ በቦታው ታትቶዋል። የዚህንም ሥርዓት አፈጻጸም በቀኖነቀ ቤተ ክርስቲያን እንደተወሰነውና ሲሠራበት እወንደቆየው እንመለከተዋለን ።

## ክፍል 1

## ሀ/ የቤተ ክርስቲያን አተካከልና አሠራር

### 1/ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ፈቃድ

ቤተ ክርስቲያን ለመትከል ሲፈለግ የክፍሉን ኤጲስ ቆጶስ ማስፈቀድ ያስፈልጋል ። ያለ ኤጲስ ቆጶስ ፈቃድ ቤተ ክርስቲያን አይተከልም ። አይሠራም /ፍት.መን.አን.1 ቁጥር 3/ ።



### 2/ የቤተ ክርስቲያን ዕቅድ /ፕላን/

ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ 3 ክፍል ማለት መቅደስ፥ ቅድስት፥ ቅኔ ማሕሌት ሆኖ ነው ፤ የቤተ ክርስቲያን /ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን / አሠራር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ 3 ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አሠራር አለ።

ከእነዚህም አንዱ እንደ ብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስ /ምኩራብ /ቅርጽ ስቀላ ወይም ሞላላ ቅርጽ ነው።የዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ቅርፅ የተወረሰው ከሰሎሞን ቤተ መቅደስና ኋላም በዘመነ ክርስትና ታላቁ ቈስጠንጢኖስና እናቱ ዕሌኒ በኢየሩሳሌምና በቤተ ልሔም ከአሠሩዋቸው አብያተ ክርስቲያናት የተቀዳ ነው።

ለምሳሌ ያህል የደብረ ዳሞ የአክሱምና ደብረ ሮሐ የሚገኙ የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛዎቹ ስቀላ ናቸው ።ይህ የሰቀላ ቅርዕ ቤተ ክርስቲያን በመጋረጃ ወይም በአዕማድ እንጂ በግንብ የተከፋፈለ አይደለም ። የንዑስ ክርስቲያን ፥ የፍጹማን አማንያንና ዋናው መንበር ያለበት ቦታ የተለየ ነው። የሰቀላ ቤተ ክርስቲያን ጉልላቱ አንድ ብቻ አይደለም። እንደ ትልቅነቱ ነው ።

ለምሳሌ ዓፄ ዮሐንስ አራተኛ ያሠሩት የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን ሰቀላ ሆኖ 18 ጉላልት ነበረው ይባላል ።የሰቀላ ቤተ ክርስቲያን በሩ የተወሰነ አይደለም ።ሦስትም አራትም ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛው ቅርፅ ዙሪያው ክብ ነው ። ቤተ ንጉሥ ቅርፅ ይባላል ። በግድግዳ ከ3 ይከፈላል ። የመጀመሪያው ዙሪያ /ክፍል/ ቅኔ ማሕሌት ይባላል ።

ስያሜው ከግብሩ የጠወረሰ ነው መዘምራን /ደባትር/ ስብሐተ እግዚአብሐየር ማሕሌተ እግዚአብሔር የሚዘምሩበት ነውና ። በዚሁ ክፍል በመስዕ በኩል ቀሳውስትና ዲያቆናት በመንፈቀ ሌሊት ፥ ሰዓታት ይቆሙበታል ፥በነግህ ኪዳን ያደርሱበታል።

በጥንት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸመው በዚሁ ክፍል ነበር።

ለጥምቀተ ክርስትናና ለቁርባን ያልበቁ በትምህርት ፥ በንስሐ ገና የሚፈተኑ ሐዲሳን አማንያንም /ንዑስ ክርስቲያን/ ዲያቆኑ ፃዑ ንዑስ ክርስቲያን እስከሚል ድረስ በዚህ ይቆያሉ ።ዲያቆኑ የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ ብሎ በደወል ሲያውጅ ወደ መካነ ቀኖናቸው ተመልሰው ይሔዳሉ ።ወንዶች ምእመናንም ቆመው የሚያስቀድሱት በዚሁ ቦታ ነው።

መዘምራን በሚዘምሩበት በቅኔ ማሕሌት ቆመው የሚያስቀድሱ ንፍቀ ዲያቆናት ፥ አናጉንስጢስ ፥ መዘምራን ናቸው/ፍት.መን.አንቀጽ 9/።

በዚሁ ክፍል በሌብ በኩል የሚገኘው ቦታ የሴቶች መቆሚያ ነው ። በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወንዶችና ሴቶች አብረው ቆመው ስለማይጸልዩ በመጋረጃ ይከፈላል ። ክፍሉ በምሥራቅ የካህናት መግቢያ ፥ በሰሜን የወንዶች መግቢያ ፥ በደቡብ የሴቶች መግቢያ 3 በር አለው ።

**ሁለተኛው ክፍል** ቅድስት ይባላል።ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው።የቤተ ክርስቲያኑ ማዕከላዊ ቦታ ነው።በዚህ ክፍል በስተ ምዕራብ በኩል ቆመው የሚያስቀድሱት ቆሞሳት

ቆሞሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት ናቸው ፤ በስተሰሜን በኩል መነኮሳትና የሚቆርቡ ወንዶች ምእመናን፤ በስተደቡብ በኩል ደናግል መነኮሳይያት ፥ የካህናት ፥ የዲያቆናት ሚስቶችና የሚቆርቡ ምእመናት ቆመው ያስቀድሱበታል ፡፡ በዚሁ ክፍል ቆመው ሳስቀደሱ ምእመናን ሥርዓተ ቁርባን ይፈጸማል ፡፡ ከሥርዓተ ጥምቀት ፥ ከሥርዓተ ቁርባንና ከሥርዓተ ንስሐ በስተቀር የሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ በምሥራቅ ፥ በምዕራብ ፥ በስሜንና በደቡብ አራት በሮች አሉት ፡፡

ሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል መቅደስ ነው፡፡ እንደ ብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን የዚህም ስያሜው ከብሉይ ኪዳን የተወረሰ ነው፡፡በዚሁ ውስጥ ምሥጢረ ቁርባን ፥ ሥርዓተ ቁርባን የሚፈጸምበት መንበረ ታቦቱ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ ፡፡ በዚህ ክፍል ክርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ያስቀድሳሉ ፡፡ወደዚህ ክፍል ለመግባት የሚችሉ ካህናትና ዲያቆናት ብቻ ናቸው፡፡መቅደሱ ሦስት በር አለው ይህም በር በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ በር መንጠላዕት /መጋረጃ አለው፡፡ የዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ባለ አንድ ጉልላት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ በጉልላቱ ላይ ምሳሌነት በአለው በተወሰነ ቁጥር የሰጎን ዕንቁላል ይሰካበታል፡፡ ቁጥሩ ሦስት ፥ አምስት ፥ ስድስት ፥ ሰባት ወይም አሥራ ሁለት መሆን አለበት ፡፡ሦስት ቢሆን የምሥረጢረ ሥላሴ ፥ አምስት ቢሆን ጌታ የተቸነከረባቸው አምስት ቅንዋት ፥ ስድስት ቢሆን የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ፥



ሰባት ቢሆን የሰባቱ ምሥጢራት ፥ አሥራ ሁለት ቢሆን የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው ፡፡ምሳሌነት ብቻ ሳይሆን ምሥጢ ርም አለው፡፡ ሰጎን ጫጩቶችዋን የምትፈለፈለው እንደ ሌሎች ወፎች በመታቀፍ አይደለም ፡፡ ተባዕቱም ሆነ እንስቲቱ ሰጎን በየተራ ዕንቁላሉን ትኩር ብለው 40 ቀን ይመለከቱታል፡፡ዕንቁላሉም ለ40 ኛው ቀን ነፍስ ዘርቶ ይፈለፈላል፡፡ ለጥቂት ፊታቸውን ቢመልሱ ግን ዕንቁላሉ ገምቶ ይቀራል፡፡ በእግዚአብሔርና በምእመናን መካከል ያለው ግንኙነትም እንደዚህ የረቀቀ ነው፡፡ምእመናን በጸሎታቸው ጊዜ ህሊናቸውን ወደ እግዚአብሔር ፊት በተመስጦ ከአቀረቡ የጸሎታቸውን ፍሬ ያገኛሉ፡፡ ወዲያ ወዲህ ከአወላወሉ ግን ከንቱ ድካም ነው ለማለት ምእመናንን በምሳሌ ለማስተማር ነው፡፡

ሦስተኛው ቅርፅ ዋሻ ነው፡፡ የዋሻ ቤተክርስቲያን በሩ አንድ ብቻ ነው፡፡ቅኔ ማህሌት ፥ ቅድስቱና መቅደሱም የሚለየው በመጋረጃ ብቻ ነው፡፡ ላሊበላ ሠራቸው ናቸው ፡፡ የዋሻ ቤተ ክርስቲያን ጉልላት የለውም የመቅደሱም በር አንድ ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ የሚሠራው አንድ ቤት ብቻ አይደለም ፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ሊሠሩ የሚገባቸው ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር አብረው አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች አሉ፡፡ በቤተ ክርስቲያኑ ምሥራቅ ዲያቆናቱ ለመሥዋዕት የሚሆነውን ኅብስትና ወይም የሚያዘጋጁበት ሁለተኛው ቤት ይሠራል፡፡ ይህም ቤት ቤተ ልሔም ይባላል፡፡ስያሜው የተወሰደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተ ልሔም ዘይሁዳ ምሳሌ ነው ፡፡ ምሥጢሩና ቁም ነገሩ ደግሞ ዲያቆናት ኅብስቱን በቤተ ልሔም አዘጋጅተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሥዋዕት መምጣቱ



በቤተልሔም የተወለደው ፥ በጎልጎታ ለመሥዋዕት የቀረበው ክርስቶስ ይህ ነው ለማለት ነው ፡፡መቅደስ የጎልጎታ ምሳሌ ነውና፡፡

ለመሥዋዕት የሚሆነው ስንዴ /መገበሪያ/ የሚሰየምበት ፥ የሚደቅቅበት ወይም የሚፈጭበት በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ የሚሠራ ሦስተኛ ቤት አለ፡፡ ይህም "የግብር ቤት" ይባላል፡፡ስንዴው መገበሪያ ተብሏልና መፍጨቱ ደግሞ መሰየም ይባላል፡፡ይህም የመሥዋዕቱ አቀራረብ ቋንቋ ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት የሚቀመጥበት አራተኛ ቤትም ይሠራል ፡፡ ይህም ዕቃ ቤት ይባላል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ መገልገያ የሆኑት አልባሳትም፥ መጻሕፍትም የሚጠበቁት በዚሁ ቤት ነው /ሕዝ.44፡19፡ ፍት.መን.12/ ፡፡

ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸምበት የማጥመቂያ ቤትም አለ፡፡ከዚህም ሌላ የሙታን በድን የሚያርፍበትና ጸሎተ ፍትሐት የሚፈጸመበት ደጀ ሰላም ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ተያይዞ ይሠራል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት 5 ቤቶች በግድ ከቤተ ክርስቲያኑ ሳይለዩ አብረው የሚሠሩ አስፈላጊ ቤቶች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያኑ ዐቅም ሊሰሩ የሚገባቸው ቤቶች አሉ ፡እነዚህም፡-

ሀ/ የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት
ለ/ የሰንበት ት/ቤቶች ክፍሎች
ሐ/ የምእመናን መማሪያ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ
መ/ የእንግዶችና የካህናት ማረፊያ ቤቶች



ሠ/ [illegible] ት/ቤትና የተግባረ እድ መማሪያ ክፍሎች
ረ/ ቤተ መጻሕፍት
ሰ/ የንዋየ ቅድሳትና ሚፍ ሰጣን ሽያጭ ክፍሎች ናቸው፡፡

አሁን ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ምሳሌዎች የሆኑትንና ትርጉም የሚሰጡትን ነገሮች እንመልከት፡፡

የቤተ ክርስቲያን 3 በሮች፡- የሥላሴ ፥ 3 ክፍሎች የ3 ሰማያት ዓለማተ መላእክት ምሳሌዎች ናቸው ፤ ዓለማተ መላእክት የሚባሉት 3 ሰማያትም ኢዮር ፥ ራማ ፥ኤረር ናቸው፡፡

ሁለተኛ የ3 መዓርጋተ ክህነት ምሳሌዎች ናቸው ፤ 3 ማዕረግ ክህነት ዲቁና ፥ ቅስና ፥ ኤጲስ ቆጶስነት ነው፡፡

ሦስተኛ የ3 ጾታ ምእመናን ምሳሌ ነው ፤ 3 ፆታ ምእመናን ካህናት ፥ ወንዶች ፥ ሴቶች ናቸው ፡፡

ቤተ ክርስቲያን ስትሠራ ብዙ አዕማድ /ወጋግራዎች/ ያሉዋት ሆና ትሠራለች ፤ በቤተ ክርስቲያን በውስጥና በአፍአ የሚቆሙት አዕማድ /ምሰሶዎች/ የሠራዊት መላእክት ምሳሌዎች ናቸው ፡፡

ቤተ ክርስቲያን ካህናት አሉዋት ፤ ካህናት የመላእክት ምሳሌዎች ናቸው ፡፡

ቤተ ክርስቲያን መስቀል አላት ፥ መስቀል ውሀ ሳያጠጡዋት የለመለመች ያበበችና ያፈራች የበትረ አሮን ምሳሌ ነው/ዘኁ. 17፡5-8 ፤ ዕብ 9፡4/ ፡፡

## 3/ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን

ኤጲስ ቆጶስ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን በሚያደርግበት ጊዜ ከርሱ ጋር ለተራድኦ 7 ቀሳውስት እንዲገኙ ታዙዋል፡፡

ኤጲስ ቆጶሱ ቤተ ክርስቲያን ፥ ታቦትን ሲባርክ የእግዚአብሔር ማኅተም የሆነውን ቅብዐ ሜሮን ይቀባዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያኑ በተባረከ ዕለት በውስጡ ይቀደስበታል ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ ሲባረክ ወንጌለ ዮሐንስ በታቦቱ ላይ ወይም በጎኑ ሆኖ ይነበባል፡፡

ኤጲስ ቆጶሱ ሳይመጣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሳይሰበሰቡ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን አይደረግም /ፍት.መን. አን.1/ ፡፡

## 4/ የጽላት አቀራረጽ

በኦሪት ታቦት የሚባለው ጽላት የሚቀመጥበት ማደርያው ነው /ዘፀ. 40፡20-21፤ 25፡20-22፤ መዝ.131፡8 ፤ 2ቆሮ. 6፡16 ፤ ዕብ. 9፡4 ፤ ራእ. 11፡19/ ፡፡

ጽላት የሚባለው እግዚአብሔር ለሙሴ አስቀድሞ አሠርቱ ቃላት ኦሪትን በእጁ ጽፎ የሰጠው ቃሉ ተጽፎ የሚገኝበት ከዕብነ በረድ የተቀረጸው ነው /ዘፀ. 4፡13፤ 5፡1-22 ፤ ዘፀ.31፡18፤24፡12፤25፤16 ፤ 10፡1-6፤34፡1 ፤29/ ፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን የነበረው ሥርዓት ነው፡፡



በሐዲስ ኪዳን ግን ጽላትም ታቦትም የሚባለው ያው አንዱ ምሥዋዕ ነው ፤ ጽላት ሲቀረጽ ጸሕል ጽዋዕ እንዲይዝ ከቦታ ወደ ቦታ ለማዛወር እንዲቻል ሆኖ ይቀረጻል /ፍት. መን .አን 1/ ፡፡

ከዚህ በኋላ በጽላቱ ላይ አልፋ ወኦ ቤጣ የውጣ የሚለው የጌታ ስም ይቀረጽበታል ፤ ከላይ ሥዕለ ሥላሴ ፥ ቀጥሎ ምስለ ፍቁር ወልዳ ፤ ዩሐንስ ፍቁረ እግዚእ እንዲሁም መቅደሱ የተሠራለት ጻድቅም ሆነ ሰማዕት ሥዕሉ ይቀረጻል ፡፡ ስሙ ይጻፋል ፡፡

ጽላተ ኪዳኑም ማኅደረ እግዚአብሔር ነው ፤ ያለ ታቦትም መሥዋዕት አይሠዋም ፡፡

## 5/ ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን /የቤተ ክርስቲያን መብራት/

በቤተ ክርስቲያን የማበራው መብራት ጡዋፍና ዘይት ነው /ፍት.መን.አንቀጽ 1/ ፡፡የዘይቱ መብራት ቀንዲል ይባላል ፤ ቀንዲል /ክንድል/የላቲን ቃል ነው፡፡ ፍችው መብራት ማለት ነው ፡፡ መብራቱም የወይራ ዘይት ነው ፡፡

በቤተ ክርስቲያን ብዙ መብራት ማብራት ታዙዋል ፡፡ በተለይ ቅዱሳት መጻሕፍት ማለት መልእክት ጳውሎስ ፥ መልእክታተ ሐዋርያት ፥ ግብረ ሐዋርያት ሲነበቡ ቤተ ክርስቲያኑ በጣም የበራ እንዲሆን ታዝዙዋል ፡፡ይልቁንም ወንጌል ሲነበብ እጅግ በጣም መብራት ማብዛት እንደሚገባ ተሠርቶአል /ፍት.መን.አንቀጽ 1/ ፡፡



## 6/ ሥርዐተ መቅደስ ወዓውደ ምሕረት

በታቦት ፊት ለመስገድ፥ ለመጸለይ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ወደ መቅደስ ገብቶ እንዲቀመጥ አልተፈቀደለትም፡፡

ካህን ካልሆነ በስተቀር ከምእመናን ወገን ማንኛውም ሰው ወደ መቅደስ ገብቶ ሥጋ ወደሙ አይቀበልም ወደ ታቦትም አይጠጋም /ፍት.ነገ.አን.1፤በደስ.19 ኢያሱ 3፡4/፡፡

ሴቶች ወደ መቅደስ እንዲገቡና በመቅደስ ውስጥ እንዲጸልዩ አልተፈቀደም /ፍት. መን. አን. 1 ዶቅ. 44/፡፡

በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢና የውጭ ዐደባበይ ገበያ ክልክል ነው/ኤር. 7፡11 ፤ ማቴ. 21፡12-13 ፤ማር. 11፡15-17፤ ሉቃ. 19፡45-46፤ ዮሐ. 2፡13-18፤ ፍት.መን. አን. 1/፡፡

በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በቅጽረ ግቢም ቢሆን ግብዣ ማድረግ ፥ መብላት፥ መጠጣት ክልክል ነው /ፍት.መን.አን. 1 ዶቅ. 28/፡፡

በቤተ ክርስቲያን የገባውንና የተቀደሰውን ንዋየ ቅድሳት እንደገና ወደ ውጭ አውጥቶ በሥጋዊ አገልግሎት ማዋል አይገባም /ፍት. መን. አን 1 ፤ ረስጣ 28/ ፡፡



ያላመኑ ያልተጠመቁ፥ ተወግዘው የተለዩ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ፥ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያንን እንዳይሳተፉ ተከልክሏል ፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ በሮችም በአጋፋሪዎች እንዲጠበቁ ታዝዙዋል /ፍት. መን. አን. 1 ድስቅ. 12/ ፡፡

## 7/ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሔድ የሚደረግ ጥንቃቄ

ለጸሎትና ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚኬድባቸው ዕለታት እንዲሁም በጾምና በሰንበት በበዓላት ቀኖችም ወንድና ሴት መገናኘት ክልክል ነው፡፡ በመኝታ የተገናኘ ወደ ቤተ ክርስቲያን ባይሔዱም በዕለቱ አይገባም፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን በዓላትንና አጽዋማትን ሊጠብቁ ይገባል /ዘፀ.19፡15 ፤ 1 ቆሮ. 7፡5-7 ፤ ኩፋ. 34፡12/ ፡፡

ርስሐተ አንፉንና ርስሐተ ከንፈሩን የማዝረብረብ ነውር ያለበት በዚሁ ነውር ላይ እያለ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገባም ፡፡ ሥጋ ወደሙም ሊቀበል አይገባውም /ፍት.ነገ.አን. 13/ ፡፡

ሴት የወር አበባዋ /መርገሙዋ/ ሲመጣ እስከ 7 ቀን ድረስ፥ ስትወልድ ወንድ ከወለደች እስከ 40 ቀን ሴት ለወለደች እስከ 80 ቀን ድረስ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ ክልክል ነው ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ገላዋን ታጥባ ትገባለች /ዘሌዋ. 12፡1-ፍ ፤ 15፡19-28 ፤ ፍት.መን.አን 6 ዘኒቅያ 29/ ፡፡

ወንድ ሕልመ ሌሊት /ዝንየት/ ከመታው በዕለቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይገባም በማግሥቱ ገላውን ታጥቦ ይገባል / ዘሌዋ 15፡2-18/ ፡፡

## 8/ ቤተ ክርስቲያን የመሳለም ሥርዐት

ጡዋትና ማታ ቤተ ክርስቲያንን ለመሳለም መትጋት ያስፈልጋል /ምሳ.8፡34/ ፡፡

ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ በር ላይ ሲደርሱ መሳለም ይገባል /መዝ.28፡2 ፤ 95፡9 ፤ ኤር. 26፡2 ፤ ሕዝ. 46፡3 ፤ ፊልጵ. 2፡9-10/ ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ጫማ አውልቆ ወገብን ታጥቆ አደግድጎ መግባት ነው፡፡ ጫማ አድርጎ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ክልክል ነው /ዘፀ. 3፡5-6 ፤የሐ.ሥ. 7፡33 ፤ ኢያ. 5፡15፤ ፍት. ምን.12/ ፡፡ አሳብን በመንፈሳዊ ነገር ወስኖ ወደ ውጪ ወደ ዓለማዊ ነገር እንዳይሔድ መግታትና መቆጣጠር ያስፈልጋል ፡፡

ከካህን ቀርቦ መስቀል መሳለምና በረከትም መቀበል ያሻል፡፤ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተስለው የሚገኙትን የሥላሴን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፤ የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን የመላእክትን የነቢያትን የሐዋርያትን የጻድቃን የሰማዕታትን የደጋጎች ቅድሳን አበውን ሥዕሎች እጅ መንሳትና የአክብሮት ስግደት መስገድ ይገባል ፡፡

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሳቅ ፥ ስለ ዓለማዊ ሥራ መነጋገር ክልክል ነው ፡፡ ከገቡ በኋላ ዝምታ ፥ ጸጥታ፥ ፍርሃት፥ የእግዚአብሔርን ምሕረት በጥብዓት ልብ መፈለግ አለ ፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የመዘምራንን ማሕሌት፥ የቅዱሳን መላእክትን ምስጋና፥ የነቢያትን ትንቢት፥



የሐዋርያትን ስብከት መስሚያና የልዑል እግዚአብሔርን ነገር መማሪያ ቦታ ስለሆነች ነው ፡፡ ከዚህም ሌላ የሥጋ ወደሙ ምሥጢር የሚፈጸምባት ናት/ዘሌ.26፡2 ፤ ዮሐ. አፈ..አን.19-32/ "እስመ ቤተ ክርስቲያን በአምሳለ ሰማይ ወመሐይምናን ይኩኑ ወስቲታ አምሳለ መላእክት ወያፅምዑ በትዕግሥት ወበአርምሞ ወይትመሐለሉ በልቦሙ ዘእንበለ ዕረፍት" /ዮሐ.አፈ..አን.48/ ፡፡"ኢይትናገር አሐዱ ለግሙራ በውስተ ቤተ ክርስቲያን እስመ ቤተ እግዚአብሔር ቤተ ጸሎት ወአኮ ቤተ ነገር ወዘተናገረ በውስቴታ ይጻዕ ወኢይቅረብ በይእቲ ዕለት (ቀኖና አቡሊዲስ አንቀጽ (7) ወሶበ ትቀውም ቅድመ ንጉስ ምድራዊ ዘኢትደፍር ከመ. ትስሐቅ ወኢ.ምንተኒ ንጉሠ ገነሥት ሰማያዊ" ትስሕቅኑ ሶበ ትቀውም ቅድመ ንጉሠ ገነሥት ሰማያዊ" /ዮሐ. አፈ. አን. 6/ ፡፡

"እመኬ ዓለማዊ ሶበ ይስሕቅ በውስተ ቅዳሴ ያውጽእዎ አፍአ ወኢይመጥውዎ እምሥጢር ቅዱስ" /ቀኖና ባስ. አን. 79/

አጭርና ያደፈ ልብስ ለብሶ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድ ክልክል ነው ፡፡ረዘም ያለና ንጽሕ ልብስ ለብሶ መሔድ ያስፈልጋል /ዘፀ. 19፡10-11/ ፡፡

በተለይ ሴቶች ራሳቸውን ተከናንበው እንዲጸልዩ ታዝዘዋል ፡፡ኢይባዕ ብእሲ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወኢይጸሊ ውስቴታ ዘእንበለ ይኩን ልብሱ ድርማንተ በከመ ይቤ ጳውሎስ ሐዋርያ ለብሔረ ቆሮንቶስ ቀዳማዊ ለእመ ኮነ ዘይጸሊ አልባሲሁ ሐፂረ ወይትከሠት እምኔሁ ጊዜ ስግዴቱ፥ ይእቲ መዕዓሉ ዘቀበጽን በእንቲአሁ ወይከውን ጌጋየ ለዘነጸረ



ወለዘተነጸረ እስመ ለዘነጸረ ይመጽእ ሁቱ ሲሑ ወበእንተዝ ይወርድ ላእሌሁ ከመ ወረደ ላዕለ ወልያ ኖን ሶበ ለሐቀ ዲበ አበሁ በከመ ይቤ መጽሐፈ ኦሪት ወዘነጸረ እስመ ኮነ ምክንያተ ለአብጽሖ ጌጋዩ ለዘነጸተ አበሳሁ /ዮሐ. አፈ. /አን. 4፡49-72 ፤ ዘፍ. 9፡21-27 ፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡5-14/ ወደ ቤተ ክርስቲያን ባዶ እጅ መሔድ አይገባም" መባዕ፥ ምጽዋት ይዞ መሔድ አለ/ዘፀ.34፡20/ ፡፡

## ክፍል 2

### ለ/ ሥርዐተ ጥምቀት

#### 1. የጥምቀት አመሠራረት

ጥምቀት ማለት አጥመቀ አጠመቀ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የሚወጣ ማጥመቅ መጠመቅ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሳቢ ዘር ነው ፡፡

ጥምቀት ሌሎችን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለመሳተፍ፥ የቤተ ክርስቲያን ዐባል ለመሆን የመጀመሪያው መግቢያ በር ነው፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በ30 ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ጥምቀትን መሠረተ፡፡

ስለ ጥምቀቱም ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢትና የተመሰለ ምሳሌ አለ /መዝ. 67፡22፤ 28፡3፤ 76፡16፤ 113፡5-7 ፤ 1ኛ. ቆሮ 10፡2 ፤ የሐ. ሥ. 1፡5/ ፡፡



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውሃው ከወጣ በኋላ አብ "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ" ብሎ የባሕርይ ልጅነቱን መስክሮለታል ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጦዋል /ማቴ. 3፡16-17/ ፡፡

በትምህርቱ መጨረሻ " በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ" በማለት ጥምቀትን አዝዞአል /ማቴ. 28፡19/ ፡፡

#### 2. ከመጠመቅ በፊት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ከጥምቀት በፊት ፡- 1ኛ/ ትምህርት
2ኛ/ እምነት ያስፈልጋል

ተጠማቂው በዕድሜ ከፍ ያለ ከሆነ የክርስትናን ትምህርት የተማረ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና መድኃኒትነት ያመነ መሆን አለበት ፡፡ ጌታችን "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ብሎዋል /ማር. 16፡16/ ፡፡

እምነት መሠረት ነው ፡፡ሌሎች ምግባራት ግን ሕንጻዎች ናቸው ፡፡ እምነቱን ለመግለጥ የማይችል ሕጻን ከሆነ ግን በወላጆቹና በክርስትና አባቱ ወይም እናትዋ ሐላፊነት ይጠመቃል ፡፡ከአደገ በኋላ በሐላፊነታቸው ይመከሩታል ፡፡ ያሥተምሩታል፡፡

ንዑስ ክርስቲያን ከመጠመቁ በፊት ሥራው ይመረመራል ፡፡ ተመርምሮ እምነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ይጠመቃል /ፍት. መን. አን. 3 ሥርዋጽ 2/፡፡

ንዑስ ክርስቲያን ከመጠመቁ በፊት ከመጽሐፈ ኪዳን እግዚአብሔር ዘብርሃናትን እየደገሙ ያጠምቁታል ። ዘይት ይቀባል /ፍት. መን. አን. 3/።

## 3/ ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ

ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ ለወንዶች 40 ቀን ለሴቶች 80 ቀን ነው ።/ኩፋ. 4:9-11 ፤ ዘሌዋ 12/ ሕጻኑ ሞት የሚያሰጋው ሆኖ ከተገኘ ግን ፥ ከ40 -ከ80 ቀንም በፊት በሞግዚት ታዝሎ ሔዶ ይጠመቃል ። /ፍት. መን. አን. 3 ሥር. 2/ ለመጠመቅ ቀኑ የደረሰውን ሰው ለነገ ብሎ ቀጠሮ መስጠትና በልዩ ልዩ ምክንያት ማሳደር አይገባም /ፍት.መን.አንቀጽ 3/ ።

ቀደሞ ብሎ በተጠቀሰው ጥቅስ ያመነ የተጠመቀ ይድናል የተባለው ዐዋቂ ሰው ከአልሆነ በቀር ከመጠመቅ በፊት እምነት መቅደም አለበት ለማለት አይደለም ።

በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት፥ የሕጻናት ጥምቀት አከራካሪ አልነበረም ። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 10:48 ላይ ቆርኔሌዎስ ከነቤተሰቡ መጠመቁ በም. 16 ቁጥር 15 ላይ ሊድያ ከነቤተሰብዋ መጠመቋዋ፥ በ1ኛ ቆሮ. 1:16 ላይ የእስጢፋኖስ ቤተሰብ የተጠመቀ መሆኑ ስለተገለጸ ሐዋርያት ያጠምቁ የነበሩት ቤተሰብን በመላ እ ንጂ ሕፃናትን አስቀርተው እንደ አልነበረ ያመለክተናል ። ይህን የመሰለ በቂ ማስረጃ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እያለ የሕፃናት ጥምቀት ሊያጠያይቀን ፥ ሊያከራክረን አይችልም ።



## 4/ የጥምቀት ሥርዓት

1/ ጥምቀት የሚደረገው በሥላሴ ስም ነው። የሥላሴ ስም ሳይጠራ የተጠመቁት ጥምቀት በባዶ ውሀ ተነክሮ እንደ መውጣት የሚቆጠር እንጂ የሚሰጠው ዋጋ ወይም ጥቅም የለውም / ማቴ.28:19/።

2/ ጥምቀት የሚፈጸመው በፈሳሽ ወይም በጥልቅ ውሀ ነው ። የሥላሴን ስም እየጠሩ "አጠምቀከ በስመ አብ አጠምቀከ በስመ ወልድ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ" እያሉ ፥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረጉ ማጥመቅ ነው ።

ጥልቅ ውሀ በማይገኝበት ጊዜ ግን ውሀ ቀድተው ወይም በእጅ እየታፈኑ ያጠምቁታል ።

"ወይኩን ጥምቀት ውስተ ማይ ውኂዝ ወለእመ ኮነ ሀየ ዐጸባ ይክዓው ማየ ዘረከቡ ቀዲሆሙ እምኅበ ምጥማቅ" /ፍት. መን. አን . 3 ረስጠብ 34/ ።

"ወለእመ ኢተረከበ ማይ ዘይውኅዝ ርእሶ ለዘይጠመቅ ይንሣዕ መጠነ ሠለስቱ ሕፍን እምነ ማይ ወይሕፅብ ርእሶ በስመ ሥላሴ" /በስ 107/ ።

3/ አጥማቂው ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ነው ።ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሊያጠምቅ አይችልም ።

"ኢያጥምቅ ዘእንበለ ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ" /ፍት. መን. አን. 3 ድስ. 21/



ሀ/ ሴቶች አያጠምቁም /ፍት. መን.አን. 3 ድስቅ 20/

ለ/ ኤጲስ ቆጶስም ሆነ ቄስ ዋጋ ተቀብሎ ማጥመቅ አይገባውም ።

"ወኢይከውኖ ለአሐዱሂ ከመ ያጥምቅ በህልያን" /ፍት. ነገ. አን. 3 ጴጥ. 4/

ሐ/ ማንናውም ተጠማቂ በሃይማኖት ከተለዩ ሰዎች ቢጠመቅ ክርስቲያን አይባልም ። እመቦ ብእሲ ዘተጠምቀ ጥምቀተ እምዐላውያን ኢኮነ ውእቱምእመነ " /ፍት. መን. 3 ረስጣ 4/ ።

## በማጥመቅ ጊዜ የሚፈጸመው ሥርዐት የሚከተለው ነው፦

ንዑስ ክርስቲያን የሚጠመቁበት የትንሣኤ ዕለት የሆነ እንደሆነ በሰሙነ ሕማማት በሱባኤው ውስጥ ሐሙስ ሰውነታቸውን ይታጠባሉ ዐርብ ይጾሙና እሑድ ይጠመቃሉ /ፍት. መን. አን. 3፤ በደስ 19/ ።

2/ ተጠማቂዎች እሑድ ሌሊት በሚጠመቁበት ቦታ ይቆማሉ ።

3/ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ የሚጠመቁትን ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙሮ እጁን ዘርግቶ ይጸልይላቸዋል ።



4/ ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ከቁራኝነት በሚለዩበት በትብሰ ትዱሱ ላይ ይጸልይበታል ።

5/ ኤጲስ ቆጶሱ ለቄሱ ቅብዐ ቅዱሱን ይሰጡና በተጠማቂዎች ግራ ያቆመዋል ።

6/ ቀጥሎ ልጅነት በሚያሰጠው መንፈስ ቅዱስን በሚያሳድረው በሜሮኑ ይጸልይበታል ።

7/ ከጸለየበት በኋላ ለሌላ ቄስ ይሰጠውና በተጠማቂዎች ቀኝ ያቆመዋል ።

8/ ተጠማቂዎች በውሀው አንጻር ሆነው ወደ ሰማይ እየ ተመለከቱ ፊታቸውን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ይመልሳሉ።

9/ ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ዲያብሎስን ትክደዋለህን እያለ እየአንዳንዳቸውን ተጠማቂዎች ሲጠይቃቸው አዎን እንክደዋለን እያሉ እያንዳንዳቸው ይክዱታል ።

10/ ከዚያ በኋላ አንዱ ቄስ የየአንዳንዱን ተጠማቂ ቀኝ እጅ ይዞ በውሀው አንጻር ፊቱን ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይመልሰዋል ።

11/ ወደ መጠመቂያው ከመግባታቸው አስቀድሞ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ እንደ አመኑ ይናገራሉ ። ማለት "በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ታምናለህን" እያለ እየአንዳንዳቸውን የይጠይቃቸዋል ። "አዎን አምናለሁ" እያሉ እየአንዳንዳቸው ይመልሳሉ ።

12/ ከዚህ በኋላ [illegible] ልጆችን ያስደርባቸዋል። ሲጠመቁ ልብ ሳቸውን አውልቀው ነው ። ሴቶችም ሲጠመቁ የጠጉራቸውን ሹሩባ፥ የአንገታቸውን የጆሮዋቸውንና የጣታቸውን የእግራቸውን ጌጥ ፈትተው ነው /ፍት. መን. አንቀጽ 3 ፤ ረስጠብ 34/ ።

ሴት በምትጠመቅበት ቀን ግዳጅ ከመጣባት እስክትነጻ ድረስ ትቆያለች ።

13/ ተጠማቂዎች መናገር የሚችሉ ከሆኑ ራሳቸው እምነታቸውን በመመስከር ጸሎተ ሃይማኖትን ያነብባሉ ።መናገር የማይቻላቸው ከሆኑ የክርስትና አባትና እናት ስለእነሱ ሃይማኖታቸውን ይመሰክራሉ ።ጸሎተ ሃይማኖትን ያነብባሉ ።

14/ ወንዶች ሴቶችን ፥ ሴቶች ወንዶችን ክርስትና አያነሡም /ፍት. መን. አን. 3 ረስጠብ 34 ዘኒቅያ 24/

15/ የተጠማቂዎች ቅደም ተከተል ተራ በመጀመሪያ የ40 የ80 ቀን ሕፃናት ይጠመቃሉ ። በኋላ ንዑስ ክርስቲያን ወንዶች ይጠመቃሉ።፤ በመጨረሻ ንዑስ ክርስቲያን ሴቶች ይጠመቃሉ /ፍት. መን. አንቀጽ 3 ረስጠብ 34/።

16/ ተጠማቂዎች ከተጠመቁ በኋላ ካህኑ ሜሮን ይቀባቸዋል ። ከዚያ በኋላ ሥጋውን ደሙን ያቀብላቸዋል ።ሥጋውን ደሙን ሳይቀበሉ ምንም አይቀምሱም ።



17/ የክርስትና አባትና እናትም አብትም አብረው ጾመው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ ።

18/ በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ከሌሎች ቀራቢዎች በፊት ሥጋ ወደሙ ይቀበላሉ ወይትመጠው ቁርባን እምቅድመ ሕዝብ /ፍት. መን. አን. 3 በስ 105/ ።

19/ የምትጠመቀዋን ንዑስ ክርስቲያን ሴት ቅብዐ ቅዱሳንና ሜሮኑን ኤጲስ ቆጶሱ ከአንገትዋ በላይ ከቀባት በኋላ ሌላውን ሰውነትዋን የምትቀባት ዲያቆናዊት ሴት ናት /ፍት. መን. አን. 3 ፤ ድስቅ. 34/ ።

## 5/ የጥምቀት አፈጻጸም

ሀ/ በውሀው ላይ መጽሐፈ ክርስትና /ጸሎተ ጥምቀት/ ይደርሳል።

ለ/ መስተብቁዕ ከበእንተ ዱያን እስከ በእንተ ሰላም ይጸለያል ።

ሐ/ ጸሎተ ጥምቀቱን ካህኑ ሲጸልይ እጁን በተጠማቂው ላይ ያኖራል /እንብሮተ እድ ያደርጋል/ ።

መ/ የሚጠመቀውን ሰው ስመ ክርስትና ይሰይማል ።

ሠ/ ጸሎተ አኰቴትና ጸሎተ ወንጌል እድርሶ በእንተ ሰላም ፥ በእንተ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ፥ በእንተ ማኅበር የተባሉትን ጸዋትው ይጸልያል። ሕዝቡ ጸሎተ ሃይማኖትን ይጸልያሉ ።



ረ/ ካህኑ እጁን በትእምርተ መስቀል አምሳል በተጠማቂው ላይ አኑሮ "ይኩን ስምከ እገሌ" እያለ ስመ ጥምቀቱን 3 ጊዜ ይጠራል ።

ሰ/ "ቡሩክ እግዚአብሔር ዘያበርህ ለኩሉ ሰብእ" እያለ በውሀው ላይ 3 ጊዜ ሜሮን ይጨምራል ። "ብሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ዓለም አምላክነ ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ መጽንኢ ወመንጽሔ ኵልነ" እያለ በመስቀል ሦስት ጊዜ ውሀውን ይባርካል ።

ቀ/ "አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በልዑል ዜማ በማዜም ውሀውን ያትባል /ይባርካል/ ።

በ/ "ስብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ አሕዛብ የሚለውን ካህኑና ሕዝቡ" በመቀባበል እንደ ሥርዐተ ቅዳሴው ይፈጽማሉ።

ተ/ ዲያቆኑ የሚጠመቀውን ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ያመጣዋል። ካህኑም "አጠምቀከ በስመ አብ፥ አጠምቀከ በስመ ወልድ፥ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ" እያለ 3 ጊዜ ያጠምቀዋል።

ኀ/ ተጠማቂው ሲጠመቅ 50ኛውን መዝሙረ ዳዊት ያነብባል ። ሕፃን ከሆነ የክርስትና አባቱ ወይም እናትዋ ያነብባሉ ።

ነ/ ካህኑ በተጠማቂው ፊት ላይ ንሣዕ መንፈስ ቅዱስ እያለ ዕፍ ይልበታል ።ቀጥሎ ቅብዐ ሜሮን ይቀባዋል። ሜሮን በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ



የሚደረግ ሥርዐት ነው ። በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ አፈጻጸሙ በመጽሐፈ ክርስትና ተገልጡዋል ። ከዚህም ሌላ ሜሮን ለቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን /ለአዲስ ቤተ ክርስቲያን ማክበሪያ/ ለንዋየ ቅድሳት ማክበሪያም ይሆናል። ካህኑ ሜሮን ሲቀባ የተጠማቂውን ሰውነት ክፍል ክፍሉን እየለየ በትእምርተ መስቀል 36 ሕዋሳቱን ይቀባዋል። ስለሜሮን ሥርዓት በቦታው እንማረዋለን ።

አ/ ጸሎተ ቡራኬና አንብሮ እድ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል ።

## 6/ በጥምቀት የሚገኝ ክብር

1/ ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልደት መወለድ /ልጅነት ማግኘት/ ።

2/ ከኃጢአት መንጻት ነው ።

ሰው በጥምቀት ከኃጢአት በመለየቱ ከእግዚአብሔር በጸጋ በመወለዱ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ይበቃል /ሕዝ. 36፡25 ፤ የሐ. ሥ. 2፡38፤ 1ቆሮ 6፡11/ ።

" ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት /ጸሎተ ሃይማኖት/

የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ልጅ የሚሰጠው በጥምቀት ከሥላሴ ሲወለድ፥ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ተነግሮዋል /ዮሐ. 3፡5፤ ኤፌ. 5፡26፤ ገላ. 3፡27 ፤ ቲቶ 3፡15 ፤ 1 ቆር 2፡11-13 ፤ 1ጴጥ. 1፡3-6/ ።

## 7/ የሥርዓተ ጥምቀት ትርጉም

ሀ/ በውሀ የምናጠምቅበት ምክንያት ራሱ ክርስቶስ በውሀ ተጠምቋዋል ። ሐዋርያትንም በውሀ እንዲያጠምቁ አዝዙዋል /ማቴ. 3፡13-16፤ ማር. 1፡9 ፤ ዮሐ 3፡5፤ ኤፌ. 5፡26፤ ቲቶ 3፡5 ፤ 1ዮሐ. 5፡6-8/ ።

ለ/ ከውሀው ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለን መጠመቃችን ክርስቶስ በከርሠ መቃብር ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው /ፍት. መን. አን. 3 ድስ. 34/ ።

ሐ/ ተጠማቂው በሚጠቅበት ጊዜ ዲያብሎስን ሲክደው ፊቱን ወደ ምዕራብ ማዞሩ የዲያብሎስ ቦታው ምዕራብ ስለሆነ ነው ።

መ/ ተጠማቂው ፊቱን ወደ ምሥራቅ የሚመልሰው አዳም በገነት ሰባት ዓመት መኖሩን ለማስታወስ ነው ። ገነት ምሥራቅ ናትና ።

ሠ/ ተጠማቂው ወደ ምዕራብ የሚመለስበት ምክንያት አዳም ሲያል መውረዱን ለማዘከር ነው ። ሲያል ምዕራብ ናትና ።

ረ/ ተጠማቂው በውሀ አንጻር መቆሙ አዳም የድኅነትን ተስፋ መስማቱን ለማዘከር ነው ። ምክንያቱም ድኅነት በጥምቀት ነውና "የማነ እዴ የመጠውክምሙ ወኮነቶሙ ጥምቀተ" /መጽሐፈ ኪዳን 2ኛ. ክፍል / ።



ሰ/ ካህኑ የተጠማቂውን እጁን ይዞ ወደ ምስራቅ ፊቱን የሚመልስበት ምክንያት ጌታ በጥምቀት ወደ ምሥራቃዊት ገነት እንደ መለሰን ለማጠየቅ ነው

ሸ/ የ40 ፥ የ80 ቀን ሕፃናት በፊት፥ በኋላ ንዑስ ክርስቲያን የሚጠመቁበት ምክንያት ሕፃናት የኖሎት የቅዱሳት እንስት ፤ ንዑስ ክርስቲያኑ የስብአ ሰገል ፥ የሐዋርያት ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው ።

ቀ/ ወንዶች ሴቶችን፥ ሴቶች ወንዶችን ክርስትና እንዳያነሱ የተከለከለበት ምክንያት በፆታቸው ለማስተማር እንዲመች ነው ።

## 8/ ለንዑስ ክርስቲያን የሚደረግ የቅብዐ ቅዱስ ሥርዓት

ሀ/ ዳዊት ይደገማል ።ጸሎተ አኰቴት ይደርሳል ። ንዑስ ክርስቲያኑ ይታጠናል ።

ለ/ ዲያቆኑ ጸሎት እያዘዘ ሕዝቡ ይጸልያል ።

ሐ/ ካህኑ ቀርነ ቅብዑን በእጁ ይዞ ጸሎተ ዘይት ይጸልያል።

መ/ ካህኑ ዘይቱን ከጸለየበት በኋላ ወንዱን፥ ደረቱን ልቡን ትከሻውን፥ የእጁን መዳፍ ውስጡንና ውጭውን፥ ጀርባውን ይቀባል ። ሲቀባም "ዕቀብዐከ በስመ እሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ እግዚአብሔር አሜን" እያለ ነው ።



ሠ/ ካህኑ በየተራው የዘይቱን ጸሎትና ቡራኬ ከአደረሰ በኋላ ንዑስ ክርስቲያኑን በዘይቱ በተቀላቀለ ውኃ /ጠበል/ ይረጨዋል ።

ረ/ በመጨረሻው ሥርዓተ ጥምቀት አድርሶ ቅብዐ ቅዱሱን ቀብቶ ያጠምቀዋል ።

## ክፍል 3

## ሐ/ ሥርዐተ ሜሮን

### 1/ የሜሮን አመሠራረት

ሜሮን ማለት ቅባት ማለት ነው ።፤ እርሱም መልካም መዓዛ ከሚሰጡ ዘይትንት ከአላቸው ዕፀዋት ተነጥሮ የሚወጣ ቅብዕ ነው ።ሲሠራ በፓትርያርክና በጳጳሳት ጸሎት ይባረካል፥ ይከብራል ።

ከብዙ ዕፀዋት እየተቀመመ በማንጠር እስከ አሁን እየተሠራ መጥቷዋል /ዮሐ. 2;፡27 /

የሜሮን ምሳሌ የሆነ በኦሪቱ ታቦትና የደብተራ ኦሪቱ ንዋያተ ቅድሳት የሚከብሩት ፥ ካህናት ሲሾሙ ፥ ነገሥታት ሲነግሡ የሚቀቡት ቅብዐ መንግሥትና ቅብዐ ክህነት እንደነገረን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እናገኛለን /ዘፀ. 28፡41፣29፡7-21፣40፡9-16፤ዘሌዋ.4፡3፣ 6፡20-22 ፣ 7፡36፣ 8፡2-30፣ 21፡10-12፤ 1ሳሙ. 9፡16፣ 10፡1 ፤16፡1-13፤1ነገ.1፡34-45/ ።

በዘመነ ሐዲስም በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ አንብሮተ እድና ቅብዐ ሜሮን እንዲደረግ ሐዋርያት በሲኖዶስ አዝአዋል።



አዲስ የተሠራ ቤተ ክርስቲያንና አዲስ ንዋየ ቅድሳት በቅብዐ ሜሮን ይከብራል ። ታቦትም የሚከብረው በቅብዐ ሜሮን ነው።

### 2/ የሜሮን አቀባብ ሥርዐት

ሀ/ ሜሮን ከጥምቀት አይለይም ተከታትሎ ሁለቱም ምሥጢር ዕለቱን ይፈጸማል ።

ለ/ ሜሮን በጳጳሳት ከተባረከ በኋላ ቄስ በእጅ ይዞ ይጸልይበታል ። መጽሐፈ ክርስትና ያነብባል።

ሐ/ የተጠማቂውን ሰውነት ክፍል ክፍሉን እየለየ በትእምርተ መስቀል አምሳል 36 ሕዋሳቱን ይቀባል።

መ/ በሥርዓተ ጥምቀት እንደተገለጠው ካህኑ ሴቱየዋን ንዑስ ክርስቲያን ከአንገትዋ በላይ ያለውን አካሉዋን ከቀባ በኋላ ከዚያ በታች ያለውን ሰውነቱዋን ዲያቆናዊት ሴት የ ካህኑን እጅ ይዛ ትቀባታለች ።

ሠ/ ዲያቆን ተጠማቂው ራሱን ዝቅ አድርጎ /በአትሕቶ ርእስ/ በእግዚአብሔር ፊት እንዲቆም ያዝዛል ።

ረ/ ክህኑ ሜሮኑን ይዞ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል ።

ሰ/ ካህኑ ሜሮኑን በመጀመሪያ በትምእርተ መስቀል አምሳል እያመሳቀለ በገጹ /ግንባር/ ግራና ቀኝ ሁለት ላይ ይቀባል ። ግንባሩን ሲቀባ በፊቱ ላይ ዕፍ ይልበታል ።

ሰ/ ተጥሎም ትብዐ ቅዱስ አቀብዐከ ለሱታፌ ሕይወት ዘለዓለም እያለ ሁለቱን የአፍንጫውን በር ሁለት ፥ ሁለቱን ከናፍር ሁለት ፤ የቀኝ ጆሮ አንድ ፤ የግራ ጆሮ አንድ ፤ የቀኝ ዓይን አንድ ፤ የግራ ዓይን አንድ ፤ ደረት አንድ ፤ ልብ አንድ ፤ ከማህል ራስ እስከ ወገብ አንድ ፤ ማህል ጀርባ አንድ ፤ ዕንብርት አንድ ይቀባል ።

ቀ/ ከዚያም ዕቀብዐከ ለእምላክ መሢሕ በማኅተመ ዘኢይትፈታሕ እያለ ቀኝ እጁ አንድ ፤ ግራ እጅ አንድ ፤ የእጆች መገናኛዎችን ሁለት ፤ የቀኝ ትከሻ አንድ ፤የግራ ትከሻ አንድ ፤ ማጅራት አንድ ፤ አንገት አንድ፤ የቀኝ ክርን አንድ፤ የግራ ክርን አንድ ፤ የሁለት እጅ መዳፍ የውጭው ሁለት ፤ የውስጡ ሁለት ይቀባል።

በ/ እንዲዚሁም እቀብዕከ ቅብዐተ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ እያለ የእግር መገናኛዎችን /ዳሌ ፥ ሙላ ፥ ታፋ/ የሁለት እግር ጉልበት ሁለት ፤ የሁለት እግር ጣቶች የውጭው ሁለት ፤ የውስጡ ሁለት ይቀባል ።

ተ/ ካህኑ ሜሮን ቀብቶ ከፈጸመ በኋላ በተጠማቂው ላይ እጁን ጭኖ /በእንብሮተ እድ/ ቡሩክ ኩን በበረከተ መላእክት ሰማያውያን ... እያለ ይባርከዋል ።

ቸ/ ከዚያ በኋላ ተጠማቂው ነጭ ልብስ ይለብስና በራሱ ላይ አክሊል ይቀዳጃል ።



## 3/ በሜሮን የሚገኝ ጸጋ

ሜሮን የእግዚአብሔር ጸጋ ለምእመናን የሚሰጥበት ፥ መንፈስ ቅዱስ የሚያድርበት ምሥጢር ነው።

በጥምቀት የሚሰጠውን ሀብተ ጸጋ የሚያረጋግጥ የሚያጸና ማኅተም ሜሮን ነው ። በጠቅላላው መንፈሳዊ ሕይወት በጥምቀት ይጀመራል ማለት ዳግም ልደት ይወለዳል ፤ በሜሮን ይታተማል /የሐ.ሥራ 8:14-17/ ።

## 4/ የሥርዐተ ሜሮን ትርጉም

ሀ/ ሜሮን ከብዙ ዓይነት ዕፀዋት ተደባልቆ ተሠርቶ አንድ መሆኑ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን ሀብቱ ብዙ የሆኑ ምሳ ነው /ቆር. 12:4-31/ ።

ለ/ አክሊል የሚቀዳጀው አይሁድ በዕለተ ዓርብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያቀዳጁት አክሊለ ሦክ ምሳሌ ነው /ማቴ 27:29 ፤ ዮሐ. 19:2፤ ማር. 15:17/ ።

## ክፍል 4

## መ/ ሥርዐተ ቍርባን

### 1/ የመሥዋዕትና የቍርባን አመሠራረት

መሥዋዕት መሠዋት ፥ ቁርባን ማቅረብ የተጀመረ በአዳም ጊዜ ነው ። ከአዳም እስከ ሙሴ የተነሡ አበው ሁሉ በሕገ ልብና ለእግዚአብሔር



መሥዋዕት ይሠው፥ ቁርባን ያቀርቡ ነበር ። መሥዋዕታቸውም ከእንስሳ ሲሆን ቁርባናቸው ከእህልና ከአትክልት ማለት ከስንዴ እህል ፥ ከወይን ፍሬ የሚቀርብ ነበር /ኩፋ. 5:1-5 ፤ ሀፍ. 4:3-5 ፤ 8:20. 21፤ 12:8-9፤ 13:4-18፤ 14:18፤ 22:2-13፤ 26:25/ ።

### 2/ መሥዋዕተ ኦሪት

በዘመነ አበው ይደረግ እንደነበረው የመሥዋዕት አቀራረብ በኦሪትም በሁለት ዓይነት ይሠራ ነበር። ይኸውም ከሥጋ ከደም ወገን የሆነው መሥዋዕት ፤ ከእህል ወገን የሆነው ቁርባን ይባል ነበር /ዘፀ. 29:39-42 ፤ ዘሌ. 7:20-30፤ 7 በሙሉ፤ 8 በሙሉ ፤ 9 በሙሉ፤ 110:12-20 ፤ መዝ. 49:8 ፤ 1ነገ. 18:32-38/።

መሥዋዕቱና ቁርባኑ የሚቀርበው የሠርቀ ወርኀ /መባቻ/ የሰንበትና /ቀዳሚት/ የታላላቅ በዓላት ዕለት ሲሆን የፈቃድ፥ የምስጋና ፥ የበዓል፥ የነድኃኒት፥ የንስሐ፥ የብፅዓት፥ የቅንዓት እየተባለ ይጠራ ነበር ።

መሥዋዕት አቅራቢዎችና ቦታው ልዩነት ነበራቸው ። ይኸውም ከመጋረጃ ውጪ ቦታው ቅድስት ፥ መሥዋዕት አቅራቦዎች ካህናት፥ ከመጋረጃ ውስጥ ቦታው ቅድስተ ቅዱሳን፥ መሥዋዕት አቅራቢው ሊቀ ካህናት ይባል ነበር።

ጊዜውም እንዲዚሁ ልዩነት ስለነበረው ካህናት ዘውትር ሲሠው የካህናቱ አለቃ በዓመት አንድ ቀን ይሠዋ ነበር /ዕብ. 9:6-7/ ።



ካህናቱም ሆኑ ሊቀ ካህናቱ አስቀድሞ ስለነበራቸው በደል መሥዋዕት ከሠው በሓላ ነበር ስለሕዝቡ ሓጢአት መስዋዕት የሚያቀርቡት /ዕቢ 7:27/ የምሥዋዕት ኦሪት አቀራረብ እንዲህ ሲሆን መሥዋዕቱ የማንጻት ሓይል አልነበረውም።

### 3/ መሥዋዕተ ወንጌል

ወልደ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ወደ በአቀረበልን በሥጋው በደሙ ቅዱስ ቁርባንነት እኛ ሁላችን እንከብር ዘንድ ለሚያምኑ ሁሉ መንጻት ፥ ሥርየተ ሓጢአተ ፥ ክብር ፥ ሕይወት ፥ የሚገኝበትን አንዲት መሥዋዕት ለዘለዓለም የማትሻር የማትለወጥ አድርጎ ሠራ ይችም መስዋዕተ ወንጌል ናት /ዕብ.10-14/።

አይሁድ ስለሓላፊው መብል ብቻ አጥብቀው ሲፈልጉት ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ለኃላፊው መብል ሳይሆን ዘለዓለም ለሚኖረው ምግብ አስቡ" ቢላቸው "አባቶቻችን ከሰማይ እንጀራ በሉ አንተስ ከዚህ የተሸለ ምን ተአምራት ታደርጋለህ" አሉት ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን "ይህ ሙሴ የሰጣችሁ እንጀራ አይደለም ይህ ከሰማይ የወረደ ኅብስት ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው ። እኔም የምሰጣችሁ ኅብስት ሥጋዬ ነው ፤ በእኔ የሚያምን አይራብም ፤ አይጠማም ፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ እንጀራ በሉና ሞቱ ፤ ከዚህ ኅብስት የሚበላ ግን ለዘለዓለም ይኖራል እንጂ አይሞትም፤ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ለዘለዓለም ሕይወት የምሰጠው ምግብ ሥጋዬ ነውና በእውነት እነግራችኋለሁ የወልደ ዕጓለ እመሕያውን ሥጋውን

ከአልበላችሁ ደሙንም ከአልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላችሁም" ብሎ አስተምሮዋቸዋል /ዮሐ. 6፡27-58/ ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሙስ ማታ አይሁድ በብሉይ ኪዳን ሥርዓት በጉን በመቅደስ አርደው ፥ ሲመሽ ወስደው ፥ በቤታቸው ከተካፈሉት በኋላ ምሳሌ የነበረው በግዐ ፍሲካ አልፎ "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም" የተባለው አማናዊ መሥዋዕት ተተካ /ዘፀ.12፡3-15 ፤ ዮሐ. 1፡29/ ።

በብሉይ ኪዳን ስለፋሲካ በዓል አከባበር በሚደረገው ማዕድ ላይ ተቀምጦ ሳለ አምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፋሲካው ራት ከቀረበው ኅብስት አንሥቶ አመስግኖ ባርኮ ቆርሶ "ስለእናንተና ስለብዙዎች ቤዛ የሚፈተትና የሚሰጥ ሥጋዬ ይህ ነው ።እንኩ ብሉ" ብሎ ሰጣቸው ።እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶ፥ አመስግኖ አክብሮ "ስለእናንተ ስለዓለም ሕይወት የሚፈስው አዲስ ሥርዓት ሁኖ የሚሰጠው ደሜ ይህ ነው ። እንኩ ጠጡ" ብሎ ሰጣቸው /ማቴ. 26፡26-28 ፤ ማር. 14፡17-25፤ ሉቃ 22፡14-38 ፤ ዮሐ. 6፡56-59፤ 1ቆሮ. 11፡23-26/ ።

እነሱም አምነው ተቀብለው ሥጋውን በሉ ደሙን ጠጡ ፈጣሪያችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ምሥጢርን ሠርቶ አሳይቶ "መታሰቢያዬን እንደዚህ አድርጉ" ብሎ ስለ አዘዛቸው ሐዋርያት ከክርስቶስ የተቀበሉትን ትእዛዝ ለቤተ ክርስቲያን በመስጠታቸው ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ሕማሙን፥ ሞቱን፥ ትንሣኤውን ዕርገቱን ፥ ዳግም



ምጽአቱን በልብ እየአሰበች ፥ በአፍዋ እየመሰከረች በሐዲስ ኪዳን ለሐዲስ ሥርዓት የተሰጠውን የዓለሙን ኃጢአት የሚያስተሠርየውን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔርን ደመ ወልደ እግዚአብሔርን ስትቀበል ስታቀብል ኖራለች ትኖራለች ።

## 4. ለቁርባ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ/ የሚቀድሱና የሚቆርቡ ሰዎች በጋብቻ ሥርዓት የሚኖሩ ከሆኑ ከመቀደሳቸውና ከመቁረባቸው በፊት 3 ቀን ፥ ከቁርባን በኋላ ሁለት ቀን ከሩካቤ ሥጋ መከልከል ይገባቸዋል ።

ለ/ ቁርባን መቀበል ንስሐ ገብቶ ከኃጢአት ነጽቶ ነው። ከክርስቲያን ወገን ማንም ሰው የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ትንሣኤ ዘለሕይወትን ሊወርስ ቢወድ ልቡን ከቂም ከበቀል ሰውነቱን ከበደል ንጹሕ አድርጎ መቀበል አለበት ። ይህም ማለት ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዝዞ ስለማያወቀው ይቅር በለኝ እያለ በንጹሕ ይቁረብ ማለት ነው ።ከኃጢአት ሳይነጻ ቢቀበል ግን የጌታ ሥጋ እንደ ሆነ አላወቀምና እንደ ምድራዊ ምግብም አቃልሎታልና በኃጢአት ሳለ ያለ ኃፍረት በድፍረት ሥጋውን ደሙን በመቀበሉ ሥላሴ ይፈርዱበታል /1ቆሮ. 11፡23-29/ ።

ሐ/ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል 18 ሰዓት ከእህል ከውሀ ተከልክሎ መጾም ይገባል /ኢይንሣእ መኑሂ. ቁርባነ ዘእንበለ ይጹም በንጹሕ /ፍት.መን. 13 ፤ ረስጠብ 46/ ።

መ/ ሰው ዝንየት /ርስሐት/ ከአገኘው በዚያ ቀን አይቆርብም።



ሠ/ ካህን በሚቀድስበት ቀን ዕንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር፥ ትውኪያ /እንቃር/ ብስና ማንኛውም የአካል መድማት መቁሰል ወደ አፍ የሚገባ እንደ ትንኝ ዝምብ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያው ዕለት መቀደስ መቁረብ አይገባውም ።

ይህም ለካህን ብቻ ሳይሆን ምእመናንንም የሚመለከት ነው ።ከቁርባን በኋላ ከአለመጠንቀቅ የተነሣ እንዲህ ያለ ነገር ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው የገባል ። ንስሐውን ሳይፈጽም እንደ ገና መቁረብ አይችልም /ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ/ ።

## 5/ ለመሥዋዕት የሚገባ ስንዴ

ሀ/ መሥዋዕት የሚሆነው በወራቱ የደረሰ፥ ዋግ ያልመታው እንክርዳድ የሌለበት ንጹሕ ስንዴ ነው /ፍት.መን.13 ረስጠጅ 3/ ።

ለ/ ለመሥዋዕት የሚቀርበው ኅብስት ዕለቱን የተሠራ እንዲሆን ታዝዙዋል ።ከተሠዋም በኋላ ለማግሥቱ አያድርም /ፍት. መን. አን. 13 ረስጠብ 30/ ።

ሐ/ ኅብስቱም ነቅዕ ያለበት አይሆንም ነቅዕ የሌለበት ያላረረ ያልጠቆረ እንዲሆን ታዝዘዋል /ፍት.መን. 13 በስ. 98/ ።

መ/ ኅብስተ አኰቴቱ ሲሠራ አሥራ ሦስት መስቀል በአለው ማኅተም ታትሞ ይሠራል ።

## 6/ ለመሥዋዕት የሚገባ ወይን

ሀ/ ወፍ ያልመጠጠው፥ አይጥ ያልቆረጠመው መጀመሪያ የደረሰው ወይን ሊሆን ይገባል ።



ለ/ ለመሥዋዕት የሚቀርበው ወይን በእሳት ከሚበስሉ ከበድ ፥ ከአረቂ ወገን በማንኛውም አይሠራም /ፍት.ነገ.13 ፤ ረስጣ 3/ ።

ሐ/ ወይኑንም ሲሠሩ ጥሩ መሆኑን ተመልክቶ መሥራት ይገባል ። ንጹሕ ጽሩይ ከአልሆነ ለመሥዋዕት አይገባም። ከሚሶ የበለጠ ውሀም አይጨመርበትም /ፍት.መን. 13 ፤ በስ. 99/ ።

መ/ ዓመት ያለፈውና መዓዛው የለወጠ ወይን ለመሥዋዕት ሊቀርብ አይገባም/ ፍት. መን. አን. 13፤ በስ. 102/ ።

## 7/ በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ ካህናትና ምእመናን የሚቆሙበት ቦታ

ካህናትና ምእመናን በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ በየት መቆም እንዳለባቸው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የታዘዘላቸውን፥ በየማዕርጋቸው የሚቆሙበትን ቦታ በክፍል 1 የቤተ ክርስቲያን ሥራ አቅድ /ፕላን/ በሚለው ርእስ ተተንትኖ የተነገረ ስለሆነ እዚህ ላይ በድጋሚ ማንሳት አስፈላጊ አይደለም።

ካህናትና ምእመናን በተወሰነላቸው ቦታ እንዲቆሙ ዲያቆናት ማስተናበር አለባቸው "ወይኩኑ ዲያቆናት ዘያስተሐምሙ ከመይባዕ ለለ አሐዱ አሐዱ ውስተ መካነ ዘሥሩዕ ሉቱ" /ፍት. መን. አን. 12 ፤ ድስቅ. 12 ፤ ኒቅያ 61/ ።

## 8/ መቀደሻ አልባሳት

ሀ/ የሚቀደስባቸው አልባሳት ለቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ሊቀመጡና በንጽሕና ሊጠበቁ ይገባል ።ከዚህ ውጪ በሌላ ቦታ እንዲቀመጡ

እልተፈቀደም /ሕዝ. 44፡19 ፤ ፍት. መን. 12 ፤ ዳን. 5፡1-ፍ/ ፡፡

ለ/ ካህናት የሚደርቡት ካባ ላንቃ አምስት መንዲል /ከልጅ/ ያለው እንዲሆን ታዝዙዋል፡፡ መንዲል ወይም ከልጅ ማለት ለምድ ነው ፡፡

ሐ/ ካህናት በቀደሱ ጊዜ የሚለብሱት እስከ ተረከዛቸው የሚደርስ መሆን አለበት /ፍት. መን. አን. 12/ ፡፡

መ/ ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ልኩ የሚሆነውን መርጦ ይለብሳል፡፡ ልብሰ ተክህኖ ከለበሰ በኋላ ማውለቅ አይገባውም ፡፡ ቀሚሱ ከረዘመበት በዝናር ይታጠቀዋል /ፍት. መን. አን. 12/ ፡፡

ሠ/ የሚቀድሱ ካህናት ሲቀድሱ ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ታዝዞአል ፡፡ የሚቆርቡ ምእመናንም ንጹሕ ነጭ ልብስ ለብሰው መቁረብ ይገባቸዋል፡፡ ወአልባሰ ቅዳሴሰ እለ ለካህናት ወአኮ ኅብራት /ፍት. መን. 12 ፤ በደስ. 37፤ በስ. 96/ ፡፡

ረ/ ክህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ጳጳስ ከአለ ጳጳሱን አስባርኮ ይለብሳል ከሌለ ራሱ ባርኮ ይለብሳል፡፡

## 9/ ሥርዓተ ቅዳሴ

ሀ/ ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት አብሮት የሚቀድስ ዲያቆን መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡



ለ/ ካህን ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ በታቦቱ ፊት ከመጋረጃ ውጪ አንድ ጊዜ በመጋረጃ ውስጥ በመሠዊያው ፊት ሦስት ጊዜ ይሰግዳል /ሕዝ. 46፡3/ ፡፡

ሐ/ ካህን በክብር በፍርሃት ሆኖ "ተንሥኡ ጸልዩ" እያለ ለሕዝቡ የሚሰብክለት ዐዋጅ የሚናገርለት ዲያቆን ሳይዝ እንዳይቀድስ ተከልክሎዋል፡፡ ዲያቆኑም አስምቶ የሚያነብና የሚያዜም ሊሆን ይገባል፡፡

መ/ ሕዝቡ ሳይሰበሰቡ ቅዳሴ መግባት ክልክል ነው /ፍት. መን. አን. 12 ፤ በስ 97/ ፡፡

ሠ/ ሕዝቡ እንዳይፈዙ፥ እንዳያንቀላፉ ዲያቆኑ ያነቃቃቸዋል /ፍት. መን. አን. 12 ፤ ስድቅ 12/ ፡፡

ረ/ ካህኑ ቅዳሴ ሲገባ ከሁሉ በፊት አንድ ጊዜ በታቦቱ ፊት ሰግዶ አንድ ጊዜ ቀሳውስቱን አንድ ጊዜ ዲያቆናቱን እጅ ይነሣል፡፡

ሰ/ የሚለብሰውን ልብሰ ተክህኖ ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ 3 ጊዜ ሰግዶ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልያል፡፡

ሸ/ ዲያቆን በቤተልሔም ኅበስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት ከሠራና ከአዘጋጀ በኋላ ንፍቁ ዲያቆን ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ላይ አድርጎ፥ ወይኑን ሠራዒው ዲያቆን በጽዋዕ ይዞ ቃጭል እያቃጨለ በፊት በፊት ፥ ንፍቀ ቄስ መስቀልና ማዕጠንት ይዞ እያጠነ በኋላ በኋላው



ሆነው ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ ፡፡ /ፍት መን. 12 ፤ ረስጠብ 92/ ፡፡

ቀ/ በደብረ ታቦር ዕለትና እሑድ እሑድ አራት ኅብስት ይገባል፡፡ ዘወትር ግን ሦስት ሦስት ይገባል ፡፡

በ/ ደሙ በምድር ላይ እንዳይፈስ ጽዋውን ከመጠን በላይ መሙላት አይገባም ፡፡ሲያቀብልም መጠንቀቅ አለበት /ፍት. መን. አን. 13 ፤ ረስጣ 45/ ፡፡

ተ/ ቅዳሴ ሲገቡ ቀዳስያን መንበሩን ከብበው ይቆማሉ ፡፡ሠራዒ ካህን ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ በምዕራብ ይቆማል ፡፡ሠራዒ ዲያቆን ፊቱን ወደ ምዕራብ አድርጎ በምስራቅ ይቆማል ፡፡ንፍቅ ካህን ፊቱን ወደ ሰሜን አድርጎ በደቡብ ይቆማል ፡፡ንፍቅ ካህን ፊቱን ወደ ደቡብ አድርጎ በሰሜን ይቆማል ፡፡ሦስተኛው ቄስ በስተግራ ቆሞ ለሠራዒው ካህን መብራት ያበራለታል ፤ መጽሐፍ ይገልጥለታል ፡፤ሦስተኛ ሆኖ የሚገባ ቄስ ባይኖር ዲያቆን መብራት ያበራል መጽሐፍ ይገልጣል ፡፡ይህን ሲሠራ ግን ዲያቆን መንበሩን እንዳይጠጋና እንዳይዳስስ መጠንቀቅ ይገባዋል፡፡

ቸ/ ዲያቆናት በዐውደ መንበሩ ቆመው ተሰጠውን ይቀበላሉ ፤ በተለይ 2 ዲያቆናት ከልዝብ ሐር የተሠራ መነሳንስ ይዘው አንድ በቀኝ ፥ አንዱ በግራ ቆመው ወደ ጽዋው ምንም ምን እንዳይገባ ተሐዋስያንን የከለክላሉ /ፍት. መን. አን. 12 ፤ ረስጣ 52/ ፡፡



ኀ/ የሚቀድሱ ካህናት በቅዳሴ ጊዜ የጌታን ነገረ መስቀል በማሰብ በቅድመ እግዚአብሔር መቆማቸውን ባለመዘንጋት ይቀድሱ እንጂ ዜማውን ከልክ አሳልፈው በማቀማጠል ማዜም አይገባቸውም /ፍት. መን. አን. 12 ፤ በስ. 99/፡፡

ነ/ የሚቀድሰው ካህን በሥጋዬ ይቀስፈኛል ፤ በነፍሴ ይፈርድብኛል ብሎ ፈርቶ መቆም ይገብዋል ፡፡

ኘ/ በቤተ ክርስቲያን የተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ የእግዚአብሔርን ነገር /ትምህርቱን ጸሎቱን/ ለመስማት በጸጥታ መቆም አለባቸው ፡፡ተስጥዎ ከመቀበል በቀር መናገር መሳቅ አይገባቸውም በቅዳሴ ጊዜ ፈጽሞ የሚስቅ አይኑር /ፍት. መን. አን. 12፤ ድስቅ 12 ፤ ኒቅያ 61 ፤ በስ 72/ ፡፡

አ/ ካህናት በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ጥምጥማቸውን ማውለቅ ቀጸላቸውን ማውረድ ወንጌልና ኪዳን ሲነበብ አክሊላቸውን ማውረድ ቢያቅታቸውም ወንጌል ሲነበብ ይህን መፈጸም አለ ፡፡ ወንጌል ሲነበብ ማድረግ ባይቻልም በሚሳለሙበት ጊዜ ራስን መግለጥ ግዴታ ነው፡፡

ከ/ ወንጌል ሲነበብ መቆም ነው እንጂ መቀመጥ ክልክል ነው፡፡

ኸ/ ወንጌል ሲሳለሙም ነአምን በቃለ ወንጌል ቅዱስ እያሉ ን ነው ፡፡

ወ/ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ኤጲሥ ቆጶስ ከአለ ወንጌሉን በእጁ ይዞ በክፍሎቹ የተነበበውን ለሕዝቡ ተርጉሞ መንገር ይገባዋል ፤ ኤጲስ ቆጶሱ ከሌለ ትርጓሜውን የሚችል ካህን እንዲያስተምር ታዝዙዋል /ፍት. መን. 12 በደስ 99/ ፡፡

ዐ/ ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄሱ መንጌልን ከማንበቡ በፊት ንፍቅ ቄስ "ርኑቀ መዓተ" የሚለውን ጸሎት ይጸልያል ::

ዘ/ ካህኑ በስርዓተ ቅዳሴ መጀመሪያና በፍሬ ቅዳሴ መጀመሪያ ሁለት ጊዜ እጁን ይታጠባል:: እንዲሁም ሌሎች ካህናትና ዲያቆናት ከቁርባን አስቀድሞ እጆቸውን ይታጠባሉ ::

ዠ/ በቅዳሴ ጊዜ በ2 ጧፍ እንጂ በአንድ ጧፍ አይቀደስም::

የ/ ካህኑ በቅዳሴ ጊዜ ሙቀት ሳይለየው ሥጋውን ደሙን ለማቀበል ይችል ዘንድ የነቃ የተጋ መሆን አለበት::

ደ/ በቅዳሴ ጊዜ ዕርገተ ዕጣን አይቀርም የሚደረገውም ዕርገተ ዕጣን አምስት ጊዜ ነው /አብጥሊስ 3/ ::

ጀ/ ማዕጠንቱን /ጥና/ የሚይዝና የሚያጥን ቄስ ነው እንጂ ዲያቆን በእጁ ይዞ አያጥንም ::ኤጲስ ቆጶስ መሥዋዕቱን ከአጠነ በኋላ ሕዝቡንና ካህናቱን ፥ ቤተ ክርስቲያኑ እየዞረ እንዲያጥን ጥናውን ለቄስ ይሰጣል /ድስቅ 12 ፤ 23 ፤ 38/ ::

ገ/ የቅዳሴ ቡራኬያት 42 ናቸው ::እነዚህም 21 የአፍአ 21 የውስጥ ቡራኬያት ናቸው :: የአፍአ ቡራኬ ለካህናትና ለሕዝብ ነው ፤ የውስጥ ቡራኬ ግን በሥጋ ወደሙ ላይ ነው ፤ የአፍአ ቡራኬ በመስቀል ነው ፤ የውስጥ ቡራኬ ግን ካህኑ በእጁ በሥጋውና በደሙ ይባርካል ፤ ንፍቅ ካህን ግን አይባርክም ::ሠራዒው ካህን ሥጋ ወደሙን ::



በእጁ እንጂ በመስቀል አይባርክም ::ጽዋውንም ሲባርክ የጽዋውን ከንፈር በግራ እጅ መያዝ አይገባውም :: በቀኝ እጁ በተአምርተ መስቀል አምሳል መወዝወዝ አለበት ::

ጠ/ በቅዳሴ ጊዜ የሥዒው ካህን ዑደት ሰባት ነው ፤ ይኸውም በመጀመሪያው ጸሎተ ዕጣን በመቅደሱ ውስጥ 3፥ በአንቀጸ ምዕራብ "ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ" እያለ አጥኖ ከፈጸመ በኋላ "እግዚአብሔር አምላክነ በከመ እንሀልክ ቅድመ ጥቅማ ለኢያሪኮ" እያለ ሲዞር አንድ፥ በ2ኛው ጸሎተ ዕጣን 3፥ በድምሩ 78 ዑደት ይሆናል ::

ጨ/ የንፍቅ ካህን ዑደት ሦስት ነው :: "ግብረ ሐዋርያት" እንብቦ ሲገባ 1 ፥ "ወንጌል" ተነብቦ ሲገባ 1 ጊዜ ፥ "ሠራዊተ መላእክቲሁ" ተብሎ ሲገባ አንድ ጊዜ ይዞራል ::በድምሩ 3 ይሆናል ::

ደ/ እማሬያት 11 ናቸው :: እነዚህም በጸሎተ ዕንፎራ 2 ፥ "አዕኰተ" ሲል በሥጋው አንድ በደሙ 1፥ "ይረስዮ" ሲል 2፥ "ሥጋ ቅዱስ" ሲል አንድ፥ "ደም ክቡር" ሲል 1 ፥ "እስመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ" ሲል 1፥ በመጀመሪያው "አአምን" 1፥ በመጨረሻው "አአምን" አንድ ሲደመር 11 ይሆናል::

ፀ/ ጸሎተ ቅዳሴ ከተጀመረ በኋላ ዲያቆን "ዕትው በሰላም" ብሎ ሳይሰናብት በከባድ ችግርና በሕመም ከአልሆነ በቀር ከቤተ ክርስቲያን መውጣት ክልክል ነው /ፍት. መን. አን. 12፤ በስ 92/ ::



ዲያቆን "ጸልዩ በእንተ ሰላም" ብሎ ስለ ሰላም እንዲጸለይ በቅዳሴ ላይ ተእዛዝ ሲሰጥ ወንዶች ወንዶችን፥ ሴቶች ሴቶችን ፥ ሁሉም በየጾታቸው እጅ ይነሣሣሉ ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ወንዶችን እጅ አይነሡም /ፍት መን. 12 ፤ ረስጣ 103፡32፡53/::

ፐ/ ካህኑ ጎብስቱን ሲፈትት ከላይ ወደታች፥ ከቀኝ ወደግራ፥ ከግራ ወደቀኝ፥ ከታች ወደላይ በትክክል መስቀሉንተከትሎ ይፈትተዋል:: ሲፈትትም እንዳይነጥበው መጠንቀቅ አለበት /ፍት. መን. 12 ፤ በስ 99/ ::

## 10. ለመቁረብ የሚያበቃና የማያበቃ ሁኔታ

ሀ/ ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ሰው አይቆርብም ፤ ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ካህንም እንደዚሁ ሥጋ ወደሙ ሊቀበል ሊያቀብል አልተፈቀደለትም /ገፍት.መን. 13 ረስጠብ 44/ ::

ለ/ ከምእመናን በስተቀር ያላመኑ ሰዎች ሥጋ ወደሙ እንዳይቀበሉ መጠበቅና መቆጣጠር ያስፈልጋል /ፍት.መን. 13 ረስጠብ 44/ ::

ሐ/ በንስሐ የተለየ ሰው የንስሐ ጊዜውን ሳይፈጽም ለሞት የሚያበቃ ደዌ ቢታመም ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም:: ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ከዳነም ከምእመናን ጋር በጸሎት ይሳተፋል ፤ በቀኖና ወደ ተለየ ሰዎች አይመለስም /ፍት መን. 13 ፤ ዕንቁራ 15/ ::



መ/ ጋኔን የሚጥለው፥ ሕመም ያለበት ሰውን የማይስድብ ፥ ከጣለው በኋላ አረፋ የማያስደፍቀው ከሆነ ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይለከልም /ፍት. መን. 13/ ::

## 11. የቍርባን ሥርዐት

ሀ/ ሥጋውን ቄሱ በእጁ ሲያቀብል ደሙን ንፍቅ ቄስ በዕርፈ መስቀል ፥ ለካንናት ዲያቆን ለምእመናን በዕርፈ መስቀል ይሰጣል እንጂ ንፍቀ ቄስና ዲያቆን ሥጋውን ደሙን በእጃቸው አይነኩም ::

ለ/ ያቍራረቡ ተራ ቀጥሎ እንደተዘረዘረው ነው ::

1/ ሊቃነ ጳጳሳት
2/ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት
3/ ቆሞሳት
4/ ቀሳውስት እነዚህ ሥጋው ከታቦቱ ላይ ሳይነሣ በመንበር ላይ እንዳለ በቅድሚያ በየማዕርጋቸው ይቀበላሉ::
6/ ዲያቆናት በመቅደስ ይቆርባሉ::
7/ ከንፍቀ ዲያቆናት ጀምሮ ሁሉም በየማዕርጉ በ ቅድስት ይቀበላሉ::
8/ ከዐጸውተ ጎዋጎውና ከዲያቆናውያት በኋላ በዕለ ቱ ክርስትና የተነሡ ይቀበላሉ ::ከእነሱም ለ40 ና ለ80 ቀን ሕፃናት ቅድሚያ ይሰጣል::
9/ ከሕፃናት ቀጥሎ ደናግል
10/ የቀሳውስት ሚስቶች
11/ የዲያቆናት ሚስቶች

12/ መነኮሳት ምእመናን
13/ መነኮሳይያት
14/ ምእመናን ወንዶችና ሴቶች ተራቸውን ጠብቀው በየማዕርጋቸው ይቆርባሉ።

ሐ/ ቁርባን ለተቀበሉ ክሐዳፌ ነፍስ በኋላ ማየ መቁረር /የቅዳሴ ጠበል/ ይሰጣል /ፍት. መን. 13 ፤ ክርስጣ 65/።

## 12 ከቁርባን በኋላ የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ/ ከቆረቡ በኋላ በዚያው ዕለት ወደ ፍርድ ቤት መሔድና መሟገት ክልክል ነው /ጉባኤ ኒቅያ/ ።

ለ/ በቆረቡበት ቀን ከሚስት መገናኘት ፥ አብዝቶ መብላት መጠጣት ፥ ጥፍር መቁረጥና ጠጉር መላጨት ፥ በውሀ መታጠብ ፥ ከልብስ መራቆት ክልክል ነው /ሥርዓተ ቅዳሴ ቁ. 166/ ።

## 13/ የሥርዓተ ቅዳሴ አፈጻጸም

የሥርዓተ ቅዳሴው አፈጻጸም በመጽሐፈ ቅዳሴ እንደተጻፈው ነው። ከመጽሐፈ ቅዳሴው አንብቦ በመረዳትና በመገንዘብ ሥርዓቱን ጠብቆ መጸለይ ፥ መባረክና እማሬ ማድረግ ፥ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ፊትን መልሶ የሚባለውን ቀለም ለይቶ ማወቅና መፈጸም ፥ በዑደት ጊዜ የሚደረገውን ሄደት ቅደም ተከተል ጠብቆ መዞሮ ነው።



## 14/ የሥርዐተ ቍርባን ትርጕም

ሀ/ ወይን ለመሥዋዕት ሲቀርብና ሲታሽ ከወይኑ ውሀ መጨመሩ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ደም ብቻ ከጎኑ አልፈሰሰም ፤ ውሀም ስለፈሰሰ የዚያ ምሳሌ ነው /ዮሐ. 19:34/ ።

ለ/ ወይኑን ሲላክ ሁለት እጅ ወይን ፥ ሲሦ ውሀ የሚደረግበት ምክንያት በዕለተ ዐርብ ለንጊኖስ ቀኝ ጎኑን በጦር በወጋው ጊዜ ደሙ ግራና ቀኝ ውሀው በመካከል ስለወረደ የዚያ ምሳሌ ነው።

ሐ/ ብዙ ወይን ሲገኝ ዘጠኝ እጅ ፥ አሥረኛ ውሀ ተደርጎ የሚታሽበት ምክንያት ጌታ አሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል ሲቀበል በዘጠኝ ቦታ ደሙ ስለፈሰሰ ነው። ይኸውም ከራሱ ከአፍንጫው ከግርፋቱ ከጎኑ አምስት ቅንዋት ነው። በዚህ እንደ አዳነን ለማጠየቅ ነው።

መ/ ቀዳሾችና ቆራቢዎች ከመቀደሳቸውና ሥጋ ወደሙ ከመቀበላቸው በፊት 3 ቀን ከሴት ተከልክለው ተጠብቀው እንዲቆዩ የተደረገበት ምክንያት በአራቱ ዳዊትና ከርሱ ጋር የነበሩት ወደ ካህኑ ወደ አብያታር /አቤሜሌክ/ በመጡና የሚበሉት የቁርባን ኅብስት እንዲሰጣቸው ካህኑን በጠየቁበት ጊዜ ከሴት ከራቃችሁ ሦስት ቀን ሞልቷችኋላ ወይ ብሎ ወልስ ጠይቋቸው ነበር። እነሱም ከቤታችን ከወጣንና መንገድ ከጀመርን ሦስት ቀን ሆኖናል ብለው ሲመልሱለት ኅብስተ ቁርባኑን ሰጥቶዋቸው ዳዊትና ሠራዊቱ ስለበሉ የዚያ ምሳሌ ነው። ከዚያም ቀደም ብሎ እሥራኤል ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በተጠሩ ጊዜ ሦስት ቀን ከሴት እንዳይገናኙ ሙሴ ያዘዘ



ስለሆነ የዚያ ምሳሌ ነው /ዘፀ. 19:15 ፤ 1ሳሙ 21:1-6/ ። ከቁረቡ በኋላ ሁለት ቀን ከሴት የሚጠበቁት ዘካርያስ ሊቀ ካህናት ከዕጣን አገልግሎት ከወጣ ከሁለት ቀን በኋላ ከሚስቱ ስለተገናኘ ነው /ሉቃ. 1:22-23/ ።

ሠ/ ካህናት ወንጌል ሲነበብ አክሊላቸውን የሚያወርዱት ጌታ ከተጠመቀ በኋላ በፍልስጥኤምና በምድረ ይሁዳ በግብጽ የማስተማሩና የመታየቱ ምሳሌ ነው።

ረ/ ታቦት የእመቤታችን፥ ጽላት ከእመቤታችን የነሣው ሥጋና ነፍስ፥ በጽላት ላይ ያለ ቃል የተዋሐደው አካላዊ ቃል ምሳሌ ነው።

ሰ/ ምሥዋዑ /መሠዊያው/ ጻሕሉ፥ ጽዋው፥ የመንበረ ጸባዖት፥ የጎል ፥ የመቃብር ምሳሌ ነው።

ሸ/ መሶበ ወርቅ፥ ማዕጠንተ እሳት፥ የእመቤታችን ምሳሌ ነው ፍሕም የመለኮት ፥ዕጣን የትስብእት፥ መዓዛው የመዓዛ መሥዋዕት ምሳሌ ነው ።

ቀ/ ኅብስተ ቁርባኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ጻሕል የሚለብሰው ማኅፈድ ጌታ ሲወለድ የተጠቀለለበት ጨርቅ፥ ሲሞት የተገነዘበት መግነዝ ምሳሌ ነው ።ይኸውም ኅብስቱ የሚጠቀለልበት ማኅፈድ ነው።

በ/ ከላይ የሚለብሰው ማኅፈድ ጌታ ሲወለድ እናቱ ያለበሰችው ቈ ጽለ በለሶን ምሳሌ ነው /የልደት ድጓ/ ።



ተ/ ጻሕሉ ከላይ የለበሰው ሁለተኛው ማኅፈድ በበረት ሲወለድ የተነጠፈለት መንጸፈ እሳት ምሳሌ ነው።

ቸ/ በታቦት ላይ የሚነጠፈው ማኅፈድ የመንጦላዕተ እሳት ምሳሌ ነው /የቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ሠራዊት/ ።

ጻሕሉ ከላይ የለበሰው 3ኛው ማዕፈድ የጌታ መቃብር ድንጋይ ምሳሌ ነው ፤ ኅብስተ ምሥዋዑ የሚለብሰው የሚከደንበት ልብስ ጌታ የጠገነዘበት በፍታ ምሳሌ ነው።

ኀ/ ዕርፈ መስቀል /መንካ/ የሱራፊ ጉጠት ምሳሌ ነው /ኢሳ. 6:5-7/ ዲያቆን ደም ይሰጥበታል ሱራፊ ለነብይ ኢሳይያስ ፍሕመ እሳት በጉጠት ሰጥቶት ኢሳይያሥ ከለምፁ የመንጻቱ ምሳሌ ነው። ለምፁ ኃጢያት ምሳሌ ነው። ሱራፊ የዲያቆኑ ምሳሌ ነው። ፍሕሙን ሱራፊ በእጁ አለመያዙ፥ በጉጠት መያዙ ሥጋውን ደሙን ሲቀበሉ ከኃጢአት የመዳናቸው ምሳሌ ነው።

ነ/ በእሑድ በደብረ ታቦር 4 ኅብስት የሚገባው ጌታ እሑድ በደብረ ታቦር 3 ሐዋርያት ይዞ የመውጣቱ ምሳ ነው ። በዘወትር 3 ኅብስት የሚገባው የፈያታይ ዘየማንና የፈያታይ ዘፀጋም ምሳሌ ነው።

ኘ/ ቁርባን በአንድ ኅብስት የሚቆርብበት ምክንያት መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውና የተሠዋው አንድ አካል ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ነው።

አ/ ካህኑ እጁን ታጥቦ በርጥብ እጁ ኅብስቱን የሚመዘምዝበት የጥምቀቱ ምሳሌ ነው።

ከ/ ዲያቆን እግዚአብሔር ይፌእየኒን እያነበበ ጽዋውን ይዞ 3 ጊዜ የሚዞርበት ምክንያት ጌታ በምድረ ፍልስጥኤም እየተመላለሰ 3 ዓመት ከ3 ወር ወንጌል የማስተማሩ ምሳሌ ነው።

ኸ/ ቁርባኑ በጻሕሉ ላይ መቀመጡ ጌታ በመቃብር የመቀበሩ ምሳሌ ነው።

ወ/ ዕርገተ ዕጣን የደመ ዐቢል ፥ የቁርባነ ኖኅ ፥ የኂሩተ አብርሃም ፥ የመባዐ ይስሐቅ ፥ የመልእክተ ሙሴ ምሳሌ ነው/ ዘፀ. 4:9-12 ፣ 8:20፣ 12:1-3 ፣ 29:2-18፤ ዘፀ. 3:10-22፣ 4:1-3/።

ዐ/ ቡራኬ 42 መሆኑ ይኸውም የሕዝቡ 21፥ የሥጋ ወደሙ 21 መሆኑ ጌታችን በዕለተ ዐርብ ከሌሊቱ በ3 ሰዓት ከመዓልቱ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ 18 ሰዓት ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ ስመቀበሉ፥ ሦስት መዓልት፥ ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ለማደሩ ምሳሌ ነው። መዓልትና ሌሊት ሳይቆጠርም በመስቀል ላይ ከሞት በኋላ 2 ሰዓት መቆየቱንና የወረደበትን 1 ሰዓት በመቁጠር 21 ሰዓት ስለሚሆን ምሳሌው በዚህም ይሆናል።



ዘ/ ሕማሬ 11 መሆኑ የአሥሩ ሕዋሳት ፥ አንዱ የግዕዝ ርትዕት ምሳሌ ነው።

ዠ/ የሥራዒ ካህን ዑደት ሰባት መሆኑ ኢያሱ ወልደ ነዌ የኢያሪኮን ግንብ ሰባት ጊዜ ዞሮ እንዳፈረሰ ቄሱም 7 ጊዜ እየዞረ በሚጸልየው ጸሎት በሚያጥነው ማዕጠንት የምእመናንን የኃጢአት ግንብ ስለሚያፈርስ የዚያ ምሳሌ ነው። /ዕብ. 11:30/ ።

የ/ ካህኑ ዑደት በሚያደርግበት ጊዜ መብራት የያዘው የመጥምቁ ንፍቅ ዲያቆን ከካህኑ ፊት ቀድሞ የሚሄደው የመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌ ነው። ካህኑ ከንፍቅ ዲያቆን ቀጥሎ ተከትሎ የሚዞረው የጌታ ምሳሌ ስለሆነ ነው ። ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ ከጌታ መንፈቅ ቀጥሎ መከራ የተቀበለ ቅዱስ እስጢፋኖስ ነውና /የሐ. ሥ. 7:58/ ።

ደ/ በወንጌል ዑደት ጊዜ መብራት የያዘው ንፍቁ ዲያቆን መቅደሙ የነቢያት፥ ንፍቅ ካህን ወንጌል ተሸክሞ መከተሉ የመጥምቁ ዮሐንስ ፥ ሠራኢ ካህን እያጠነ ንፍቁን ቄስ ተከትሎ መዞሩ የጌታ ፥ ሠራኢ ዲያቆን በኋላ ሆኖ መዞሩ የእስጢፋኖስ ፥ ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው ።

ንፍቅ ቄስ ወንጌሉን ተሸክሞ ከካህኑ ፊት ከዞረ በኋላ ለካህኑ የሚሰጠው መጥምቁ ዮሐንስ መንፈቅ ከጌታ ቀድሞ ከአስተማረ በኋላ ጌታ ወንጌልን የማስተማሩ ምሳሌ ነው /ማቴ. 4:12-18/ ።



ጀ/ የንፍቅ ካህን ዑደት 3 ጊዜ መሆኑ የ3ቱ ሥላሴ አምሳል ነው /ማቴ. 28:19/ ።

ገ/ የጳውሎስ መልእክት ወደ ምዕራብ የሚነበበው የጳውሎስ መልእክትና ትምህርት የተሰጠው ማለት ጳውሎስ ያስተማረው በምዕራን ሀገሮች ነው።

ጠ/ የሐዋርያት ሥራና የሐዋርያት መልእክታት በሰሜንና በደቡብ የሚነበቡት ሐዋርያት በሰሜኑም በደቡብም ክፍለ ዓለማት እየተዘዋወሩ ወንጌልን ስለ ሰበኩ ነው /ማቴ. 28:19 ፣ የሐ. ሥ. 1:8/ ።

ጨ/ ወንጌል ወደ ምሥራቅ የሚነበበው ውእቱ አማረ ይሠርቅ ለክሙ ፀሐየ ጽድቅ ወሕይወት ታሕተ ክነፊሁ የተባለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የምትሰብክ ስለሆነ ነው /ሚልክያስ 4:2/ ያረገውም ወደ ምሥራቅ ነው ።የሚመጣውም በምሥራቅ ስለሆነ ነው /መዝ. 67:33 ፣ ማቴ. 24:27/ ።

ጸ/ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ዲያቆኑ ንዑስ ክርስቲያኖች ውጡ ብሎ የሚያውጅበት ምክንያት ንዑስ ክርስቲያን የሚባሉት የክርስትናን ትምህርት ገና በመማር ያሉትና ያልተጠመቁት ስለሆኑ ለመቍረብ የማይችሉ በመሆናቸው ነው ።

ፀ/ ካህኑ በከመ አንጽሕኩ ብሎ እጁን ታጥቦ ሲመለስ ንፍቅ ክህን ማኅፈዱን የሚገልጽበት ምክንያት ጌታ በተነሣ ጊዜ መግነዙ ለብቻው ሰበኑ ለብቻው ተጠቅልሎ በመቃብሩ መገኘቱን ለማስታወስ ነው /ዮሐ. 20:7/ ።



ፈ/ ዲያቆን እንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት ሲል ሠራኢው ካህን ኅብስቱን ማንሣቱ ትንሣኤውን፥ ንፍቀ ካህን ማኅፈዱን ማንሣቱ፥ በትንሣኤ መልአኩ "ወአንኮርኮራ ለይእቲ ዕብን" ያለውን ማስታወስ ነው/ ማቴ. 28:2/ ።

ፐ/ ካህኑ ኅብስቱን ከባረከ በኋላ ከ5 ቦታ የሚያንቃው /የማወጋው/ በአምስት ቀኖት /ምስማር/ መቸንከሩን ለማስታወስ ነው /ዩሐ. 19:34/

ቈ/ ደሙን በጣቱ አጥቅሶ ሥጋውን መቀባቱ መላእክት ደሙን ተቀብለው በዓለሙ የመርጨታቸው ምሳሌ ነው።

ኈ/ ኅብስተ ቁርባን ከ13 ቦታ መፈተቱ ጌታ በተሰቀለበት ዐርብ ዕለት 13ቱን ሕማማተ መስቀል መቀበሉን ለማሰብ ነው ።

ኰ/ ጽዋውን ከባረከ በኋላ የሚወዘውዘው ጌታ በጦር በተወጋ ጊዜ በመስቀሉ ላይ አካሉ መናውጡን ለማስታወስ ነው /ዮሐ. 19:34/

ጐ/ ካህኑ ሥጋውን ከፈተተ በኋላ የቁርባኑን መስቀል በ 8ቱ ማዕዘን የሚያዘዋውረውና ኋላ በየቦታው የሚመልሰው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ወደ ግራ ሄደን የነበርን እኛን ከግራ ወደ ቀኝ የመመለሱ ምሳሌ ነው /ማቴ. 25:33/ ።

ይህም ማለት የላዩን ከታች ማድረጉ አምላክ ሰው መሆኑ፥ የታቹን ከላይ ማድረጉ ሰው አምላክ መሆኑ ፥ የቀኙን ከግራ ማድረጉ ኃያል መለኮት ደካማ ሥጋን መዋሐዱ፥ የግራውን

ከቀኝ ማድረጉ ደባማ ሥጋ ኃያል መለኮትን መዋሐዱ፥ በየቦታው መመለስ ከዕርገት በኋላ አንድ ወገን ሆኖ በአምላክነት ግብር ጸንቶ ይኖራልና የዚያ ምሳሌ ነው ፡፡ "ውን ደገ ንዴተ ህላዌ ዘትካት ተመይጠ ወገብአ ኀበ ስብሐቲሁ ወክብሩ እንዲል ፡፡

ሳ/ ሠራዊት ሦስት ጊዜ መባሉ የሦስትነት፥ ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ነው ፡፡

ሚ/ ከመጋረጃ በአፍአ ሠራዊት የሚሉት ንፍቅ ቂስና ንፍቅ ዲያቆን ሕዝቡ የነቢያት፥ ከመጋረጃ ውስጥ ሠራዊት የሚሉት ሠራዒ ካህን ፥ ዲያቆን እረ ካህን የሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው ፡፡

ሯ/ "አርኅው" ሲል በር ወይም መጋረጃ መከፈተ ጌታ በገበያ ቀን በዐደባባይ የመሰቀሉ ምሳሌ ነው፡፡

ሏ/ ካህኑና ሕዝቡ እየተቀባበሉ 40 እግዚኦታ ማድረሳቸው የጌታ የግርፋቱ፥ ካህኑ 41ኛው ብቻውን የሚለው የአዳም ቀኖና ምሳሌ ነው ፡፡

ሿ/ ደሙን ሲቀበል ሁለት ጊዜ አሜን ወአሜን መባለ ደሙ ሁለት ጊዜ ከሞቱ በፊትና ከሞት በኋላ የመፍሰሱ ምሳሌ፥ ከሥጋው ጋር 3 ጊዜ መባል ለቁረሱ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ ሥጋው መቁረሱን ይተረጉማል፡፡

ቧ/ ዐስበ ዲያቆን የእስጢፋኖስ መከራ ምሳሌ ነው ዲያቆን የሚወስደው የእስጢፋኖስ ምሳ ስለሆነ ነው ፡፡

ቷ/እርገተ ስጠረድ ከመሬት የሚወደቀው ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በመንገድ ቅዱሳት አንስትን አግኝቷቸው "በሀክን" ሲላቸው ድምፁን ሰምተው ከመሬት የመውደቃቸውና የመስገዳቸው ምሳሌ ነው ፡፡

ቿ/ ድርገት ወደ ምዕራብ መወረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ለመሰቀሉ ምሳሌ ነው "እስመ ገጹ ምዕራብ መልሶ ለመሰቀሉ ምሳሌ ነው" ... 

ኗ/ ዲያቆን ከድርገት በኋላ ነአኩቶ እያለ በቅድስት መዞሩ ከጌታ ዕርገት በኋላ እስጢፋኖስ በቅድሚያ አስተምሮ ሰማዕትነት የመቀበሉ ምሳሌ ነው ፡፡

ኟ/ አንብሮእድ እንዲሁም የካህኑ ሕዝቡን በእጁ መባረክ በዐረገ ጊዜ ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ ባርኮ የማረጉ ምሳሌ ነው ፡፡

ኣ/ ከካህናት ቀጥሎ አዲስ የተጠመቁ ሕጻናት እንዲቆርቡ ተደረገበት ምክንያት ጌታ የተወለደ ዕለት በመጀመሪያ ያመሰገኑ መላእክት ናቸው ከዚያ በኋላ የእነሱን ዜና ሰምተው ኖሎት /እረኞች/ ያመሰገኑ ስለሆነ ነው /ሉቃ. 2፡13-20/ "ጸልዩ" ያለበት የሐዳፌ ነፍስ ጸሎት "ጸሎት" እስከሚለው ያለው ወደ ምዕራብ፥ ጸልዩ ከአለ በኋላ ወደ ምሥራቅ የሚጸለየው አዳምና ልጆቹ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በሲዖል ከኖሩ በኋላ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከሲዖል ወደ ገነት መመለሳቸውን ለማዘከር ነው /1ጴጥ. 3፡18-22/ ፡፡



ሟ/ ሥጋ ወደሙ ከተቀበሉ በኋላ መስገድ የተከለከለበት ምክንያት ፡-

1ኛ/ ወዙ እንዳይንጠፈጠፍ ነው ፡፡
2ኛ/ ድኅነት በሥጋው በደሙ ሳይሆን በትሩፋት ዳንን እንዳያሰኝ ነው ፡፡

## ክፍል 5

## ሠ/ ሥርዐተ ንስሐ

### 1/ የንስሐ አመሠራረት

ንስሐ የግዕዝ ቃል ነው ፤ ትርጉሙ በሠሩት ኃጢአት የመጸጸት ወደ ገቢረ ኃጢአት አለመመለስ ነው ፡፡ ስለዚህ ከልብ መመለስ በኃጢአት መጸጸትና ከኃጢአት ለመጠበቅ ቁርጥ አሳብ ማድረግ ንስሐ ይገላል ፡፡

ንስሐ ከጥንት የመጣ ምሥጢርና ሥርዓት ነው፡፡ አዳም በድሎ ንስሐ ቢገባ ተስፋው ድኅነትን አግኝቷዋል ፡፡የነነዌ ሰዎች በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተው ድነዋል /ትንቢተ ዮናስን በሙሉ አንብብ/ ፡፡

ከሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ምሳሌ ይሆናል ፡፡ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘበት ሌሊት ጌታውን አላውቅም ብሎ 3ጊዜ ከካደ በኋላ "ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ያለውን የአምላኩን ቃል አስቦ በኀሊናው ተወቅሶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ፡፡ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም ንስሐውን አይቶ ኃጢአቱን ይቅር ብሎ "በጎቼን ጠብቅ" ሲል የሐዋርያትን ሹመት ሰጠው ፤ የመንግሥተ ሰማያትን



መክፈቻ እሰጥሃለሁ ሲል በቂሣርያ የሰጠውን ተስፋም ፈጸመለት /ማቴ 26፡69-75 ፤ ማቴ. 16፡19 ፤ ዮሐ. 21፡15-17 /፡፡

### ስለ ንስሐ ጌታ የሰጠን የይቅርታ ቃል፡-

1ኛ/ "እመኒ ሰብእ ለለሰለቱ አበሰ ወሰብእ ለለሰለቱ ተጋነየ ኅድግ ሎቱ"

2ኛ/ "ለእለ ገደግሙ ኃጢአት ይትኀደግ ሎሙ ወለእለ ኢኀደግሙ ኢይትሐደግ ሎሙ" የሚለው ነው /ሉቃ. 19፡3-4 ፤ ዮሐ፣ 20፡22-23/ ፡፡

ስለዚህ ንስሐ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ አንዱ እንኳ እንዳይጠፋ የበደለውን ሁሉ ይቅር በማለት ታላቁን የምሕረት በር ንስሐን ከፈተ ይህም ምሥጢር ያለማቋረጥ እንዲሠራ ሥልጣኑን ለሐዋርያት ሰጠ፡፡

"የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሠርኸው በሰማይ የታሠረ ይሆናል ፤ በምድርም የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል " /ማቴ. 16፡19 ፤ 18፡18 / ፡፡

ክህናት የሕይወት መሰላል ወይም ድልድይ ሆነው የሕዝቡን ንስሐና ልመና ወደ እግዚአብሔር፥ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሕዝቡ የሚያደርሱ ናቸው ፤ በኃጢአት የሚሰናከል ሁሉ ንስሐ ያሥፈልገዋል፡፡

## 2/ የንስሐና የኑዛዜ ሥርዐት

ሰው በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ ኃጢአቱ ይሠረይለት ዘንድ እግዚአብሄርን በኀዘን በልቅሶ ይቅር በለኝ ማለት ከንስሐው በኋላ ኃጢአት እንደማያደርግ አሳቡን ቆርጦ በመጣል ምሕረትን መለመን ይገባል /1መቃ. 26፡5/ ሲናገርም ሲሠራ ያላፈረበትን ኃጢአት ሳይከፍል ሳይሰውር እያዘነ እየተጸጸተ ለካህን መናገር ልቡናውን ታዛቢ ምስክር እንደበቱን ከሳሽ እግዚአብሔርን ዳኛ አድርጎ ራሱን መክሰስ ነው "ኃጢአትየ ነገርኩ ወአበሳየ ኢኀባዕኩ" /መዝ 31፡4/ ።

በንስሐ እግዚአብሐየርን መፍራትና ለቃሉ መታዘዝ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን መፍራትና ለካህን ኃጢአቱን ነግሮ ሥርየት መቀበል ይገባዋል ።

የበደለ ሁሉ በቃለ ካህን የኃጢአቱን ሥርየት ያገኛል ፤ምክንያቱም እግዚአብሐየር ማንኛዬቱም ወገን ብትበድል ካህን ኃጢአቱዋን ያስተሥርይላት፤ ኃጢአቱን የተዋችሁለት ይሠረይለትም ሲል በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ለካህናት የሰጠው ሥርዓት ስለአለ ነው /ዘሌ. 4፡20 ፤ ዮሐ. 20፡22-23/ ።

የታመመ ሰው ወደ ሐኪም ሔዶ በሽታውን ሲነግረው ሐኪሙ በሽተኛው የነገረውን ሰምቶና መርምሮ ለበሽታው ተቃዋሚ ፥ ለጤናው ተስማሚ የሚሆን መድኃኒት እንዲሰጠው ሁሉ ወደ ካህን የሔደ ተነሣሒ ሲታወቀው በድፍረት ፥ ሳይታወቀው በስሕተት የሠራውን ገልጦ ሲናገር ካህኑ ቀኖና ይሰጠዋል። የሠራውን ኃጢአት የፈጸመውን በደል



ገልጦ ካልተናገረና ካልተጸጸተ በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም እንደተባለው ፍጹም ድኅነትን ሊያገኝ አይችልም ።

ካህኑ ንስሐውን ተመልክቶ በስፌሐ እድ በስቂለ አዕይንት፥ በአንቃዕድዎ ኅሊና የንስሐ ጸሎትና ኑዛዜ ከአደረገለት በኋላ ተነሣሂውን ፍትሐት ሰጥቶ /እግዚአብሔር ይፍታሕ ብሎ/ ያሰናብተዋል ።በዚህ ጊዜ ተነሣሒው ሥርየተ ኃጢአት ያገኛል።

## 3/ በንስሐና ኑዛዜ የሚገኝ ጸጋ

ንስሐ ዘማዊውን እንደ ድንግል ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ በአጠቃላይ የበደለውን እንደ አልበደለ ያደርገዋል።

በአንብዐ ንስሐ መታጠብ ፍጹም ንጹሕ ያደርጋል ። የንስሐ ጥምቀት በዕንባ መታጠብ ነውና ። ይህም ነቢዩ ፤ "ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን በዕንባዬ አጥባለሁ ፤ ምንጣፌንም በዕንባዬ አርሳለሁ" እንደአለው ነው /መዝ. 6፡6/ ።

## 4/ የንስሐ ኑዛዜ አፈጻጸም

በንስሐ የሚሰጠው ቀኖና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ለመምህረ መሠረት ይፈጸማል ተነሣሒው ኃጢአቱን ለመምህረ ንስሐው ይነግረዋል ፤ መምህረ ንስሐው የተነሣሒውን ዐቅም መዝኖ የጾም፥ የጸሎት ፥ የስግደት ፥ የምጽዋት ቅጣት ይሰጠዋል ። ለዚህም ጊዜ ይወስንለታል ። የቀኖናውን ጊዜ ከጨረሰ በኋላ



ተነሳሒው ወደ መምህረ ንስሐው ተመልሶ እንደ ትእዛዙ መፈጸሙን ይነግረዋል ።ቄሱም ፍትሐት ሰጥቶ /ናዝዞ/ ሥጋውን ደሙን አቀብሎ ከምእመናን ጋር እንዲቀላቀል ይፈቅድለታል ።

# ክፍል 6

## ረ/ ሥርዐተ ክህነት

### 1/ የክህነት አመሠራረት

ክህነት የተጀመረው በመጀመሪያው ሰው በአዳም ነው። እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ነቢይ ካህን አድርጎ ስለሾመው በኦሪት በወንጌል ሥርዓት እስኪወሰን ድረስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከት አበው ከእግዚአብሔር እየተሸሙ ትንቢትን ክህነትን ከቅዱስ መንፈስ እየተቀበሉ /እየተሸሙ/ በነቢይነታቸው ያለፈውን የሚመጣውን ሲገልጡ ሲያሥተምሩ በክህነታቸው መሥዋዕት ሲያቀርቡ በጸሎታቸው አምላካቸውን ሲጠሩና ቃል በቃል ሲነጋገሩ ኖረዋል ።

አዳም ከገነት በወጣ በማግሥቱ በሠራው ኃጢአት ተጸጽቶ እያዘነና እያለቀሰ ቸርነት ምሕረት የባሕርዩ ከሆነው አምላክ ምሕረት ለመጠየቅ የመዓዛ መሥዋዕት አቀረበ።

"ወዐጠነ አዳም ምሳለ ትንሣኤ ፀሐይ ከርቤ ወሚዓ ወሰሊክ" /ኩፋሌ 5፡1-5/ ካህን መባል በኦሪት ከመገለጹ በፊት የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ፥



የወንጌል ሥርዐተ ቍርባን መምህርና ሰባኪ የብዑዓን ሐዋርያት መሪና ፊት አውራሪ ሆኖ በቀራንዮ ሊያገለግል ታላቁ ክህን ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱና ለመሥዋዕት ከመቆሙ በፊት ቤተ መቅደሱን ሊጠብቅ ንዋያተ ቅድሳትን ፥ ጾምን ፥ ጸሎትን ተባሕትዎን ድንግልናን ከዊን ሰማዕትን ሊያዘጋጅ ከእግዚአብሔር ተመርጦ የተሸመውና የተላከው ታላቁ ካህን መልከ ጼዴቅ ነው /ዘፍ. 14፡18-23 ፤ መዝ. 109፡4/ ።

ታላቁ ካህን መልከ ጼዴቅ የወልደ እግዚአብሔር ምሳ እንደ መሆኑ መጠን ሌዋውያን ካህናት የማይተካከሉትና የማይወዳደሩት ማዕርገ ክብሩ ምዩቅ፥ ምሥጢረ ክህነቱ ረቂቅ ስለሆነ የሌዋውያን አባት አብርሃም ሌዊ ገና በወገቡ ሳለ በረከተ ገጽ /እጅ መንሻ/ አቀረበለት ፤ አሥራት አወጣለት ። መልከ ጼዴቅም ኅብስተ አኰቴቱን፥ ጽዋዐ በረከቱን ባርኮ፥ ቀድሶ በመስጠት አብርሃምን ባረከው ዕብ. 7፡1-14/ ።

ሙሴ ለአሮንና ለአልአዛር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ለመስጠቱ በፊት ክህነትን በመምህራን ቡራኬ ከመንፈስ ቅዱስ ለማግኘትና ለመሾም መሠረቱና መጀመሪያው መልከ ጼዴቅ አብርሃም የባረከበት ፥ አብርሃም ከመልከ ጼዴቅ የተባረከበት ያ ቡሩክ ሰዓት ነው /ሉቃ. 24፡50 ፤ ዮሐ. 20፡21-24 ፤ ዘሌ. 21፡10-12/ ።

ክህነት በዘመነ ኦሪት ለሌዊ ነገድ ከተሰጠ በኋላ ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ክርስቶስ ደርሱዋል ። ታላቁ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ብሉይ ኪዳን ክህናት መሥዋዕተ እንስሳን ሳይሆን መሥዋዕተ ደሙን ይዞ ራሱ መሥዋዕት፥ ራሱ ሠዋዒ ሆኖ ወደ

መቅደስ ገብቷዋል /ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ ኤፍሬም በእግሩም ሐዋርያት እንዲተኩ በእንብሮተ እድ በንፍሐት ሾሞዋቸዋል /ዮሐ. 20፡22-23 ፤ ሉቃ. 24፡50/

ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በእንብሮተ እድና በንፍሐት እያስተላለፉ እስከዛሬ ደርሱዋል /የሐ. ሥ. 6፡3-9፤ 14፡23 ፤ 1ጢሞ. 1፡3፤ 4-14 ፤ 2ጢሞ. 1፡6 ቲቶ 1፡5/ እስከ ምጽአትም ድረስ እንዲሁ እየተሰጠ ይቀጥላል ።

## 2/ የክህነት ሥልጣን

ክህነት ከፍ ያለ ሥልጣን አለው ። የማሠር የመፍታት ሌሎችንም የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የመቀደስ የማክበር የመፈጸም ችሎታና ሥልጣን ያለው ጸጋ ነው ።

በሐዲስ ኪዳን የክህነት ሥልጣን ለሁሉ አይሰጥም በሃይማኖትን ለተመረጡና ማስተማር ለሚችሉ ሰዎች ብቻ ነው። ሢመተ ክህነት አይደገምም ሹመቱ የሚሰጠው በየደረጃው አንድ ጊዜ ብቻ ነው ። ከፈረስ ይቀራል ፤ አይታደስም ፤ አይጠገንም ።

## 3/ የክህነት ተግባር

የክህነት ተግባር እግዚአብሔርንና ሰውን ማገልገል ነው ። እግዚአብሔርን ማገልገል ማለትም ካህናት መላእክትን መስለው በመዓልትና በሌሊት ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና ነው ።

ሰውን ማገልገል ማለትም ማስተማር፥ ማጥመቅ፥ ማቁረብ፥ መባረክ፥ መጠበቅ፥



መናዘዝ፥ መቀደስ፥ ማንጻት፥ ከኃጢአት መፍታት ከእግዚአብሔር ማስታረቅ፥ በሞት ለሚለዩ ጸሎት ፍትሐት ማድረግ፥ በጠቅላላ በትምህርት በትሩፋት ክርስቶስን መስሎ አብነት ሆኖ መገኘት /ማቴ. 13፡1-14 ፤ የሐ.ሥ. 6፡4 ፤ 20፡28-31 ፤ ዮሐ. 20፡21- 24 ፤ 1 ጢሞ. 4፡13 ፤ ማቴ. 16፡19 ፤ ኤፌ. 4፡11 ፤ 1ጴጥ. 5፡1-4/።

## 4/ ሢመተ ክህነት

ሢመተ ክህነት 3 ደረጃ አለው ።ይኸውም ዲቁና ቅስና ኤጲስ ቆጶስነት ነው ። ከዚህም በላይ ጳጳስ፥ ሊቀጳጳስ ፓትርያርክ አለ ። እንደየማዕረጉም ሥርዓተ ሢመትና ጸሎት አለው ። ስለዚህ ሥርዓቱ እንዴት እንደ ሆነ ከፀፃዌ ኖኅት እስከ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሕገ ቤተ ክርስቲያን የተወሰነው ሥርዓተ ሢመት በየደረጃው እንደሚከተለው ተገልጹዋል ።

### ሀ/ የፓትርያርክ /ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ ወይም የሊቀ ጳጳሳት አሹዋሹዋም ሥርዓት

ሀ/ ሊቃነ ጳጳሳት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ክርስቶስ የሾማቸው የሐዋርያት ተከታዮች ናቸው /የሐ. ሥ. 20፡28/ ።

ለ/ በአንድ ዘመን በአንድ ወምበር ሁለት ሰዎች አይሾሙም ።

ሐ/ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሲሾም ሊቃነ ጳጳሳት፥ ኤጲስ ቆጶሳት ይገኛሉ ።ይህ ሹመት ያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ አይደረግም ።



የሀልው ኤጲስ ቆጶሳት በሢመተ ሊቀ ጳጳሳ/ ለሰ[illegible] ኢይትፈጸም ዝንቱ ዘእንበለ በህላዌ ጉባኤሆሙ ለኤጲስ ቆጶሳት ወህላዌ ሚጥሮጶሊስ ዘውእቱ ጳጳስ /ፍት. መን. እን. 4፤ ረስጣ 11/ ።

መ/ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ጳጳስ፥ ጳጳስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፥ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ቄስ፥ ሳለም ከሞተም በኋላ አይፈታውም ። ቄስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፥ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ፥ ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳሳት፥ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ፓትርያርክ /ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ ሳለም ለሞተም በኋላ ይፈታዋል ። ሊቃ ጳጳሳት ያወገዘውን ቄስ ሳለ አይፈታውም ፤ ከሞት በኋላ ግን ይፈታዋል ። ወኢይደሉ እምሊቃጳጳሳት፥ ወጳጳሳት፥ ወኤጲስ ቆጶስ ከመ ይፍታሁ ዘአሠሮ ካልዑ ዘእንበለ እምድኅረ ሞቱ፥ ወሊቀ ጳጳሳት ብውህ ውእቱ እምድኅረ ተከሥተ ከመይፍታሕ ማእሠርሙ ለኩሎሙ ሰበ ርእየ ዝክተ /ሲኖዶስ 51/ ።

ሠ/ ሊቀ ጳጳሳቱ ወይም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ የታመመ እንደሆነ እስከሚድን፥ የታሠረ እንደሆነ እስከሚፈታ ይጠበቃል ፤ ሹመቱ ለሌላ አይሰጥም ፤ የማይድን ደዌ ከያዘውና ሊፈታ የማይችልበት እሥራት ከሆነ በላዩ ይሾማል ፤ አይጠበቅም /ፍት. መን. እን. 4 / ።



## ለ/ የኤጲስ ቆጶሳት ሢመተ ክህነት ሥርዐት

ሀ/ ኤጲስ ቆጶስ ኖላዊ /ጠባቂ/ ነው ፥ /ፍት. መን. እን. 5፤ ሕዝ. 34፡1-10 ፤ ዮሐ. 10፡2-16፤ 21፡15-17/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾም ነውር የሌለበት በልቡናው ከሐኬት የነቃ፥ የሚያረጋጋ፥ እንግዳ መቀበልን የሚወድ ፥ የተማረ አብዝቶ የማይጠጣ ፈጥኖ የማይማታ ብልህና አዋቂ ነው ። ወነዋ ይደሉ ከመይኩን ኤጲስ ቆጶስ ዘኢተረከበ ወስቴቱ ነውር ወዘአውሰበ አሐተ ብእሲተ ዘንቁሕ በሕሊናሁ ወእቱ ጠቢብ ወመናዝዝ ወመፍቀሬ ነግድ መምህር ዘኢያበዝኅ ስትየ ወይን ወዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘቢጥ /ፍት. መን . እን. 5፤ 1ጢሞ. ፤ ጢት ዘ፬/ ።

ሐ/ ኤጲስ ቆጶስ በጠባዩ ትሑት፥ የማይጣላ፥ ትዕግሥተኛ ሰውን የሚያስታርቅ ገንዘብ የማይወድ ለሰው የሚያዝንና የሚራራ ቤተሰቡን ሠርቶ ቀጥቶ የሚኖር ልጆቹን ሠርቶ ቀጥቶ የሚያሳድግ መክሮ አስተምሮ በንጽሕና እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው፥ ለካራምና ቁጡ ያልሆነ ከቂም በቀል ከፀመፃ የተለየ ሐዲስ አማኒ ያልሆነ እንዲሆን ታዟል /1 ጢሞ. 3፡3-7 ፤ ፍት.ነገ. እን. 5/ ።

መ/ ኤጲስ ቆጶስ ከ50 ዓመት በታች እንዳይሾም ተከልክሏል። ወዘኢኮነ ሕይወቱ ህፁፀ እም ፶ ዓመት /ፍት. ነገ. 5 ፤ ድስቅ 4/ ።

ሠ/ ኤጲስ ቆጶስ ብሉይ ሐዲስ የተማረ እንዲሆን ታዟል።

ረ/ ኤጲስቆጶሱን የሚመርጡት 30 ዘመን የሆናቸው ናቸው / ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ 28/ ።

ሰ/ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው በሚሾምበት አገር ምእመናን ምርጫና በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፈቃድ ነው /ፍት. ነገ. አን. 5/ "ለይሡየም ኤጲስ ቆጶስ በኀርየተ ኩሎሙ ሕዝበ ዚአሁ በሥምረተ መንፈስ ቅዱስ" /ፍት. ነገ. አን 5 ድስቅ 36/ "እመቦ ብእሲ ዘእምጽእዎ ከመይሰየም ኤጲስ ቆጶስ ወይኩን ዘንቱ በሥምረተ ስብአብሔሩ ኩሎሙ ወይኩን ዘንቱ ጳጳስ አው ሊቀጳጳሳት ዘይሰየም..." /ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ረስጣ (አብጥሊስ) 2/ ።

ሸ/ ካህናትና ሕዝቡ እንዲሾምላቸው ኤጲስ ቆጶስ የሚሆነውን ቆሞስ መርጠው ሲያቀርቡ ስለደግነቱና ትሩፋቱ፥ ስለንጽሕናውና ከነውር የራቀ ስለሆነ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሦስት ጊዜ እየመላለሰ ማረጋገጫ ይጠይቃቸዋል፡ ሕዝቡም አረጋግጠው የሚገባው ነው ብለው ሦስት ጊዜ መልስ ይሰጣሉ ።በሦስተኛው ሕዝቡ መልስ ሲሰጡ እጃቸውን እንሥተው ይገባዋል እያሉ ያጨበጭባሉ ።ወይም አመልጥነው አማን በአማን እያሉ ያሸበሽባሉ ። ካጨበጨቡ በኋላ ተቃውሞ ቢነሣ ያስታርቁታል እንጂ ተቀባይነት የለውም /ፍት.. ነገ. አን. 5 ፤ ረስጠብ 52/ ።

ቀ/ በሹመቱ ጊዜ ሦስት ወይም ሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ጋር አብረው ይሾማሉ አንብሮተ እድ ያደርጋሉ ። "... ወየሃልው



ለሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት ክልኤቱ አው ሠለስቱ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘ ዊስክ ሞገስ /ፍት. ነገ. አን. 5፤ ረስጣ (አብጥሊስ) 2/ ።

"ወየሃልው ከመ ይሢምዎ ኤጲስ ቆጶሳት አው ቱ" /ፍት.ነገ. አን. 5፤ ረስጣ 3 (ቀሌ) 4/ ።

በ/ ጋኔን ያደረበት ሰው ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም።
"ኢይደሉ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶስ ዘጋኔን /3 ቀሌ2/ ።

ተ/ ዕውር ደንቆሮ ሰነፍ ዝንጉ ኤጲስ ቆጶስ አይሆንም ።
"ወኢይደሉ ከመ ይኩን ዕውር ወኢጽሙም ወኢዝንጉዕ" /3ቀሌ 52 ፤ ፍት. መን. 5/ ።

ቸ/ ደግነቱ ያልታወቀ፥ በራሱ ፈቃድ ዐባለዘሩን የሰለበ፥ ቀድሞ ሳያምን ኖሮ በኋላ የተጠመቀ ኃጢአተኛ ሁኖ በኋላ ንስሐ የገባ ኤጲስ ቆጶስነት አይሾምም /ፍት. መን. 5 ፤ ረስጠጅ /3 ቀሌ. 75 ።

ኀ/ ኤጲስ ቆጶስ ከአንድ ኤጲስ ቆጶስ አይሾምም።

ወኢይደሉ ከመ ይሡየም ለክሙ እምእሐዱ ኤጲስ ቆጶስ እስመ ስምዐ ክልዔቱ አውሠለስቱ ይከውን ቀዋሚ ወለእመ ኮነ ውእቱ ኤጲስ ቆጶስ እሐዱ ዘአንበረ እዴሁ ላእሌሁ ይትፌለጥ /ፍት. መን. አን. 5 ፤ ረስጣ 58 ድስቅ 34/ ።



ነ/ አንድ ዓይንና አንካሳ ኤጲስ ቆጶስነት ከመሾም አይከለከልም ።ይኸውም አንካሳው ዞሮ የሚያጥን፥ ዓውድ የማይጥል፥ አንድ ዓይናው ቀለም የማይጥል፥ ፍታቱ የሚያደላድል ከሆነ ነው ።

"ወኢይትከላዕ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶስ ነቋር፥ ወኢሐንካስ፥ ወኢሐንካስ፥ ለእመ ኮነ ይሤኒ ዝግብር" /ፍት. መን. 5 ፤ ረስጠጅ (3 ቀሌ) አንቀጽ 72/ ።

ኘ/ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው እሑድ ቀን ነው፥ ተሿሚውን በሚገባው ወንበር ያስቀምጡታል ። ወይሡየም ኤጲስ ቆጶስ በዕለተ እሑድ /ፍት. መን. 5 ድስቅ. 37/ ።

አ/ ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ካህናቱም ሕዝቡም በሙሉ ተገኝተው እየመሰከሩለት ነው የሚሾመው ። ወኩሎሙ ሰብእ ይንበሩ በእንተ ተሰይሞቱ ሕዝብ ኒ ወካህናት እንዘ ስምጨ ይከውኑ ሎቱ /ፍት. መን. 5/ ።

ከ/ በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶሱን ሲሾሙ የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጶሳት እጃቸውን ይታጠባሉ ።ከታጠቡ በኋላ በአንብሮተ እድ ይሾሙታል ።

ወኤጲስ ቆጶሳትኒ እለ መጽኡ ከመ ያንብሩ እደዊሆሙ ዲቤሁ ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ወእምዝ ይሢምዎ /ፍት. መን. አን. 5/ ።

ኸ/ ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙት ሕዝቡ በፍርሃት ፀጥ ብለው ይቆማሉ ። ወሕዝብ ቀዊሞሙ በአርምሞ ወበፍርሃት ያንሥኡ



ወያንብሩ ኤጲስ ቆጶሳት እደዊሆሙ ዲቤሁ /ፍት.መን. 5/ ።

ወ/ ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙ ንህነ ናንብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ገብር ኅሩይ ዘእግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እያለ የቡራኬ ቃላት እየተናገሩ ነው /ፍት. መን. 5/ ።

ዐ/ ኤጲስ ቆጶሳቱ የአንብሮተ እዱን ጸሎተ ቡራኬ ከፈጸሙ በኋላ ለተሿሚው መስቀል ይሰጡታል /ፍት.መን. 5/ ።

ዘ/ ኤጲስ ቆጶሳቱ የአንብሮተ እድ በሚሾሙበት ጊዜ በመጀመሪያ የተሾመው ኤጲስ ቆጶስ ከእለ ከርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ቀጥሎ በቅድሚያ አንብሮተ እድ ያደርጋል፥ እጁን ከእጁ ላይ ይጭናል ።

ወእምድኅረ ዝንቱ ያንብር ኤጲስ ቆጶስ ቀዳማዊ እምኔሆሙ እዴሁ ዲቤሁ /ፍት. መን. አን. 5/ ።

ገ/ ከዚህ በኋላ ጸሎተ ሢመቱን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ይጸልያል፥ ሕዝቡ አሜን ይላሉ /ፍት. መን. አን. 5/ ።

የ/ ጸሎተ ሢመቱም ሲያበቃ ኤጲስ ቆጶሱ ተሹዋሚውን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በአንብሮተ እድ እጅ ይነሡታል ፤ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ያሳድርበታል ።በዚህ ጊዜ በንፍሐት መንፈስ ቅዱስን ይደልዎ፥ ይደልዎ፥ ይደልዎ ይላሉ። ካህናቱና ሕዝቡ ይደልዎ ይደልዎ ይላሉ፥ ካህናቱና ይህንንም ምስክርነት በከፍተኛ ድምፅ እያሰሙ ካህናቱና ሕዝቡ ተሹዋሚውን እጅ ይነሡታል ።

ደ/ በእንተ ሰላምን ይጸልዩለታል ፤ ከዚህ በኋላ ሊመቱን የሚያወሱ መጻሕፍት አየለዩ ያነብባሉ ፤ ዲያቆናት በሚሾመው ራስ ላይ ወንጌል ዘርግግተው ይይዛሉ ፤ጸሎተ ሊመቱ ሲፈጸም ሕዝቡ ሁሉ እጅ እየነሡ መስቀሉን ይሳለማሉ ፡፡

ጀ/ ከዚህ በኋላ ቅዳሴ ባስልዮስን መቀደስ እንዲገባ አዘዙዋል፡፡ ሥጋ ወደሙ መጀመሪያ የሚቀበለው አዲሱ ተሿሚ ነው ፡፡

ገ/ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ ጊዜ ሦስት ቀን በዓል ይከበርለታል /ፍት. መን. አን. 5/ ፡፡

ጠ/ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሦስት ሱባኤ ይጾማል ፤ የተሾመበት ጊዜ በዓል ከሆነ በዚያ ጊዜ መጾም ስለማይችል አሳልፎ በዚያው ዓመት በየሱባኤው ሦስት ሦስት ቀን ጾሞ ይጨርሳል፡፡ ወእምከመ ተሠይመ ኤጲስ ቆጶስ ይንበር ሠለስተ ሱባኤያተ በጾም ዝንቱ ለእመ ኮነ በመዋዕለ ... እምዝኒ ይፈጽም ይእተ ዓመተ በጾም በበሠለስቱ /ፍት. መን. አን. 5/ ፡፡

ጨ/ ምክንያት ከአልከለከለው በስተቀር ዕለት ዕለት ሥጋውን ደሙን ይቀበል ዘንድ መትጋት አለበት ፤ ይህም በመላ ዘመኑ ጤነኛ ሆኖ ለመኖር እንዲረዳው ነው ፡፡

ወይጽሐቅ ከመ ይትመጠው በኩሉ ዕለት ምሥጢራተ ለእመ ኢከልዖ ምክንያት ከመ ይሕየው ባቲ በኩሉ ዘመን /ግት. መን. 5 ሥርዋፅ 5/ ፡፡



ጰ/ ኤጲስ ቆጶስ የሚጸመው ሕዝቡ ሁሉ በሚጸሙበት ጊዜ ነው እንጂ ሕዝቡ በማይጸምበት ጊዜ አይደለም፡፡

ወኢይደልዎ ለኤጲስ ቆጶስ ይጹም ዘእንበለ በዕለት ዘይጸውሙ ቦቱ ኩሉ ሕዝብ እስመ ውእቱ ለእመ መጽአ ኀበ ቤተ ክርስቲያን ወአምጽአ አሐዱ ምንተኒ ኀበ ቤተ ክርስቲያን አይትፈቅድ ከመ ይብላዕ ምስለ ማኅበር /1 ቀሌ. አን. 37/ ፡፡

ደ/ በማስተማር ጊዜ መጻሕፍትን የሚያነብብ፥ ኦሪትን፥ ነቢያትን ፥ ወንጌልን ፥ መጻሕፍተ ሊቃውንትን፥ ምዕራፍን፥ ቁጥሩን፥ አንቀጹን እየለየ የሚተረጉም፥ ዘወትር የሚያስተምር፥ ንቁሕ፥ ትጉህ እንዲሆን ታዝዙዋል /ፍት. መን. አን. 5/ ፡፡

ፀ/ ኤጲስ ቆጶስ ከሃይማኖት ወደ ማይመስሉ ወደ አሕዛብ በዓል እንዳይሔድና እንዳያከብር ተከልክሉዋል ፡፡ ወኢይሑር ኀበ በዓላተ አሕዛብ /ፍት. መን. አን. 5/ ፡፡

ፈ/ ኤጲስ ቆጶስ ሕዝቡን በምሳሌነት ለማስተማር ማንንም የሚወድ፥ የሁሉ ወዳጅ፥ ቂም በቀል የማይዝ፥ ጎዳኔ በቀል ፥ ልበ ሰፊ ነገር አላፊ መሆን አለበት ፡፡ከማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ ካልሆነው የሰይጣን ሥራ ከሆነው ነገር ሁሉ መጠበቅ እዳለበት ታዟል ፡፡ ነቢዩ ሆሴዕ መምህሩ ደግ ከሆነ ሕዝቡም እንደርሱ ደጋግ ይሆናሉ ብሎ እንደተናገረ ኤጲስ ቆጶሱ ደግ ከሆነ ብዙ ሰዎችን ወደሱ መሳብ ስለሚችል ነው ፡፡



ወይኩን ፍቁረ ለኩሉ ወለኩሉ ግብር ሠናይ ዘሀሎ ላእለ ሰብእ ለይርባሃ ለነፍሱ እስመ ኖላዊ ለእመ ርሑቀ እምዓመፃ ይሰሕቦሙ ለአርዳኢሁ ... በከመ ይቤ ሖሴዕ ነቢይ እስመ በከመ ይከውን ካህን ከማሁ ካዕበ ሕዝብኒ /ፍት. ነገ. አን. 5 ፤ ድስቅ 8፤ ሆሴዕ 4፡9/ ፡፡

ፐ/ ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ዘወትር ያገለግላል ፤ በመዓልትም በሌሊትም ስለራሱና ስለሕዝቡ፥ ስለ ሀገሩና ስለዓለሙ ይጸልይ ዘንድ ታዟል ፤ በቤተ ክርስቲያን ብቻውን ይኖራል ማለት ቤቱን ከቤተ ክርስቲያን አጠገብ ያደርጋል ፡፡ ካስፈለገው በጸሎተ ማኅበር የሚረዱት አንድ ሰው፥ ሁለት ሰው በቤቱ ለማኖር ይችላል ፡፡

ወለእመ ኮነ ሎቱ ዘያሠምሮ ለነቢር ምስሌሁ እመ አኮ አሐዱ አው ክልዔቱ ወውእቶሙ አሐቲ ነፍስ ምስሌሁ ይግበር በዘይትራድእዎ በእንተ ዘይደሉ /ፍት. ነገ. አን. 5/ ፡፡

ቈ/ ኤጲስ ቆጶስ ቀሳውስትን ይበርካል ፤ እሱ ግን በቀሳውስት አይባረክም ኤጲስ ቆጶስ ይባርክ ወኢይባርኩ ኪያሁ /ፍት. ነገ. 5 ረስጣ (ቀሌ) 21/ ፡፡

ኈ/ ኤጲስ ቆጶስ ከቀሳውስት እስከ ዓፃዌ ኆኅት ያለውን ሹመት ይሾማል ፤ ነገር ግን ሳይመረምር፥ ሳይፈትን ማንንም ክህነት እንዳይሾም ተከልክሏል፡፡ወኢታፍጥን አንብሮ



እደ..ከ ላእለ አሐዱ.ሂ ወኢትሳተፍ በዝንቱ ኃጢአተ ካልዕከ /1ጢሞ. 5፡22 ፤ ፍት. ነገ. አን. 5 ክፍል 4/ ፡፡

ኰ/ ከኤጲስ ቆጶስ በስተቀር መሻር የሚገባውን ካህን ይሽራል /ፍት. ነገ. አን. 5 ክፍል 4/ እግዚአብሔር እንደሾመው ኖላዊነት በእሱ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም ኃጢአት ስለሚጠየቅ ተግቶ ማስተማርና ሕዝቡን ከኃጢአት መጠበቅ እንዳለበት ታዟል ፡፡

አንተሰ ዖርከ ዖረ ከቡደ ጽሑፍ ከመ እግዚአብሔር ይቤሉ ለሙሴ አንተ ወአሮን ትፀውሩ አበሳሆሙ ለሕዝብ...ወሶበ መጽአ ኀቤከ ዘሀለወ ቦቱ ዓቢይ አበሳ ኢትትሀየይ ኪያሁ ይቤ ሕዝቅኤል ነቢይ በእንተ ኤጲስ ቆጶስ ዘይት-ሄየይ እንበይነ ሕዝቡ አሌ ሎሙ ለኖሎተ እሥራኤል እለ ኀደጉ አባግኢሆሙ ዘይርዕዩ አባግዐ ወአንትሙ ለሀሊብ ትሰትይዎ ወለፀምር ዘትለብስዎ ወለመግዝዕኒ ስቡሐ ዘትጠብህዎ ወአባግዕየሰ ኢትርዕዩ ... /ሕዝ. 34፡1-19 ፤ ፍት. ነገ. አን. 5/ ፡፡

ኀ/ ኤጲስ ቆጶስ ስሙ በጸሎት ላይ ይጠራል ፤ በቅዳሴም ይነሣል /ፍት. ነገ፣ 5 ክፍል 4/

ኊ/ ኤጲስ ቆጶስ ሥጋውን ደሙን ከኤጶስ ቆጶሳት እንጂ ከቀሳውስት አይቀበልም /ፍት. ነገ. 5 ክፍል 4/

ሟ/ በካህናት መካከል እኔ በላይ፥ እኔ በላይ ልቁም፥ ልቀመጥ በማለት ጠብ ክርክር እንዳይሆን፥ ካህናትም በማዕረግ ከሕዝበ ጋር አንድ እንዳይሆኑ፥ ሊቃነ ካህናት ከተራ ካህናት ጋር እኩል እንዳይሆኑ የካህናቱን ማዕረግና መቆሚያቸውን ማጠትና ጽፎ መያዝ እንደሚገባው ታዟል "ወይደልዎ ከመ ይጽሐፍ ወያእምር ኩሎ ማዕርጋተ ካህናት ወምሥርዓታቲሆሙ ከመ ኢይኩን ማእከሌሆሙ ጋዕዝ በዝንቱ ግብር ወከመ ኢይደመሩ ሰብአ ቤተ ክርስቲያን እንተ ሐዋርያት ምስለ ሕዝባውያን ወከመ ኢይኩኑ ምስለ ሊቃነ ካህናት እንተ ሐዋርያት ምስለ ሕዝባውያን በመዓርግ በአምሳሊሆሙ /የኒቅያ ሲኖዶስ አን 67/ ::

ሯ/ ኤጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ከተማና ገጠር ትቶ በሌላ ሀገር እንዲቀመጥ አልተፈቀደም:: "ወኢይደልዎ ለኤጲስ ቆጶስ ከመይኅድግ መንበሮ ወሀገሮ ወይሑር ኀበ ካልዕ ሀገር" /2ቀሌ 11/ ::

ሷ/ ኤጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ለቆ ወደ ሌላ ሀገር መዛወር እንደሌለበት ባል ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት የማይገባውን ያህል አይገባውም ተብሎ ታዟል "ወኢይሑር ኤጲስ ቆጶስ ኀበ ካልዕ ሀገር እምነ ሀገሩ ዘኮነ ላእሌሁ ወተሠይመ ኤጲስ ቆጶስ በእንተ ራሕበብሔር ወናዕስ ዚአሃወ ውህደተ ሰብእ ወበረከታቲሃ ወዝንቱስ ይትሜሰል አምሳለ እለ አውሰቡ ብእሲተ እምነ ሕዝባውያን ለእመ ተአቅፈ ብእሲ በብእሲቱ ዘእንበለ በምክንያተ ተአቅፈ ብእሲ በብእሲቱ ዘእንበለ በምክንያተ ዝሙት ለእመ ፈቀደ ወልጦታ በዘትፌኑ እምኔሃ ወእቱ መዓስብ ፈድፋደ ወክማሁ



ኤጲስ ቆጶሳትኒ ወካህናት አምሳለ የሐሥሡ ፈድፋደ ዘይኄይስ አምሀገሮሙ /ጉባኤ ኒቅያ 77/ ::

ሿ/ ኤጲስ ቆጶስ ቢያጠፋ ያሳመኑ ሰዎች ምስክርነት ወይም የአንድ ኤጲስ ቆጶስ ምስክርነት አይሰማበትም "ኢይትወከፋ ስምዐ ሐራጥቃ ዘው እቶሙ አላውያን ላዕለ ኤጲስ ቆጶስ ወኢይትወከፋ ላዕሌሁ ስምዐ አሐዱ ኤጲስ ቆጶስ" /3ቀሌ. አን. 70፣ 2ቀሌ. 12/ ::

## ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት /ሲኖዶስ/

ሀ/ ኤጲስ ቆጶሳት በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባሉ::"ወይኩን ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት ክልዔተ ጊዜ በበዓመት" /ፍት. መን. አን. 5 ክፍል 5 ፤ ረስጠብ 27፤ ረስጠጅ 28፤ ጸክ 28/ ::

ለ/ የመጀመሪያው ጉባኤ በበዓለ ፶ በ4ኛው ሰባኤ በአራተኛው ቀን ይደረጋል ፤ ይኸውም ርክበ ካህናት በሚውልበት ዕለት ማለት ነው ::

ሁለተኛው ጉባኤ ጥቅምት በባተ በ12ኛው ቀን ይደረጋል ፤ ይህም ዕለት ዕለት ዕረፍቱ ለማቱምስ ወንጌሳዊ ነው::

"ወጊዜ ቀዳሚት ጉባኤ በራብዕ ሰባኤ እምዖምሳ፥ ወዳግሚትኒ እመ ፲ወ፪ ለጥቅምት /ፍት. መን. 5 ክፍል 5/ ::



"ይትጋብኡ ኤጲስ ቆጶሳት ዘኩሉ መካናት ኀበ ጳጳሶሙ. አው ኀበ ሊቀ ጳጳሳቲሆሙ ክልዔተ ጊዜ በኩሉ ዓመታት" /ፍት. መን. አን. 5፣ ኒቅያ 9፤ 45/ ::

ሐ/ በጉባኤው መካከል አንድ መንበር ተደርጎ በላዩ ላይ ወንጌል ይቀመጣል ፤ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በፊት ለፊት ይቀመጣል ፤ በር ይዘጋና ኤጲስ ቆጶሳት ተነሥተው የማኅበር ጸሎት ያደርጋሉ፤ ጸሎቱ ሲያልቅ ይቀመጣሉ፥ ከዚያ በኋላ ስለሃይማኖት መጽናት፥ ስለ በጎ ምግባር መስፋፋት፥ ስለ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን መቃናት፥ በጠቅላላው ስለ መንፈሳዊ ሕግና ፍትሕ ተነጋግረው ውሳኔ ይሰጣሉ ::

"ወያንብሩ ማዕከለ ምርፋቆሙ አሐደ መንበረ ወያንብርዎ ዲቤሁ ለወንጌል ቅዱስ ወይንበር ሊቀ ጳጳሳት በቅድሜሆሙ ወይዕፅው አናቅፀ ወይት ነሥኡ ኀቡረ ወይጸልዩ ወይግብኡ ኀበ ምርፋቆሙ ወይሕትቱ በእንተ ግብር ዘተጋብኡ በእንቲአሁ በኅቡዕ" /ፍት.መን. 5 ክፍል 5/

## ሐ/ የሚመተ ቀሳውስት ሥርዐት

### 1/ ለቅስና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ/ ለቅስና የሚመረጥ ዲያቆን ነውርና ነቀፋ የሌለበት፥ አንዲት ድንግል ሴት ያገባ፥ ደጎች ልጆች ያሉት፥ ቂመኛ ያልሆነ፥ አብዝቶ የማይጠጣ፥ እጁን ለመማታት እንደበቱን ለመገዘት የማያፈጥን፥ ገንዘብ የማይወድ፥



እንግዳ የሚቀበል፥ በጎ ሥራን የሚያፈቅር፥ ከኃጢአት የነፃ፥ ደግና ቸር የሆነ ሰውነቱን ከፍትወት የጌታ ወንጌልን በማስተማር ምእመናንን የሚረዳ፥ እውነተኛ ትምህርት በማስተማር ሰውን ማጽናናት የሚቻለው፥ ከደው ሊያስከዱ የሚተናኮሉትን የሚከራከራቸው መሆን እንዳለበት ተሠርቷል /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 1 ዘሌ. 21፡7-16 /::

ለ/ ሠላሳ ዓመት ያልሞላው እንዳይሾም ተከልክሏል::

"ኢይሠየም ቀሲስ ዘእንበለ በ፴ ዓመት /ፍት. መን. 6 ቀጠግ. 11/

ሐ/ ብሉያትን ሐዲሳትን ያልተማረ፥ ይልቁኑም አራቱን ወንጌል ያላወቀ ቅስና እንዳይሾም ተከልክሏል::

"ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲስ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት አምላካውያት ሠናያት" /ፍት. መን. አን. 6 በስ. 89/

መ/ ለቅስና መብቃቱ ያልተመሰከረለት ቅስና አይሾምም ::

"ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲስ ዘኢተንእደ በስምዐ ሐምስቱ ዕደው" /ፍት. መን. አንቀጽ 6 ፤ በስ. 47/

## 2/ ሢመተ ቅስና

ሀ/ ኤጲስ ቆጶስ በአንብሮተ እድ ይሾመዋል ፤ ቀሳውስት ቆመው ይዳስሱታል ፤ ይጸልዩለታል ።ቄስ፥ ዲያቆን፥ ንፍቀ ዲያቆንና ከዚያ በታች ያሉት የሚሾሙት በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው ፥ ኤጲስ ቆጶሱ እነዚህን ሲሾም የማዕረጋቸውንና የስርዓተ ክህነታቸውን ደረጃ ጠብቆ በሕዝብ ፊት ጸሎተ ሲመቱን አድርሶ ይሾማቸዋል ።

ወለእመ ፈቀደ ኤጲስ ቆጶስ ከመይሢም ቀሲስ ያንብር እዴሁ ላእለ ርእሱ ወቀሳውስትኒ ኵሎሙ ይግሥሥዎ ቀዊሞሙ ወይጸልዩ ላእሌሁ /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 2 ረስጣ 22፡54/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድ ቄስና ዲያቆን አይሾምም ።

ወኢይሠየም ቀሲስ አው ዲያቆን ዘእንበለ በምክረ ኤጲስ ቆጶስ ዘውእቶሙ ታሕተ ሥልጣኑ ወይሢም ኤጲስ ቆጶስ ባሕቲቱ እስመ ሳልሣይ ማእርጊሁ /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 2 በሴ 10 ረስጣ 2/ ።

## 3/ የቀሳውስት ተግባርና ሥልጣን

ሀ/ ቄስ መምህር ነው ፤ መምህርም እንደመሆኑ የቀናች ሃይማኖትን ያስተምራል ።እስመ ቀሲስ በአማሳለ መምህር ። ወይኩኑ ቀሳውስት በንቤክሙ መምህራነ ለአእምሮተ እግዚአብሔር /ፍት. መን. አን. 6 ድስቅ 27/ ።



ለ/ ቄስ ሥራው ማስተማር ማጥመቅ ቅድሶ ማቁረብ መባረክ ማሠርና መፍታት መናዘዝ ነው /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 3/ ።

ሐ/ ቄስ በአንብሮተ እድ ሕዝቡን ይባርካል።

"ወይባርክ ወኢይትባረክ እምዘ ውእቱ ይንእስ" /ፍት. መን. አን. 6 ረስጣ 58/

መ/ ቄስ ሥልጣነ ክህነት አይሾምም ፤ አይሽርም። /ፍት. መን. 6 ክፍል 3/

## 4/ ትእዛዝ ቀሳውስት

ሀ/ ቄስ ምእመናንን መጠበቅና ሲታመሙ መጠየቅ፥ በትምህርት ማጽናት እንደሚገባው ታዙዋል። እውነተኛ ፍርድ መፍረድ ይገባዋል /ፍት. መን. 6 ክፍል 4/ ።

ለ/ በመሠዊያው ቀኝ የሚቆሙ ቀሳውስት ካህናቱን ያስተናብራሉ ፤ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉትን በየተራቸው እንዲቀበሉ ይቈጣጠራሉ።"ወቀሳውስት እለ ውስተ የማን ያስተሐምሙ ለረድኤት በውስተ ምሥዋዕ ከመ ያክብርዎ ለዘይደልዎ ክብር ወይመንንዎ ለዘይደልዎ ምናኔ ዋሳውስትስ እለ ውስተ ጸጋም ያስተሐምሙ በእንተ ጉባኤ ከመ ይኩኑ ኅዱዓነ" /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 4/ ።

ሐ/ ቀሳውስት ሐዋርያት ከሠሩት ሥርዓት ውጭ ትእዛዝ በማክበድ ሕዝቡን እንዳያስጨንቁ



ታዙዋል። "ወኢይጠስክ አሐዱ እምቀሳውስት ምንተኒ ክበደ ውጹእ እምቀኖና አበዊነ ሐዋርያት /ፍት. መን. 6 በስ 51/ ።

መ/ ቄስ ታሞ በሚመረመርበት፥ በሚታከምበት ጊዜ ከአልሆነ በስተቀር በማንም ጊዜ ፈጽሞ ዕርቃኑን ሊጥልና ሊጋለጥ አይገባውም ።

"ወኢይትዓረቅ ቀሲስ ግሙራ ቅድመ መኑሂ እምስብእ ዘእንበለ በጊዜ ዐጸባ" /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 4 በስ 53/ ።

ሠ/ ቀሳውስተ ከኤጲስ ቆጶሱ ዘንድ በየዓመቱ 3 ጊዜ እንዲሰበሰቡ ታዙዋል ።

"ወይትጋብኡ ቀሳውስት ኀበ ኤጲስ ቆጶሳቲ ሆሙ ሠለስተ ጊዜያተ በበዓመት /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 4 ኒቅያ 59/ ።

ረ/ ካህናት የራስ ጠጉራቸውን ማሳደግና ማኅፈር አይገባቸውም ።

## 5/ ቀሳውስት ከሹመት የሚሻሩበት ሥርዐት

ሀ/ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሊጠብቀው የታዘዘውን የማይጠብቅ፥ እንዳይሠራው የተከለከለውን የሚሠራ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሕዝቡን የማያስተምርና የማይመራ ቄስ ቢኖር ከክህነቱ ይሻራል /ፍት.መን. አን. 6 ክፍል 5/ ።

ለ/ ሁለት ጊዜ የተሾመ ሁለት ጊዜ ያገባ፥ ወይም ሁለት ሚስት ያለው ሕዝቡን የሚያስተምር፥



የተቸገሩትን ካህናት የማይረዳ፥ ጉቦ ሰጥቶ የተሾመ፥ የኃጢአተኛውን ንስሐ የማይቀበል፥ በሐሰት የሚመሰክር፥ ሰውን የሚያጣላ፥ የሚኮራ፥ የከፋትን ሥራ የሚሠራ፥ የሚሰክር፥ ኮከብ የሚቆጥር፥ አራጣ /ወለድ/ የሚቀበል፥ በሐሰት የሚምል፥ የጠንቋዮችን ነገር እውነት ነው ብሎ የሚቀበል፥ ከሴሰኛ ሴት የደረሰ፥ ሥር የማሰ፥ ቅጠል የበጠሰ፥ ሰውን የሚማታ፥ ከመናፍቃን የተጠመቀ፥ የሰረቀ፥ የመናፍቃንን ቁርባን የተቀበለ፥ አብሮአቸው የጸለየ፥ ሥር የማሰ፥ ቅጠል የበጠሰ፥ ሰውን የሚማታ፥ ዐባለ ዘሩን የሰለበ፥ ሲሰስን፥ በሐሰት ሲምል የተገኘ፥ በገበያ መካከል የሚበላ፥ የአይሁድን ትራፊ የሚበላ ፥ከአይሁድ ምኩራብ፥ ከዐላውያን ቤተ ክርስቲያን የሚበላ፥ የአይሁድን ጾም የሚጾም፥ በዓላቸውን የሚያከብር፥ የበዓላቸውን እጅ መንሻ የሚቀበል፥ ሃይማኖታቸውን ወደለወጡ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እጅ መንሻ የሚወስድ ከተወገዘ ሰው ጋር የተነጋገረ፥ አብሮ የጸለየ፥ የኤጲስ ቆጶሱን ደብዳቤ ሳይዝ ሩቅ አገር የሄደ፥ በአገልግሎት ምክንያት ሚስቱን የተለየና የፈታ፥ እመነኩሳለሁ ተባሕትዎ እይዛለሁ ብሎ ሚስቱን የተወ፥ ያስናበተ ካህን ከሹመቱ ይሻራል /ፍት. ነገ. አን. 6 ክፍ. 5 ፤ 2ቀሌ 3 ፤ 3ቀሌ 5/ ።

ሐ/ ቄስም ሆነ ዲያቆን ከሹመቱ በኃጢአት ከተሻረ በኋላ ደፍሮ ለአገልግሎት ቢገባ ከቤተ ክርስቲያን ተወግዞ ከምእመናን ይለያል ። እያወቁ በዚህ

ድፍረቱ የተባበሩት ሁሉ ከምእመናን ይለያሉ:: /ፍት. ነገ. 6 ፥ ረስጠብ (2ቀሌ) 19 ፥ ጸክ /

መ/ ቄስ ወይም ዲያቆን በሀገሩ የመሾመውን ኤጲስ ቆጰስ ንቆ አቃሎ ለብቻው ቤተ ክርስቲያን ከሠራ ኤጲስ ቆጰሱ እስከ ሦስት ጊዜ ጠርቶት ካልመጣ እሱና የመሳሰሉት ከሹመታቸው ይሽራሉ :: /ፍት. መን. 6፥ ረስጠብ (2 ቀሌ) 22/ ::

ሠ/ ቄስ ያለበትን ቤተ ክርስቲያን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ከሄደ፥ እንዲመለስ ተነግሮት ካልተመለሰ ከሹመቱ ይሻራል /ፍት. ነገ. 6 ፥ ረስጠብ (1ቀሌ) 14 ፥ ኒቅያ 4:4/ ::

ረ/ ቄስ በቁጣ ወይም በማናቸውም ምክንያት ምእመናንን ሥጋ ወደሙ ከከለከለ ከሥልጣኑ ይሻራል /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 5 ኒቅያ 28/ ::

ሰ/ ቀሳውስትና ዲያቆናት በሥጋዊ ነገር ዋስ፥ ተያዥ፥ ምስክር አይሆኑም ይህን ያደረገ ከሹመቱ ይሻራል /ፍት. መን. 6 ክፍል 5 ኒቅያ 28/::

## መ/ የሢመተ ዲያቆናት ሥርዓት

### 1/ ለዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ/ ዲያቆናት ጭምቶች፥ ትዕግሥተኞች፥ ግብረ ገብነት ያላቸውና የሚታዘዙ ፥ ሁለት ቃል የማይናገሩ ማለት አንድ ጊዜ እውነት አንድ ጊዜ



ሐሰት የማይናገሩ፥ አብዝተው ወይን የማይጠጡ፥ የማይገባ ትርፍ ገንዘብን መቀበል የማይሹ፥ ንጹሕ በሆነ ልቡና ሃይማኖትን የተረዱ፥ ጋብቻ ያልደገሙ ፥ ልጆቻቸውን ቤተ ሰቦቻቸውን ቀጥተው ያሳደጉ መሆን ይገባቸዋል :: በዚህ ሁሉ የተፈተኑና ነውር የሌለባቸው ሆነው ሲገኙ ዲቁና ይሾማሉ /1ጢሞ. 3:8-12 ፥ ፍት. መን. 7 ክፍል ፥ 1፥ ጢት. 4/ ::

ለ/ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ለመዓርገ ዲቁና መብቃታቸው ተመስክሮላቸው እንዲሾሙ ታዙዋል /ፍት. ነገ. 7 ፥ ረስጣ 17/ ::

ሐ/ ከዚህ ጋር ለሰው የሚራሩ፥ የማያዝኑ፥ የሚያንጎራጉሩ፥ ከቂም በቀል የራቁ፥ ቁጡዎች ብስጩዎች ያልሆኑ፥ የማያዳሉ፥ ለመማርና ለማስተማር የተጉ እንዲሆኑ ታዝዙዋል /ፍት. መን. አን. 6 ክፍል 1/ ::

### 2/ ሢመተ ዲቁና

ሀ/ ዲያቆን በአንብሮተ እድ ይሾማል::
"ሶበ ትሠይሞ ለዲያቆን አንብር እዴከ ላዕሌሁ ወጸሊ" /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 2 ረስጣ 54 ቀጠግ 54/ ::

ለ/ ዲያቆናት ሲሾሙ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከኤጲስ ቆጰሱ ጋር ሆነው አብረው ይጸልያሉ :: አንብሮተ እድ የሚያደርግለት ግን ኤጲስ ቆጰሱ ብቻ ነው ::



"ቀሳውስት ኩሎሙ ወዲያቆናትኒ እንዘ ይቀውሙ ይጸልዩ" /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 2 ፥ ረስጣ 54 ቀጠግ 14/ ::

ሐ/ "ዲያቆን 25 ዓመት ሳይሞላው አይሾምም" ይላል፥ ይሁን እንጂ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ዕድሜ በታችም ያለ ቢሆን ይሾማል /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 2 ፥ ቀጠግ 11/ ::

መ/ የዲያቆናቱ ቁጥር በቤተ ክርስቲያኑ ስበካ ስፋትና ጥበት ይወሰናል /ፍት. መን. አን. 7 ፥ ቀጠግ 14 ኒቅያ 67/ ::

### 3/ የዲያቆናት ሕይወትና ሥርዐት

ሀ/ ዲያቆናት እንደ ኤጲስ ቆጰስ፥ እንደ ቄስ ያለ ነውር ያለ ነቀፋ መኖር አለባቸው :: "ወይኩኑ ካዕበ ዲያቆናት ዘእንበለ ነውር በአምሳለ ኤጲስ ቆጰስ ወይኩኑ ፍጹማነ በክህነቶሙ ለቤተ ክርስቲያን በዘይከሉ ገቢረ ዘእንበለ ሐፍረት" /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3 ስድቅ 37/ ::

ለ/ ዲያቆናት በቦታው ሁሉ በመዓልትም በሌሊትም በጎ ሥራን የሚሠሩ መሆን ይገባቸዋል :: ከኃጢአት ንጽሕ ሆኖ መልካም አገልግሎትን የሚያገለግል ዲያቆን ይረባል፥ ይጠቀማል፥ በጎ ዕድል ፈንታን ያገኛል /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 4 ረስጣ 18/ ::

ሐ/ ዲያቆን የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደ መሆኑ መጠን ለኤጲስ ቆጰሱና ለቄሱ ይላላካል ::



"ወዲያቆንሰ ከመ ዘይትለአክ ለእግዚአብሔር ይትለአክ ለኤጲስ ቆጰስ ወለ ቀሳውስት በኩሉ ግብር /ፍት. መን አን. 7 በደ. 5/ ::

መ/ ዲያቆን ሕሙማንን በመጎብኘት የችግረኞችን ጉዳይ ወደ ቄሱ ወደ ኤጲስ ቆጰሱ በማቅረብ ለችግረኞች ምጽዋት የሚሰጡትን ምእመናንን ሁሉ በማስተባበርና በመላላክ እንዲያገለግል ታዝዞዋል /ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3/ ::

ሠ/ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ዲያቆናት ወንጌል ያነብባሉ ፥ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን አያነብቡም ::

"ወይንብብ ወንጌል እመሂ ዲያቆን ወእመሂ ቀሲስ" /ዲድስቅልያ 12 ፍት. መን. አን. 7 ክፍል 3/ ::

ረ/ ዲያቆን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ሕዝቡ ሥርዓት ይዘው እንዲቆሙና እንዲጸልዩ፥ እንዳያንቀላፉና እንዳይተኙ ፥ እንዳይስቁና እንዳይሳለቁ ይቆጣተራል /ፍት. መን. አን. 12 ድስቅ 12/ ::

ሰ/ ሥጋውን ደሙን በማቀበል ጊዜ ሥርዓት ቄሱ ሲያቀብል ዲያቆን ደሙን ለሕዝቡ ያቀብላል :: /ፍት. መን. አን. 12 ድስቅ 12/ ::

ሸ/ ቆሞሱና ሊቀ ዲያቆናቱ ለኤጲስ ቆጰሱ እንደ ሁለት እጆችና እንደ ሁለት ክንፎች ሆነው ሹመት በሚሰጥበት ጊዜ በቀኙና በግራው ይቆማሉ ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔድ አብረው ይሔዳሉ ፥

ወደ ሌላም ቦታ ሲሔድ አይለዩም ። ሊቀ ዲያቆናት በተኘ ይቆማል፥ ሌሎች ግን በግራው ይቆማሉ ።

"ወኮርኤቢስኒ ይኩን በማዕርግ ከመ ክልዔ እደዊሁ ወክልዔ ክነፊሁ ለኤጲስ ቆጶስ ወሶበ የሐውር ኀበ ቤተ ክርስቲያን አውኀበ ካልዕ ይደሉ ከመይኩን ሊቀ ዲያቆን በየማኑ ወካልዓን በፀጋሙ" /ፍት. መን. አን. 7 ኒቅያ 62/ ።

## 4/ ዲያቆን ከማዕርጉ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ/ ጉቦ ሰጥቶ፥ በጉልበት አስገድዶና አስፈራርቶ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ ተንኮል የተሾመ፥ ወይም ሁለት ጊዜ የተሾመ ።

ለ/ ሁለት ሴት ያገባ፥ ወይም በተሾመ ጊዜ ከሴት ርቄ ንጽሕ ጠብቄ እኖራለሁ ብሎ ተሥሎ ከተሾመ በኋላ ስዕለቱን አፍርሶ፥ ሚስት ያገባ፥ ወይም ከዘማዊት ሴት የደረሰ፥ ወይም ተደብቆ ተክሊል ያደረሰ፥ ወይም እመነኩሳለሁ ብሎ ሚስቱን የፈታ ።

ሐ/ ዘወትር የሚሰክር፥ በክፉ ሥራ ጸንቶ የሚኖር፥ በሐሰት የሚመሰክር ።

መ/ አራጣ የሚቀበል ፥ ነጋዴ የሆነ

ሠ/ ባልጀራውን የሚያማ

ረ/ በሰው የሚታበይ፥ ኃይልን የሚያሳይ፥ ሰውን የሚመታ፥ ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድለት የመነኮሰ፥



ኤጲስ ቆጶሱን የናቀና ያቃለለ፥ ኤጲስ ቆጶሱ ጠርቶት አልመጣም ብሎ የቀረ፥ ከደማ ያልነጻችውን ሴት ወደ ቤተ ክርስቲያን ያስገባ፥ ስጋውን ደሙን ያሰጠ፥ ከተሻረ በኋላ የክህነት ሥራ የሚሠራ፥ ለብቻው ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሠራ ።

ሰ/ ቤተ ክርስቲያን ትቶ ከሔደ በኋላ የተመለሰ፥ ከመናፍቃን የተጠመቀ፥ ቁርባናቸውን የተቀበለ፥ ከመናፍቃን ጋር የጸለየ፥ ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የሔደ፥ ወታደር የሆነ ከዲቁናው መዓርግ ይሻራል /ፍት. መን. አን. 7 ፤ ክፍል 5/ ።

## ሠ/ የንፍቀ ዲያቆናት ሢመት ሥርዓት

### 1/ ለንፍቀ ዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ/ ነገር የማያበዛ፥ የማይሰክር፥ ዋዛ ፈዛዛ የማይናገር፥ በጎ አኑዋኑዋር ያለው ፥ በጎ ነገርን የሚወድ፥ ታዛዥ የሆነ።

ለ/ የሃይማኖት ትምህርት ወደሚሰጥበት ጉባኤ የሚሔድ ።

ሐ/ ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ ለመኖሩ የተመሰከረለት ንፍቀ ዲቁና ይሾማል /ፍት. መን. አን. 8 ፤ ረስጣ 15/ ።



### 2/ ሥርዐተ ሢመት ንፍቀ ዲያቆናት

ሀ/ ንፍቀ ዲያቆን ሚስት ያላገባ ከሆነ ከሴት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ እንደኖረ ከአልተመሰከረለት አይሾምም" /ፍት. አን. 8/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስ ንፍቀ ዲያቆኑን ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም ፤ በቃል ብቻ ንፍቀ ዲያቆን ብሎ ይሾመዋል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 2 ፤ ረስጣ 27/ ።

### 3/ የንፍቀ ዲያቆናት ሥራ

ሀ/ ንፍቀ ዲያቆናት ዲያቆናትን ይረዳሉ "ንፍቀ ዲያቆናት ከመ እንተ ረዳእያን" /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/ ።

ለ/ ንፍቀ ዲያቆናት በዲያቆናት ቦታ ገብተው በዲቁና መዓርግ ማገልገል፥ ንዋየ ቅድሳት መንካት፥ የዲያቆናትን ልብስ ተክህኖ መልበስ አይችሉም ። /ፍት. መን. አን. 8 ጳክ. 45፣ 46፣ 47፣ 67፣ 21፣ 22፣ 23፣ 43/።

ሐ/ ንፍቀ ዲያቆን በመቅደሱ በር ከውጭ ይቆማል፤ ከዚያ አይለይም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/ ።

መ/ ንፍቀ ዲያቆን ደሙን አያቀብልም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ጳክ. 39/ ።



### 4/ ንፍቀ ዲያቆን የሚሻርበት ምክንያት

ንፍቀ ዲያቆን ከስረተ አንድ ዓመት ከሹመቱና ከሥራው ይታገዳል ከዓመት በኋላ ወደ ሥራው ይመለሳል ወደ ዲቁና ማዕርግ አይደርስም ፤ እስከ ዕለተ ሞቱ በንፍቀ ዲቁና ማዕርግ ይኖራል /ፍት. መን. አን 8 ክፍል 4 በስ. 48/

## ረ/ የአናጉንስጢስ ሢመት ሥርዐት

### 1/ ለአናጉንስጢስ ሢመት የሚያበቃ ሁኔታ

አናጉንስጢስ ማለት አንባቢ ማለት ነው። በችሎታው በበጎ ጠባዩ የታወቀ፥ ነገር የማይበዛ፥ የማይሰክር፥ ዋዛ ፈዛዛ የማይናገር፥ በጎ አኑዋኑዋር ያለው፥ በጎ ነገርን የሚወድ፥ የሃይማኖት ትምህርት ወደሚሰጥበት ጉባኤ ለመሔድ የሚፋጠን፥ ታዛዥ፥ የሚያነብበውን ለመሥራት የሚተጋ፥ የሚያነብበውን ኃይል ቃል የሚያውቅ አናጉስጢስነት ይሾማል ። /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ፤ ረስጣ 15/ ።

### 2/ ሥርዐተ ሢመተ አናጉስጢስ

ሀ/ አናጉንስጢስ በሚሾምበት ጊዜ አስቀድሞ ኤጲስ ቆጶሱ አንብብ ብሎ ወንጌል ይሰጠዋል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ፤ ረስጣ 20/ ።

ለ/ ኤጲስ ቆጶስ አናጉንስጢስን ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም በቃል ብቻ አናጉንስጢስ ብሎ ይሾመዋል /ፍት. መን. 8 ክፍል 2 ፤ ረስጣ 27 በደስ 7 በስ 48/ ።

ሐ/ አናጉንጺጢስ ሚስት ያላገባ ከሆነ ከሴት ርቶ እንደኖረ ካልተመሰከረለት አይሾምም / ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 2/ ::

### 3/ የአናጉንስጢስ ሥራ

ሀ/አናጉንስጢስ አንባቢ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ያነብባል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ፤ ድስቅ 1 ቀዳማዊ / ::

ለ/ አናጉንስጢስ ከፍ ካለ ቦታ ቆሞ ከብሉያት መጻሕፍት በክፍል እየከፈለ እየመጠነ ያነብባል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ድስቅ 12/ ::

ሐ/ አናጉንስጢሳውያን ንባብ በሚያነቡበት ጊዜ ልብሰ ተክኖ አይለብሱም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/ ::

### 4/ አናጉንስጢስ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ/ አናጉንስጢስ ከሰረቀ ከሹመቱና ከማንበብ ሥራው ይታገዳል ፤ ከዓመት በኋላ ግን ወደ ሥራው ይመለሳል ፤ ማዕርግ አይጨመርለትም ፤ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በአንባቢነቱ ማዕርግ ይኖራል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 4 ፤ በስ 48/ ::

ለ/ በገና መች ከሆነ ከተሾመ በኋላ ወደዚህ ሥራው መመለስ አይገባውም ፤ ከተመለሰና በዚሁ ሥራው ከተገኘ በሰባት ሱባኤ ጾም ይቀጣል ፤ ከአልታረመ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይለያል /ፍት. መን. አን. 8፤ ክፍል 4 በስ 74/ ::



### 5/ ሥርዓተ አናጉንስጢስ

አናጉንስጢስ ሚስት ማግባት ይችላል ፤ ሚስቱ ከሞተችበት ሁለተኛ ያገባል /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 5 ፤ ረስጠብ 117 በስ 55/ ::

## ለ/ የመዘምራን ሢመት ሥርዓት

### 1/ ሥርዓተ ሢመተ መዘምራን

ኤጲስ ቆጶስ መዘምራንን በቡራኬ ይሾማል እንጂ አንብሮተ እድ አያደርግም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 2/ ::

### 2/ የመዘምራን ሥራ

ሀ/ መዘምራን ዘማሪዎች ስለሆኑ ይዘምራሉ /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3/

ለ/ መዘምራን የሚዘምሩት ከመዝሙረ ዳዊት ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ደስቅ 12/ በሀገራችን የቅዱስ ያሬድን ድርሰት ጭምር ይዘምራሉ ::

ሐ/ መዘምራን በሚዘምሩበት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም /ፍት. መን.አን. 8 ክፍል3/

### 3/ ሥርዓተ መዘምራን

መዘምራን ሚስት ማግባት ይችላሉ :: ሚስታቸው ከሞተችባቸው ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ /ፍት.መን. አን. 8 ክፍል 5 ፤ ረስጠብ 17 በስ 55/



## ሸ/ የዐጸውተ ኆዋኅው ሢመት ሥርዐት

### 1/ የዐጸውተ ኆዋኅው ሥራ

ሀ/ ዐጸውተ ኆዋኅው /ደጆች የሚከፍቱና የሚዘጉ/ በወንዶች መግቢያ በር ቆመው ይጠብቃሉ /ፍት. መን. አን 8 ክፍል 3 ድስቅ 12/ ::

ለ/ ዐጸውተ ኆዋኅው አንዲት ሰዓት እንኳ ከበሩ መለየት የለባቸውም /ፍት.መን. አን. 8 ክፍል 3 ፤ ጸክ 49/ ::

ሐ/ ዐጸውተ ኆዋኅው ደሙን አያቀብሉም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ጸክ 39/ ::

### 2/ ሥርዐተ ዐጸውተ ኆዋኅው

ዐጸውተ ኆዋኅው ሚስት ማግባት ይችላሉ ሚስቶቻቸው ከሞቱባቸው ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ :: /ፍት. መን. አን. 8 ፤ ክፍል 3 በስ 55/ ::

## ቀ/ የዲያቆናውያት ሢመት ሥርዐት

1/ ለዲያቆናዊትነት ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ/ በልባቸው ከኃጢአት የነጹ
ለ/ ለበጎ ሥራ የነቁ፥
ሐ/ በሥራው ሁሉ የሚታመኑ፥
መ/ ነገር የማይሠሩ
ሠ/ 60 ዓመት የሞላቸው፥
ረ/ በአንድ ወንድ ጸንተው የኖሩ
ሰ/ ልጆቻቸውን በሥርዓት ያሳደጉ
ሸ/ እንግዳ የሚቀበሉ



ቀ/ የቅዱሳንን እግር የሚያጥቡ
በ/ በደዌ ችግር ለተጨነቁት የሚራሩ
ተ/ በበጎ ሥራ ሁሉ ጸንተው የኖሩ
በበጎ ሥራ ጸንተው ለመኖራቸውም የተመሰከረላቸው ሴቶች ዲያቆናዊትነት ይሾማሉ /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ፤ ድስቅ 17 ፤ 1ጢሞ. 5፡9-10/ ::

### 3/ ሥርዓተ ሢመተ ዲያቆናውያት

ዲያቆናውያት በአንብሮተ እድ አይሾሙም:: የሚሾሙት በቃል ብቻ ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ድስቅ 17/ ::

### 4/ የዲያቆናውያት ሥራ

ሀ/ ዲያቆናውያት የሚሾሙት ከኤጲስ ቆጶሱ ወደ ሴቶች ለመላክ፥ የሚጠመቁትን ሴቶች ከእንገት በታች ቅብዐ ሜሮን እንዲቀቡ በጠቅላላ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች ሊፈጽሙት የሚገባውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲፈጽሙ ነው /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 1 ፤ ድስቅ 17 ረስታ 59/ ::

ለ/ ዲያቆናውያት ሴቶች አይባርኩም ፤ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሠሩትን የክህነት ሥራ አይሠሩም ፥ ሴቶች የሚገቡበትን በር ብቻ ይጠብቃሉ /ፍት. መን. 8 ክፍል 3 ረስጣ 59/ ::

ሐ/ ዲያቆናውያት በሕዝቡ ዘንድ ክብር አላቸው "ወትኩን ዲያቆናዊት ክብርተ በኀቤክሙ." /ፍት. መን. አን. 8/ ::

መ/ ዲያቆናውያት እንደ ዲያቆናት "ተንሥኡ ጸልዩ" እያሉ ጸሎት አያዝዙም ፤ ዲያቆን ሳያዝዛቸው ምንም ነገር አይሠሩም /ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 በደስ 6/ ::

ሠ/ ስለማናቸውም ጉዳይ ለመነጋገር አንዲት ሴት ዲያቆናዊትን ሳትይዝ ብቻዋን ወደ ዲያቆን ወይም ወደ ኤጲስ ቆጶስ መሔድ አይገባትም ፤ ክልክል ነው /ፍት. መን. አን. 8 በደስ 34/ ::

ረ/ ዲያቆናዊት ሴቶችን ልትገሥፅ፥ ልትመክር፥ ልታስተምር በመሳሰለው ሁሉ ልትረዳቸው ይገባል /ፍት. መን. አን. 8 በደስ 34/ ::

ሰ/ ዲያቆናውያት ቅስና አይሾሙም ፤ ቄስ አይባሉም በቤተ ክርስቲያንም የማኅበር ጸሎት ጀማሪ፥ ፈጻሚ አይሆኑም ::

ቀ/ ዲያቆናውያት ቃላቸውን ከፍ አድርገው ጮኸው አይጸልዩም "ወኢይጸልያ በልዑል ቃል" / ፍት. መን. አን. 8 ክፍል 3 ጸክ 11/ ::

## 5/ የክህነት ዓላማና ጥቅም

የክህነት ዓላማና ጥቅም ሰዎችን ከኃጢአትና ከሰይጣን ሥራ ሁሉ በመለየት፥ በማስተማር፥ በመቆጣተር፥ በመጠበቅ፥ በመቀደስና በማንጻት፥ በመናዘዝና በመፍታት፡-

ሀ/ ለጨለማው ዓለም ብርሃን ለመሆን፥
ለ/ አልጫ የሆነውን ዓለም ለማጣፈጥ፥



ሐ/ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመፈጸም ለምእመናን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለማስጠት የእግዚአብሔር ልጆች፥ የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ ለማብቃትና ድኅነተ ነፍስ ለማስጠት ነው ::

መ/ እግዚአብሔርን በቅዳሴ በውዳሴ ለማመስገንና መንፈሳዊ አገልግሎት ለመፈጸም ነው ::

## 6/ የሥርዓተ ክህነት ትርጉም

ሀ/ ልጆቹን ሠርቶ ቀጥቶ ማሳደግ ያልቻለ፥ በቤተሰብ አስተዳደር ያልተፈተነ በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ሠሪዐ ቤቱን ያላሳመረ ቤተሰብ ማስተዳደር ያልቻለ ፥ ቤተ እግዚአብሔርን ማስተዳደር ስለማይችል ነው ::

"እመሰ ውእቱ ዘኢያሤኒ ሠሪዐቤቱ እፎ ያሤኒ ሠሪዐ ቤተ እግዚአብሔር ወቤተ ክርስቲያኑ"7 /1ኛ ጢሞ. 3፡4-5 ፤ ፍት. ነገ. 5/

ለ/ ሐዲስ አማኒ ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ሰይጣን በአመጣው ትዕቢት እንዳይያዝና እንዳይታበይ ነው ::

"በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን" /1ኛ. ጢሞ. 3፡6 ፤ ፍት. ነገ. አን. 5፡9/

ሐ/ ዕውር፥ ደንቆሮ፥ ዝንት ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም የተከለከለው ነውር ሆኖበት አይደለም :: በቤተ እግዚአብሔር ከሚሠራው



ሥራ እሱ ሊሠራው የሚገባውን ሥራ መሥራት የማይቻለው ስለሆነ ብቻ ነው ::

"እኮ ከመ ውእቱ ነውር አላ እስመ ውእቱ ኢይክል በእንተ ፈጽሞቱ ለዘውእቱ ይትፈቀድ እምግባራተ ቤተ ክርስቲያን" /3ቀሌ አንቀጽ 52 ፤ ፍት. ነገ. አንቀጽ 5/::

መ/ ኤጲስ ቆጶስ እሑድ እንዲሾም የተወሰነበት ምክንያት ሕዝቡ አምስቱን ቀን በተግባረ ሥጋ አሳልፈው ቀዳሚት በተግባረ ነፍስ ማለት ሰው በማስታረቅ፥ ሕሙማንን እሥረኞችን በመጠየቅ ውለው ለጸሎት፥ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሔዱትና የማሰበሰቡበት እሑድ ስለሆነ ሁሉ እንዲያውቀውና በሕዝብ ፊት እንዲሾም ነው :: ሁለተኛም እሑድ ጌታ የተጸነሰበት፥ ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር የገለጠበት ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ያወረደበት እመቤታችን ያረፈችበት ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በቅዱስ ዕለት ቅዱስ ሢመት እንዲፈጸም ነው ::ከዚህም ሌላ "አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር ወጥቼ ወርጄ ነግጄ አትርፌ አምስት ጨምሬበታለሁ እነሆ መክሊትህ ከነትርፋ" ብሎ ኤጲስ ቆጶሱ በኋላ የሚያስረክብባት ዕለት ስለሆነች ነው /ዘፀ. 20፡8-11 ፤ ማቴ. 28፡1 ፤ ማር. 16፡1-113 ፤ ሉቃ. 24፡1-43 ፤ ዮሐ. 20፡1-21 ፤ የሐ. ሥራ. 2፡1-21 ፤ ማቴ. 25፡14-23/ ::

ሠ/ ኤጲስ ቆጶሳቱ በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶሱን ከመሾማቸው በፊት እጃቸውን የሚታጠቡበት ምክንያት እኛ በምናውቀው በአፍአ ንጽሕ

ብለን ሾመንሃል :: አንተ በምታውቀው በውስጡ ዕዳ የለብንም ዕዳው በአንተ ነው ለማለት ነው ::

ረ/ ኤጲስ ቆጶሱን ሲሾሙት መስቀል የሚያሲዙት መከራ ትቀበላለህ ለማለት ነው ::

"ዘውእቱ ዘተሠይመ ለቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እምኀበ ሥሉስ ቅዱስ በምሥጢረ መስቀል" /ፍት.ነገ. አን. 5/

ሰ/ ቀዳማዊው ኤጲስ ቆጶስ በተሿሚው እጅ ላይ እጁን የሚጭነው እስከ አሁን ድረስ ከእኔ በታች ነበርህ ከእንግዲህ ወዲህ ግን በሥልጣነ ክህነት ከእኔ ጋር አንድ ነህ ሲለው ነው ::

ሸ/ የሢመተ ኤጲስ ቆጶሳት በዓል ሦስት ቀን የሚከበረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በ3ኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የመነሣቱ ምሳሌ ነው ::

"ወያብዕሉ ሠለስተ መዋዕለ በዐለ መንፈሳዊተ በአምሳለ ምሥጢሩ ለዘተ ንሥአ በሣልስት ዕለት" /ፍት. ነገ. 5 ፤ ማቴ. 16፡21 /

ቀ/ ዲያቆናት በሚሾመው ኤጲስ ቆጶስ ራስ ላይ ፬ቱን ወንጌል ዘርግተው የሚይዙበት ምክንያት ወንጌልን ገልጠህ ታስተምራለህ፥ ስለ ወንጌል መከራ ትቀበላለህ ለማለት ነው ::

በ/ <u>መጀመሪያው የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ</u> የርከበ ካህናት ዕለት እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ 3ኛ ጊዜ

በባሕረ ጥብርያዶስ ለደቀ መዛሙርቱ የተገለጠበት ቀን በመሆኑና በዚህም ዕለት ቅዱስ ጴጥሮስን ሊቀ ሐዋርያት አድርጎ በመሾም 3 ጊዜ በጎቼን ጠብቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱ የበላይና የምእመናን ጠባቂነት አደራ የሰጠበት ዕለት በመሆኑ ነው /ዮሐ. 21፡1-17/ ፡፡ **ሁለተናው ጉባኤ** ጥቅምት 12 ቀን የሆነበት ምክንያት ይህ ዕለት መጀመሪያውን ወንጌለ መንግሥት የጻፈው የሐዋርያው የማቴዎስ መታሰቢያ በዓል ከመሆኑም በላይ የሐዋርያው የማቴዎስ መታሰቢያ በዓል ከመሆኑም በላይ ወቅቱ ክረምቱ አልፎ በጋው የሚተካበት፥ አዝመራ የሚሰበሰብበት ጊዜ ስለሆነ በበጋም ችነፈርና ድንገተኛ ሞት ስለሚበዛ ከሞት አስቀድሞ በፍቅር በንጽሕና ሆኖ ንስሐ ገብቶ በጸሎትና በምስጋና እግዚአብሔርን ለመለመን ነው ፡፡

ተ/ በኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ /ሲኖዶስ/ መካከል በአለ ጠረጴዛ ላይ ወንጌል የሚቀመጥበት ምክንያት በጉባኤው መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አለ ለማለትና እውነተኛ ፍትሕ እንፈርዳለን በጽድቅ እንነጋገራለን ለማለት ነው ፡፡

ቸ/ ዲያቆን በ30 ዓመቱ ቅስና እንዲሾም የተደረገበት ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዓመቱ ስለተጠመቀና ማስተማር የጀመረው በዚሁ ዘመኑ ስለሆነ ነው /ሉቃ. 3፡23 ፤ ፍት. ነገ. አን. 6፡1/ ፡፡

ኀ/ ብሉያትን ሐዲሳትን ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያልተማረ ቅስና እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ያልተማረ ቅስና እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ምእመናንን ትምህርተ ወንጌል እያስተማረ የሚጠብቅ ስለሆነ ነው ፡፡



ነ/ ኤጲስ ቆጶስ ቄሱንና ዲያቆኑን ብቻውን የሚሾመው መዓርጉ 3ኛ/ ስለሆነ ነው ፡፡ይኸውም ወደላይ ጳጳስ፥ ሊቀ ጳጳሳት፥ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት፥ ወደታች ቄስ ዲያቆን ነው፡፡

ኘ/ ካህን ሁለት እንትማማች ከአገባ ስው ሠርግ እንዳይሔድ የተከለከለበት ምክንያት ጋብቻው ሕገወጥና ርኩስ ከመሆኑም በላይ ሠርገኛውም ኃጢአተኛ ስለሆነ ነው ፡፡

አ/ ዲያቆን ለካህናት ሥጋውን ደሙን የማያቀብልበት ምክንያት እሱ የካህናት ተላላኪ እንጂ ካህን ስለ አልሆነ ነው ፡፡

"ወኢየሀብ አውሎግያ አላ ውእቱ ይንሣእ እምኤጲስ ቆጶስ ወኢይፁር ቁርባነ ወሰበ ያረ ኤጲስ ቆጶስ አው ወእምቀሲስ ወኢይፁር ቁርባነ ወሰበ ያረ ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ ውእቱ ይመጡ ፅዋዐ ለሕዝብ አኮ ውእቱ ካህን አላ ላእከ ካህናት" 1ኛ/ ቀሌ 58 ፍት. ነገ. አን. 7 ክፍል 3/፡፡

"ወኢያንብር እዴሁ ወኢይመጡ ቁርባነ ለዘይትሌዓሉ እላ የእኃዝ ዘይቴሐትዎ ለመልእክተ ቤተ ክርስቲያን" /ቀኖና ጴጥሮስ/

ከ/ ሊቀ ዲያቆናት ለኤጲስ ቆጶሱ የአስተዳደር ሥራ ረዳት እንዲሆነውና ጥቃቅኑን ሥራ እንዲያከናውን የተደረገበት ምክንያት በኦሪቱ በእሥራኤል ልጆች መካከል ስለሚፈርደው ፍርድ ሥራ እንዳይበዛበት ሥልጣኑን በማከፋፈል ሥራ እንደተቃለለለትና ፍጻሜው እንደ አማረለት ሁሉ ኤጲስ ቆጶሱም ሥልጣኑን ከአከፋፈለ



የቤተ ክርስቲያን ሥራ ሊቃለልና ባለ ጉዳዮች በቀላሉ ውሳኔ ሊያገኙ እንደሚችሉ ስለታመነ ነው ፡፡ "ከመ ይኩን ዘኢያስተሐምም ዘእንበለ ግብራት ዓቢያን በከመ አምከሮ ዮቶር ሐሚሁ ለሙሴ በእንተ ሠሪዐ ፍትሕ ማእከለ ደቂቀ እሥራኤል ወተወክፈ ምክረ ዚአሁ ወአሠነየ ደኅራተ" /ፍት. ነገ. አን. 7 ክፍል 4 ፤ ዘፀ. 18፡13-26/ ፡፡

ኸ/ አናጉንስጢስ ከብሉያት መጻሕፍት ሁለት ሁለት ክፍል የሚያነብበት ምክንያት አንዱ የዔዋዌ ሥጋና የዔዋዌ ነፍስ፥ አንዱ የሚጠተ ሥጋና የሚጠተ ነፍስ ምሳሌ ነው ፡፡ /2ኛ/ ዜና መዋ. 36፡5-23 ፤ዕዝ. 1፡1-7 ፤ ማቴ. 1፡11-12 ፤ ዘፍ. 3፡1,24 ፤ ዮሐ. 3፡14,18 ፤ 1ኛ. ጴ. 3፡19/፡፡

## ክፍል 7

### ለ/ ሥርዐተ ጋብቻ

#### 1/ የጋብቻ አመሠራረት

ጋብቻ ከሕግጋተ እግዚአብሔር አንዱ ነው ፡፡ ስለ ጋብቻ በኦሪትም፥ በወንጌልም ሕግ ተሠርቶዋል ፡፡

በድንግልና ሊኖሩ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው ሰዎች በቀር ሁሉ በጋብቻ እንዲኖሩ ጥንቱን በአዳምና በሔዋን ጋብቻን መሠረተ ፡፡

ይኸውም "ሰው ብቻውን ሊኖር አግባብ አይደለም የምትረዳውን ጓደኛ እንፋጠርለት እንጂ" ብሎ እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን በመፍጠሩ ታውቋል፡፡ /ዘፍ. 2፡18/ ፡፡



እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ ዕንቅልፍ ጣለበት እንቀላፋም፥ ከጎኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው ፡፡ እግዚአብሔር አምላክም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ፡፡ ወደ አዳምም አመጣት ፡፡ አዳምም አለ "ይህቺ አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት ፡፡ እሱዋም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል ፡፡ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ፡፡ ሚስቱንም ይከተላል ፡፡ ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ" /ዘፍ. 2፡22-24/ ፡፡

እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ፡፡ እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት" /ዘፍ. 1፡27/ ፡፡

የአዳምና የሔዋን ጋብቻ የሕጋዊ ጋብቻ መሠረት ነው ፡፡ ለአዳም ብዙ ሴቶች አለመፈጠራቸው ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት እንጂ አያሌ ሴቶች ያልተፈቀዱለት መሆኑን፥ ለሔዋን ብዙ ወንዶች አለመፈጠራቸው ለአንዲት ሴት አንድ ባል እንጂ አያሌ ወንዶች ያልተፈቀዱ መሆኑን ያመለክታል ፡፡

በአዳምና በሔዋን የተጀመረው ሕጋዊ ጋብቻ ወደ ልጆች ሲተላለፍ በብዙዎቹ ዘንድ ሕጋዊነቱና ሥርዓቱ ባይጠበቅም ሕገ እግዚአብሔርን በጠበቁትና በታወቁት አባቶች ዘንድ ተጠብቆ ኖሩዋል፡፡

ጥቂቶቹንም ለምሳሌ ያህል ብናቀርብ በዘመነ አበው የኖኅ ጋብቻ የጠባረከ ሐረጋዊ ጋብቻ ነበር ፡፡ ሕጋዊና የተባረከም በመሆኑ በሕገ ወጥ ግንኙነትና በዝሙት የተባዛው የዓለም ሕዝብ በንፍር ውሀ ሲጠፋ

ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ ድነዋል ፡፡ በእርሱም ዘር ዓለም በሰው ልጆች ተሞልታለች /ዘፍ. 7፡9/ ፡፡

እንዲዚሁም የይስሐቅና የርብቃ፥ የዮሴፍና የአስኔት ጋብቻ ሕጋዊና የተባረከ ጋብቻ ነበር፡፡

ከክርስትና በፊት የነበረው የጋብቻ ሥርዓት የዘርና የእምነት ልዩነት ይታይበት ነበር ፡፡ በክርስትና ሥርዓት የእምነት ልዩነት የሚደረግ ቢሆንም በጋብቻ የዘር ልዩነት አይፈጸምም ፡፡

ለምሳሌ በኦሪት እሥራኤል ከአሕዛብ፥ አሕዛብ ከእሥራኤል እንዳይጋቡ ክልክል ነበር ፡፡ "ኢተሀብ ወለተከ ለአሕዛብ ወኢትንሣእ ወለቶሙ ለአሕዛብ /ዘዐ. 7፡3/ ፡፡

በኦሪት ወንድሙ ሳይወልድ ከሞተ የሟች ወንድም ሚስቱን አግብቶ ዘር ይተካ ነበር /ዘዳ. 25፡5-10 ፤ ማቴ. 22፡24-28/ ፡፡

ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ በመሆኑ በኦሪትም ሆነ በወንጌል ማንም ሰው ሚስቱን እንዳይፈታ ተከለከለ ፡፡

ይህም በመሆኑ በኦሪት ሰዎች ሚስቶቻቸውን ሲጠሉና ሲፈቱ ሲፈልጉ ሌላ የተንኮል ዘዴ አዘጋጁ ይኸውም የሰዎችን አሙዋሙዋት ሲመረምር የሚችል የፍልስፍና ጥበብ በአልተገኘበት በዚያ የሞኝ ዘመን ወንዶች ሚስቶቻቸውን መርዝ እያጠጡ አፍ እያፈኑ ልብ እያሹ መግደል ጀመሩ ፤ ይህ የሰዎች ተንኮል በግልጽ እየታወቀ ስለሔደ ኦሪትን የጻፈ ሙሴ የጋብቻን ሕግ ለማሻሻለውም ሕግ ፍቺን የሚፈቅድ ሲሆን ሥርዓቱ ግን ጠበቅ ያለ ነበር ፤



ይኸውም ባሉዋ ሚስቱን ሲፈታት ከፈለገ በመግደልና ተንኮል በመሥራት ፍንታ የምትፈታበትን ነውር በደብዳቤ ጽፎ በዐደባባይ አንብቦና አጋልጦ እንዲፈታ ሙሴ በኦሪት ሥርዓት ሠራ ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጋብቻ ሲያስተምር ፈሪሳውያን በማናቸውም ምክንያት ሰው ሚስቱን ሊፈታ ይገባል ወይ ብለው ቢጠይቁት የመለሰላቸው መልስ "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው መለየት ስለማይገባው ባል በማናቸውም ምክንያት ሚስቱን ሊፈታ አይገባውም" ባላቸው ጊዜ ለተቃውሞ ያቀረቡት ጥያቄ ይህን ሙሴ ያሻሻለውን ሥርዓት ነበረ በጥያቄያቸውም እንደተገለጠው እንግዲህ ሙሴ ሰው ሚስቱን ሲፈታ የፍችዋን ደብዳቤ ጽፎ ይፍታት ለምን አለ ቢሉት ሙሴ ይህን ያዘዘ ስለልባችሁ ክፋት እንጂ ቀድሞስ እንዲህ አልነበረም ፡፡ እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ መፍጠሩ ማግባት መፍታት እንዳይኖር ነው በማለት ካላመነዘረችበት በስተቀር ማንም ሰው ሚስቱን እንዳይፈታ የተፈታችውንም እንዳያገባ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል አዘዘ /ዘፍ. 1፡27፤2፡24 ፤ ዘዳ. 2፡4 ፤ ማቴ. 19፡3-12፤ 5፡31-32/ ፡፡

ጋብቻን ያከበሩ በሕጋዊ ጋብቻ የኖሩ ደጋግ ቅዱሳን በሕገ ልቡና እንደነበሩ ሁሉ በሕገ ኦሪትም ነበሩ ፡፡

ለምሳሌ የኢያቄምና የሐና ጋብቻ ቅዱስ ጋብቻ ነበር፡፡ የተቀደሰ ጋብቻ በመሆኑም የቤዛዊተ ዓለም የቅድስት ድንግል ማርያም ወላጆች የእምላካችን፥ የፈጣሪያችን የመድኃኒታችን አያቶች ለመሆን በቅተዋል ፡፡



እንዲሁም የዘካርያስና የኤልሳቤጥ ጋብቻ የተባረከ ጋብቻ ነበር ቡሩክና ሕጋዊ በመሆኑም መጥምቁ መለኮት ዮሐንስን አፈራ ፡፡

ጋብቻ በኦሪትም በወንጌልም የታዘዘና የተከበረ መሆኑን በዚህ መረዳት አያዳግትም "ክቡር አውስቦ በኵሉሄ ወለምስካቦሙኒ አልቦቱ ስእበት" ዕብ. 13፡4/ ፡፡

ጋብቻ በብሉይም ሆነ በሐዲስ በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ በመሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ ትምህርት በጀመረበት ወራት የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና ወደ ሠርግ ቤት ተጠርቶ በሔደ ጊዜ ፈጽሞ አክብሮታል ፡፡ ያንንም ጋብቻ ባርኮታል ፡፡

ስለ ጋብቻ ኦሪትና ወንጌል በአንድ ቃል "ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል ፤ በሚስቱም ይዋሐዳል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ" በማለታቸው እውነተኛ ምስክሮች ሆነዋል ፡፡

ዳግመኛም ቅዱስ ወንጌል "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይም" አለ ፡፡

ዳግመኛም ሐዋርያው ጳውሎስ "ወንዶችም ሚስቶቻችሁን እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱ ማንም ማን ሥጋውን ሊጠላ የሚቻለው የለም" በማለቱ ሴትን ለባሉዋ አካል አደረጋት ፡፡ ዳግመኛም "ሴቶች ሆይ ስሙ ለባሉዋ አካል አደረጋት ፡፡ ዳግመኛም "ሴቶች ሆይ ስሙ" ለባሉቻችሁ ክቡር ለሚሆን ለእግዚአብሔር እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተሀዙ" አለ ፡፡ቀጥሎም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ስለእሱዋ ሰውነቱን ለሞት የሰጠላት እንደሚወድዳት ባልም ሚስቱን እንዲወድ አዝዙዋል ፡፡

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ "አንተ ብፁዕ ነህ በጎ ነገርም ይደረግልሃል ፤ ሚስትህም በቤትህ አዳራሽ ውስጥ እንደ አማረ ወይን ትሆናለች ልጆችህም በማዕድህ ዙሪያ እንደ አዲስ ዘይት ተክል ይሆናሉ ፡፡እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል ባለ ዘመኑ ልክ በጎ ነገሮችን ያያል" ሲል የዘመረው በጋብቻ የሚገኘውን በረከትና መልካም ኑሮ ያረጋግጣል/ መዝ. 127፡1-4/ ፡፡

ጋብቻ በዚህ ዓይነት በሕግ ሲፈጸም የሰዎችን ኑሮ ሲያሳምር መልካም ዘር ሲተካ በሕገ ወጥነት በአመንዝራነት ሲፈጸም ደግሞ የሰዎችን ኑሮ ሲያበላሽ እስከ ዘመናችን ደርሱዋል ፡፡

## 2/ የጋብቻ ተፈላጊነት

የጋብቻ ተፈላጊነት ስለ ሦስት ነገር ነው ይኸውም፡-

1ኛ/ በኑሮ ለመረዳዳትና ሕይወትን በጋራ ለመምራት ነው ፡፡ "ሰው ብቻውን ሲኖር አይገባውምና የምትረዳውን እንፍጠርለት" ፡፡ ይላል /ዘፍ. 2፡18/

2ኛ/ ለመባዛትና ዘር ለመተካት ነው "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት" ይላል /ዘፍ. 1፡28-29፤ 9፡1-3/ ፡፡

3ኛ/ ከዝሙት ለመጠበቅ ነው፡፡ "ወከመሰ ኢትዘምው ኩሉ ብእሲ ይንበር በብእሲቱ ወኩላ ብእሲት ትንበር በምታ" ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አዝዞዋል /1ኛ ቆር. 7፡2 ፥5 ፤ 1-9/ ፡፡

## 3/ ማጨት

የጋብቻ መቅድሙ መተጫጨት ነው ፡፡
የመተጫጨት ባህልና ሥርዓት፡-

ሀ/ የፈቃድና የስምምነትን
ለ/ የዕድሜን
ሐ/ የሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድናን
መ/ የሃይማኖትን አንድነት ዘርዝሮ ይገልጣል ፡፡

ተጋቢዎች ከተዋወቁ ርስ በርሳቸውም ከተፈቃቀዱና ከተስማሙ ለወላጆቻቸውም አሳውቀው ፈቃድና ስምምነት ከአገኙ በኋላ የውዴታ ቃላቸውን በቅድሚያ ለመምህረ ንስሐ ወይም ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደሪ ወይም ለክፍሉ ኤጲስ ቆጶስ በመንገር ወደ ጋብቻው ቃል ኪዳን ያመራሉ ፡፡

በመተጫጨት ጊዜ በብርቱ ሊታሰብበትና ጥናት ሊደረግበት የሚገባው ዐቢይ ነገር ትዳርን የሚመሠርቱ የወጣቶች ዕድሜ መመጣጠን ጉዳይ ነው ፡፡ ወጣቶች በሚጋቡበት ጊዜ በተፈጥሮ ሕግ በሃይማኖት በሥርዓትና በማኅበረሰብእ የጋብቻ ድንጋጌ መሠረት በዕድሜ የማይቀራረቡ ከሆነ በጋብቻው ላይ ችግር እንደሚያስከትል ከወዲሁ መታወቅ ሊኖርበት የሚገባው ነው ፡፡

ዕድሜን በተመለከተ ወንዶች ከ20 በላይ ሴቶች ከ15 ዓመት በላይ ሲሆናቸው መተጫጨትና መጋባት የሚፈቀድላቸው መሆኑ በቤተ ክርስቲያን ቀኖና ተመልክቶአል /ፍት. መን. 24 ም. 3 ክፍል 2/ ፡፡

በመተጫጨት ጊዜ ሊጠነቀቁለትና ሊጠብቁት የሚገባ ሌላው ጉዳይ በተጋቢዎች መካከል ያለው የዝመድና ሁኔታ ነው ፡፡



ጋብቻን የሚከለክል የዝምድና ዓይነትም 3 ነው እርሱም፡-

1ኛ/ ሥጋዊ ዝምድና
2ኛ/ የጋብቻ ዝምድና
3ኛ/ መንፈሳዊ ዝምድና ነው ፡፡ ይህም ዓይነት ዝምድና መጠበቅ እንዳለበት በቅዱሳት መጻሕፍትና በቤተ ክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ተነግሮአል፡፡

እሥራኤላውያን ቅርብ የሆነ የሥጋና የጋብቻ ዝምድናን አፍርሰው እንዳይጋቡ ብሉይ ኪዳን በጥብቅ ያስጠነቅቃል /ዘሌ. 18፡7-20 ፤ 20-21ም ፡፡/ በሐዲስ ኪዳንም አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን እንደተነገረው ዝምድናው ካልተራራቀ በቀር ሥጋዊም ሆነ የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሁሉ እንዲጋቡ አይፈቀድም የዚህም መሠረተ አሳብ በማርቆስ 6፡19 ፤ በ1 ቆሮንቶስ 5 ተገልጦአል ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድናን ለማስጠበቅ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ዝምድና ያላቸው እንዲጋቡ አትፈቅድም ፡፡

### 1ኛ/ ሥጋዊ ዝምድና

በቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥት በአንቀጽ 24፡842-853 ቁጥር ተዘርዝሮ እንደተገለፀው ሥጋዊ ዝምድና የሚጠበቀው እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ነው ፡፡ ይህም በአንድ ጎን ሰባት በአንድ ወገን ሰባትከተቆጠረ በኋላ ስምንተኛዎቹ ሊጋቡ ይችላሉ ማለት ነው፡፡



### 2ኛ የጋብቻ ዝምድና

ወደላይ ወንድ የአባቱን የአያቱን ሚስት፥ እኅት፥ እናት አያገባም ፡፡ወደታች የልጁን፥ የልጅ ልጁን ሚስት ልጁዋን፥ እኅትዋን፥ እናቷን፥ አያትዋን አያገባም ፡፡

ወደጎን የወንድሞቹንና የልጆቻቸውን ሚስት፥ ልጁዋን እኅትዋን፥ እናትዋን ፥ አያትዋን አያገባም ፡፡

የሚስቱን አያት እናት አክስት እኅትዋን፥ ልጁዋን፥ የልጅ ልጅዋን በዚህም ደረጃ ያሉ የዘመዶችዋን ሚስቶች አያገባም ፡፡ በዚህ አንጻር በሚስት በኩል የተከለከለው ዝምድና ሁሉ በባልም በኩል የተከለከለ ነው /ፍት. መን. 34፡853/ ፡፡

### 3ኛ መንፈሳዊ ዝምድና

የመንፈሳዊ ዝምድና ዓይነት ብዙ ነው ሆኖም በጋብቻ እምዳይፈርስ የሚጠበቀው መንፈሳዊ ዝምድና በጥምቀተ ክርስትና ያለው ዝምድና ነው ፡፡ይህም እንዲጠበቅ በቤተ ክርስቲያን የሕግ መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥት ታዟል፡፡

በዚህም መሠረት ወደላይ የክርስትና ልጅ የክርስትና አባቱን ሚስት ልጁን የልጅ ልጁን እኅቱን አያገባም ፡፡

ወደታች የክርስትና አባቱ የክርስትና ልጁን እናት፥ እኅት፥ የእኅቱንና የወንድሙን ልጅ አያገባም /ፍት. ነገ. 24፡847/ ፡፡



ከዚህም ሌላ በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ወንድና ሴት መጋባት እንደሌለባቸው ተከልክሎአል ፡፡ እሥራኤላውያት ሴቶች ልጆቻቸውን ለአሕዛብ እንዳይሰጡ የአሕዛብንም ሴቶች ልጆች እንዳያመጡ በብሉይ ኪዳን የተደነገገው ሕግ በሐዲስ ኪዳንም የተጠበቀ ነው /ዘዳግ. 7፡3-4/ ፡፡

ነገር ግን ወንዱ አማኒ ሆኖ ሴትዋ ባታምን አሳምኖ ማግባት ይችላል ፤ ወይም ሴትዋ የምታምን ብትሆንና ወንዱ ባያምን አሳምና ልታገባው ትችላለች፡፡ እንዲዚሁም ወንዱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ሆኖ ሴቶዋ የሌላ እምነት ተከታይ እንድትሆን አድርጎ ማግባት አይችላል ሴትዋም እንዲሁ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መልሳ ማግባት ይገባታል /1 ቆሮ. 7፡12-17 ፤ ፍት. ነገ. 24፡912-915/ ፡፡

በጋብቻ የሃይማኖት አንድ መሆን ለተጋቢዎች እጅግ ጠቃሚ ነው ፡፡ሁለቱ ዕጩኞች ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሥርዓት ጠብቀው በወላጆቻቸውና በመምህረ ንስሐቸው የውዴታ ቃላቸውን ከገለጡ በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያዘውን ይሔዳሉ ፡፡ ከዚያም የጋብቻ ደንብ ከቤተ ክርስቲያን ይፈጽማሉ ፡፡ከኤጲስ ቆጶሱ ወይም ለቃል ኪዳን አስተዳዳሪው የጋብቻ ፈቃድ ሲያገኙ ይዘጋጃሉ ፡፡

### 4/ ቃል ኪዳን /ቀለበት/ ማሠር/

የመተጫጨት ሥርዓት በውልና በስምምነት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥለው ሥርዓት የቀለበት ማሠር ወይም ቃል ኪዳንን በቃለ መሐላ መፈጸም ነው ፡፡

ቀለበት በክብነቱና ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ የቃል ኪዳን ጋብቻም ከሕይወት ፍጻሜ በቀር መፍታትና መለያየት የሌለበት መሆኑን ይተረጉማል ። በሌላም በኩል ጋብቻን በሕግ ለሚጠብቁትና ለሚፈጽሙት ታላቅ ክብር አለው ፤ የፍቅርም ምልክት ነው ። ይህም በመሐልየ ሰሎሞን "እንብረኒ ከመ ሕልቀት ውስተ ልብከ እንደ ቀለበት በልብህ ላይ አኑረኝ..." ተብሎ ተጽፎአል /መሐ. 8፡6/ ።

በሥርዓተ ጋብቻም ቀለበት የሚደረገው የቃል ኪዳን ምልክት በመሆኑ ነው ።ቃል ኪዳን በሁለት ሰዎች መካከል በመተማመን የሚፈጸም በመሐላ የሚጸና የማይለወጥና የማይፈርስ ፥ በሁለቱም በኩል የሚጠበቅ ጽኑ የፈቃድ ውል ነው ።

### የቀለበት ማሠር ወይም የቃል ኪዳን አፈጻጸም ሥርዓትም እንደሚከተለው ነው ፥

1ኛ/ ለጋብቻ የተጫጩት ወገኖች ከጋብቻው ቀን አስቀድሞ ከቤተ ክርስቲያኒቱ የጋብቻ አገልግሎት ክፍል የተሰጣቸውን ማስረጃ ጋብቻቸውን ለሚፈጽሙበት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አቅርበው ቃል ኪዳናቸውን በቤተ ክርስቲያን ይፈጽማሉ ።

2ኛ ሙሽራውና ሙሽራዪቱ ከዘመዶቻቸው ጋር ሆነው በቃል ኪዳን በተሰጠው ሕግ መሠረት የቀለበት ማሠሩ ስነ ሥርዓት ይፈጸምላቸዋል ። በመተጫጨትም ጊዜ የሰጡትን የፈቃድ ቃል በንስሐ አባታቸው አማካይነት በመሐላ ያጸናሉ ።



## 5/ ሥርዐተ ተክሊል

በሥርዐተ ጋብቻ ቅደም ተከተል መሠረት በመተጫጨትና በቃል ኪዳን የተመሠረተው ጋብቻ በተክሊል ይፈጸማል ። ክርስቲያናዊ ጋብቻ ትክክለኛነቱ የሚታወቀው በተክሊልና በሥጋ ወደሙ ሲፈጸም ነው ። ጋብቻን ያለ ሥርዓተ ተክሊል ለመፈጸም አልተፈቀደም /ፍት. ነገ. 24 ም. 5 ክፍል ዳግም፥ መጅ 1/ ።

ሥርዐተ ተክሊል በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ካህንና ምእመናን ሳይለዩበት በድንግልናና በንጽሕና ለኖረው ክርስቲያን ሁሉ ይፈጸማል ።

ሥርዐተ ተክሊል በሚያደርሱበት ቀን ሙሽራው ከዘመዶቹ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ሙሽራውና ዘነዶቹ በሰሜናዊው ማዕዘን፥ ሙሽራዪቱና ዘመዶቹዋ በደቡብዊ ማዕዘን ሥፍራ ስፍራቸውን ይዘው ይቆማሉ ።

ከዚህ በኋላ በምዕራብ በኩል በመካከለኛው ክፍል ማለት በቅድስቱ ውስጥ ከመቅደሱ ፊት ለፊት ካለው ቦታ ላይ ሊቀ ዲያቆናቱ ሙሽራውና ሙሽራዪቱ ሥርዓተ ተክሊል የሚፈጽሙበትን ምንጣፍ አንጥፈው ለሁለቱ የሚሆን መቀመጫ ፥ እንዲሁም አንድ ጠረጴዛ ሙሽሮቹ በአንድነት የሚለብሱት ነጭ መጎናጸፊያ የሚቀበሉትን ቅብዕ ቅዱስ የሚቀዳጁዋቸውን አክሊላት ያዘጋጃል ።

ቀጥሎም ካህናቱ ሥርዓተ ተክሊሉን ያደርሱላቸዋል ። ሥርዓተ ተክሊሉ እንደተፈጸመ ሙሽሮቹ አስቀድሰው ቅዱስ ቁርባን ተቀብለው ጋብቻቸውን ያጸናሉ ።



## 6/ ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል ማለት አከበረ ካለው ግሥ የወጣ ቃል ነው ።ይኸውም ክብር ማለት ነው ።

ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቃለ ኪዳንና በቡራኬ፥ በጸሎት ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን ሲፈጸም ምሥጢርነት አለው ። ከዚህ ውጪ ግን ምሥጢር አይባልም ። ምሥጢር መባሉም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ይህ ምሥጢር /ጋብቻ/ ታላቅ ነው ። እኔ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ" ኤፌ. 5፡32/ ብሎ በተናገረው መሠረት በተክሊሉ ጊዜ በሚታዩ ምልክቶችና በሚፈጸሙ ሥርዓቶች የማይታይ ጸጋ ስለሚገኝበት ነው።

በተክሊል ሥርዓት አፈጻጸም ጊዜ የሚታዩት ምልክቶችና ሥርዓቶች ቀጥ ሎ ያሉት ናቸው ።

1/ ሙሽሮቹ የሚያደርጉት ቀለበት
2/ የሚለብሱት ነጭ ልብስ
3/ የሚቀቡት ቅብዕ ቅዱስ
4/ የሚቀዳጁት አክሊል
5/ በእነዚህ ምልክቶችና በሙሽሮቹ ላይ የሚያደርሰው የካህኑ ጸሎትና ቡራኬ ናቸው ። እነዚህ ምልክቶች ሙሽራውና ሙሽራዪቱ ከመንፈስ ቅዱስ ለሚቀበሉት የማይታይ ጸጋ መቀበያ ምክንያቶች ናቸው

የጸሎተ ተክሊል ፍጻሜ ጸሎተ ቅዳሴ ነው ።ከጸሎተ ተክሊል አያይዞ ጸሎተ ቅዳሴ ደርሶላቸው ሙሽሮቹ ሥራውን ደሙን ይቀበላሉ ።ጸሎተ ተክሊል ተደርሶ ቁርባን ከቀረ ግን ተክሊሉ ፍጹም አይደለምና ጋብቻው አይጸናም ። "ወማዕሠረ ተዋስቦስ ኢይከውን



ወኢይትፌጸም ዘእንበለ በህልዎተ ካህናት ወጸሎት ዘላዕሌሆሙ ወይመጥውዎሙ ቊርባነ ቅዱሰ በጊዜ ተክሊል ዘቦቱ ይትወሐዱ ክልዔሆሙ ወይከውኑ አሐደ ሥጋ በከመ ነገረ እግዚእነ ሎቱ ስብሐት ወዘእንበለ ዝንቱሰ፥ ኢይትኌለቊ ሎሙ አውስቦ" ይላል /ፍት. ነገ. አን. 24 መጅ 1/ ።

## 7/ በምሥጢረ ተክሊል የሚገኝ ክብርና ጸጋ

ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በተባሉት ሥርዓቶች ሁሉ ለምእመናን የሚሰጥ ልዩ ክብር አለ ።

ተክሊልም ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ እንደሆኑ ከቅዱስ ቁርባን ጋር ሲፈጸም ይህንን ታላቅ መንፈሳዊ ክብር ያስገኛል ።

ሙሽራውና ሙሽራዪቱ በቅዱስ ጋብቻ አንድ ይሆናሉ ። ይኸው አንድነታቸውም "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም" በሚለው ቃል መሠረት መለያየት ሳይኖር እስከ ሞት ድረስ የጸና ይሆንላቸዋል /ማቴ. 19፡6/ ።

ሸንገላና ግብዝነት የሌለበት እውነተኛ ፍቅር ይኖራቸዋል ። "ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው" ብሎ ክቡር ዳዊት እንደተናገረው የተባረኩ ልጆችንይወልዳሉ /መዝ. 126፡3 ።/ በአጠቃላይ የመከባበርና የመፈቃቀር፥ የመረዳዳትና የመተማመን በሁሉ ነገር የመስማማት የመተባበር መንፈስን በምሥጢረ ተክሊል ያገኛሉ

## 8/ ከጋብቻ በኋላ የባልና ሚስት አኗኗር

ሀ/ ባልና ሚስት የኑሮ ዕኩልነት አላቸው ። የሴት ከባሉዋ ጎን መገኘት የተፈጥሮን መበላለጥ አያመለክትም ፤ እንዲያውም ከፍ ብላ ከራሱ ዝቅ ብላ ከእግሩ አጥንት አለመፈጠሩዋ ከጎን መፈጠሩዋ የበላይና የበታች ሳትሆን ዕኩል መሆኑዋን ያሳያል ።

ባል ለሚስቱ ራስ ነው ፤ ሚስት ደግሞ ለባሉዋ ዘውድ ናት ባል ለሚስቱ ጠባቂዋ ኃይሉዋ ነው ፥ ሚስት ደግሞ ለባሉዋ ክብሩ ናት ፥ ይህንንም እውነተኛ ትምህርት ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች በአስተማረበት መልእክቱ ለሱ አድርጎ በመተንተን በምሳሌ እያደረገ ተርጉሞታል /1ቆሮ. 11:6/ ።

ልዑል እግዚአብሔር የአዳምን ብቸኝነት ተመልክቶ የምትስማማውን የኑሮ ጓደኛ / ሔዋንን በፈጠረለት ጊዜ በነፍስም በሥጋም አዳምን አሳክሎ አስመስሎ አስተካክሎ ፈጥሮዋታል ፥ በተፈጥሮ ጠባይም ሆነ በአስተሳሰብ ከአዳም አሳሳነሳትም። አዳምም ሔዋን እሱን አህላ እሱን መስላ በተሰጠችው ጊዜ "ይህች አጥንት ከአጥንቴ የተገኘች አጥንቴ ናት ፤ ይህችም ሥጋ ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋ ናት" በማለት አካሉ አምሳሉ መሆኑዋን አረጋገጠ ፤ ስሟንም ሔዋን ብሎ ሰይሟታል ። ሔዋንም ማለት ሕይወት የሕያዋን እናት ማለት ነው /ዘፍ. 2:23 ፤ ኩፋ. 4:6/ ።

ከጾታ ልዩነት በቀር በባልና ሚስት መካከል አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች የሚያደርግ የተፈጥሮ ልዩነት የለም ። እንዲያውም ባልና ሚስት በመካከላቸው



መከፋፈል የሌለባቸው አንድ አካል ናቸው ። ፍቺና መለያየት የሌለበት የጋብቻ ቃል ኪዳናቸው ያዋሕዳቸዋል።

የተፈጥሮ ምሥጢር በሚተረጎምበት የጋብቻ ቃል ኪዳናቸው ምክንያት ወንድ የወለዱትን ፥ ያሳደጉትንና ያሥተማሩትን እናቱንና አባቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል ። ስለሚስቱ ሰውነቱን ለመከራ አሳልፎ ይሰጣል ።አባት እናቱን አገሩንም አያስባቸውም /ካል. ዕዝ. 4:20-21/ ።

ሰው ከወለዱት ከእናቱና ከአባቱ ሚስቱን ይወዳታል /ካል. ዕዝ. 4:25/።

የፍቅርና የአንድነት ሕይወታቸው በአንድ አሳብ በአንድ ምክርና የጋራ ፈቃድ የሚመራ ነው ። ስለሆነም ጋብቻ በባልና ሚስት መካከል በአሳብ፥ በምክር፥ በሥራ የተቀናጀ በፍቅር ተዋሕዶ የጸና እኩልነት መከባበር መተሳሰብ መተዛዘንና መደጋገፍ የሰፈነበት እንዲሆን ያስፈልጋል ።

ለ/ ባልና ሚስት በቃል ኪዳን ቀለበት ተሣስረው በፈቃደ እግዚአብሔር ከተዋሐዱ በኋላ ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ ማድረግ ይገባዋል ።ሚስትም ለባሉዋ የሚገባውን መጠበቅ ማድረግ አለባት /1ቆሮ. 7:3/ ።

ሐ/ በጋብቻ ሕይወት በመጠራጠር ሳይሆን በመተማመን በመናናቅ ሳይሆን በመከባበር ባልና ሚስት በፈሪሀ እግዚአብሔር አንድ ልብ መሆን ያስፈልጋቸዋል።



የስነ ፍጥረት ባለቤት እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ የሠራው ሥርዐት ነውና ወንዶች በኃይልና በጉልበት ሳይሆን ሚስቶቻቸውን በፈሪሐ እግዚአብሔር ሊያስተዳድሩዋቸው ሊወዱዋቸውና ሊያከብሩዋቸው ይገባል ።

የአሳብና የምክር ተካፍይነት የትዳር አቻነት መብትና ነፃነት እንዳላቸው ያለማመንታት እንዲያረጋግጡላቸው ያስፈልጋል ።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ የጋብቻን ምስጢርና ክብር በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መስሎ ያስተላለፈውን መልእክት ማስተዋል ይገባል ።

ይህም ማለት ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ከቀኝ ጎኑ በፈሰሰው ደሙ ንጽሕት ክብርት ያደርጋት ዘንድ ራሱን ለሕማም ለሞት አሳልፎ እንደሰጠላት የራሱም ማደሪያ ትሆን ዘንድ እንደመረጣት እንዲሁም ወንዶች /ባሎች/ ሴቶቻቸውን /ሚስቶቻቸውን/ እንደራሳቸው አድርገው ሊወዱአቸው ይገባል "ራሱን መጥላት የሚቻለው የለም ለሰው ሁሉ የተሰጠው የሕይወት መመሪያ የተፈጥሮ ወንድምህን እንደራስህ ወደድ ነው ሚስቱን የሚድ ራሱን ወደደ" /ኤፌ. 5:25-29/ ።

በሴቶች በኩል እንደዚሁ የተለየ አመለካከትና የተዛባ ትርጉም ሳይሰጠው ከቅዱሳት መጻሕፍት በተገኘ ትምህርትና መመሪያ ሴቶች ለእግዚአብሔር እንደሚገዙና ለሕጉ እንደሚታዘዙ ለባሎቻቸው በፍቅር በፍርሃትና በአክብሮት እንዲታዘዙአቸው ተጽፎአል ። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ ገዥዋ እንደሆነ ሁሉ ለሴትም /ለሚስት/ ገዥዋ ባሏ መሆኑ ተመልክቶአል ።



ይህም ሚስት ለባልዋ፥ ባል ለሚስቱ መከባበርንና መተዛዘንን ያሳያል እንጂ የገዥና የተገዥ ምልክት አይደለም ።

ሴቶች በባሎቻቸው ዘንድ በዓለማዊ ልብስና ጌጣጌጥ ብቻ ሳይሆን ቀድም ብሎየነበሩ በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም እምነት የነበራቸው ደጋግ ሴቶች ለባሎቻቸው በመታዘዝ በመልካም ሥራ ያጌጡ እንደነበር ከበጎ ግብራቸው የተነሣ ገድል እና ድርሳን እንደተጻፈላቸው እንደነሣራ እንደነርብቃ ባለ አኗኗር የባሎቻቸው ሕይወት እንደሆኑ ተጽፎአል /1ጴጥ. 3:1-6/ ።

ስለዚህ ሴት ባሉዋ ያዘዛትን ልትፈጽም እንጂ በባሉዋ ላይ የሌላ ትእዛዝ ፈጻሚ ልትሆን የወደደችውን ልታደርግ በራስዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ በርሱዋ ላይ የማዘዝ ሥልጣን ያለው ባሉዋ ብቻ ነው ። እንዲዚሁም ወንድ በሚስቱ ላይ የሌላዬቱ ታዛዥ ሊሆን የሌላዬቱን ፈቃድ ሊፈጽም በራሱ የማዘዝ ሥልጣን የለውም ። በእሱ ላይ ሥልጣን ያላት የምታዝዝበት ሚስት ናት /1 ቆሮ. 7:4/ ።

መ/ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም ለባሉዋ መታዘዝ ይገብታል ። አሳዳሪም ስለሆነ እንዲሁም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ራሱንም ለሞት አሳልፎ እንደሰጠት ሥጋውን ደሙን እንደ መገባት ፥ እንደዚሁም ወንድ አካሉ ናትና ሚስቱን መውደድ፥ መርዳት፥ ይገባዋል /ኤፌ. 5:22-33/ ።

ሠ/ ለሴት በሥጋዊ ጌጥ ከማጌጥ ይልቅ ለባሉዋ በመታዘዝ ባሉዋን በመፍራት በመውደድ ጌታዬ እያለች በመጥራት ስትፈራና ስታፍር መልካም ሥራ በመሥራት ንጽሕ ለቡናዋን ገልጣ እያሳየች

በትሕትና በመንፈሳዊ ኃይል በመገዛት ማጌጥ አለበት ። ወንድም የምድር ሀብትና ክብር ብቻ ሳይሆን የሰማይ ሕይወትና ክብር ተሳታፊው ስለሆነች ሚስቱን ሳይንቅ እንደ ዓይን ብሌን መጠበቅ አለበት ። ባልና ሚስት አንድ ልብ አንድ አፍ ሆነው በመተማመን መኖር ይገባቸዋል እንጂ በአሳብ መለያየት መተማማት የለባቸውም /1ጴጥ. 3፡1-9/ ።

ረ/ ለጾምና ለጸሎት ከተወሰነ ቦታና ጊዜ በስተቀር ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም ።ሰይጣን ድል እንዳይነሣቸው ተጠባብቀው መኖር ይገባቸዋል /1ቆሮ. 7፡5/ ።

ሰ/ ሴት በአረገዘች ጊዜ ጽንስዋ ከገፋ፥ ሆድዋ ከሰፋ በኋላ ወንዱ ከእሱዋ ጋር ነገናኘት የለበትም "ወለእመ ወንዱ ከእሱዋ ዘይዴመር ምስለ ብእሲቱ እምድኅረ ተከሥተ ጽንሳ ወዝንቱ ኢርቱዕ ወአ በውሀ ሎቱ ለዝንቱሰ ኢይትፈቀድ ነገር በእንቲአሁ" /ፍት. ነገ. 24/ ።

ሸ/ ባልና ሚስት በጽንስ፥ በሕርስ፥ በትክት ጊዜ በበዓላት፥ በአጽዋማት ቀን ሩካቤ ሥጋ ማድረግ አይገባቸውም ።

## 9/ ፍቺ እንዳልተፈቀደ

ሰው ሚስቱን ሊፈታ ይገባል? አይገባውም ።ጋብቻ በተፈለገ ጊዜ የሚፈጸም በአልተፈለገ ጊዜ የሚፈርስ ጊዜያዊ ተባብሮ የመኖር ዘዴ ሳይሆን የሃይማኖትና የስነ ምግባር አንድነት ልባዊ ፈቃድና ስምምነት የዕድሜ



ጤንነት ያላቸው የወንድና ሴት ዘላቂነት ያለው ጽኑዕ አንድነት ነው ። ይህ ስለሆነም በማናቸውም ምክንያት ሁሉ መፋታት አይገባም።

ለአዳም ብዙ ሴቶች አለመፈጠራቸው ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት እንጂ ብዙ ሚስቶች ያልተፈቀደለት መሆኑን፥ ለሔዋንም ብዙ ወንዶች አለመፈጠራቸው ለአንዲት ሴት አንድ ባል እንጂ ብዙ ባሎች ያልተፈቀዱ መሆኑን ያመለክታል ።

በጋብቻ አንድነት ውስጥ ፍቺ ወይም መለያየት መኖር እንደሌለበት በቅዱሳት መጻሕፍትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተደንግጎዋል ።

በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ሚልክያስ ባልና ሚስት መፋታት እንደሌለባቸው ሲያስተምር "እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው ዘር አይደለምን ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል ፤ መፍታትን እጠላለሁ ይላል እግዚአብሔር የእሥራኤል አምላክ" ብሉዋል /ሚል. 2፡15-16/ ።

ጠቢቡ ሰሎሞንም "የሕፃንነት ባልዋን የምትተው የአምላኩዋንም ቃል ኪዳን የምትረሳ ቤትዋ ወደ ሞት ያዘነበለ ነው" ብሎዋል /ምሳ. 2፡17/ ።

በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሰው በማናቸውም ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን" ተብሎ ከፈሪሳውያን ለተጠየቀው ሲመልስ "እግዚአብሔር በመጀመሪያው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ... አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም ። እንግዲህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ" በማለት



ጋብቻ ጥንቱን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲመሠረት ጊዜያዊ ሳይሆን እስከ ሕይወት ፍጻሜ ዘላቂና ጽኑ አንድነት ያለው እንደሆነ አስተምሮዋል /ማቴ. 19፡5-6 ፤ ማር. 10፡2-9/ ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን መሠረት በማድረግ "ሴት ከባልዋ አትፋታ ልትፋታ ብትወድ ግን ያለ ባል ትኑር ያለዚያም ከባልዋ ጋር ትታረቅ ባልም ሚስቱን ሊፈታ አይገባውም " /1ቆሮ. 7፡10-11/ ።

እንዲሁም "ሴት ከባሉዋ አትለይ ወንድም ከሚስቱ አይለይ ሁላችሁም በጌታችን ትእዛዝ አንድ ሆናችሁ ኑሩ" /1ቆሮ. 11፡1/ ።

በተጨማሪም "አንተ ሰው ሚስት አግብተህ ከሆነ መፋታትን እትሻ /1ቆሮ. 7፡27/ ሲል የጋብቻን ጽኑነት አረጋግጦዋል ።

በቤተ ክርስቲያን የሕግና የቀኖና መጽሐፍም "ለፍቺ ያበቃል ተብሎ ከተናገረው ምክንያት በቀር ባል ሚስቱን፥ ሚስትም ባልዋን መፍታት እንደማይገባ ተወስኖዋል /ፍት. ነገ. 24 ክፍል 9 ቁጥር 11-17/ ።

በቤተ ክርስቲያን ጋብቻ እንዲህ ሊፈርስ የማይገባው መሆኑ እየታወቀ ማንኛውም ሰው ሚስቱን ሊፈታ ቢወድ ከካህናቱ አንዱ ነውሩዋን ሚናገር ደብዳቤ መጻፍ የለበትም ፤ ከጸፈ ግን መልሶ እስከሚያስታርቀው ድረስ ከምእመናን ይለያል ። "ወለእመ ፈቀደ አሐዱ ከመ ይድኅር ብእሲቶ ወጸሐፈ አሐዱ እምካህናት መጽሐፈ ኅዳጋቲሃ ይሰደድ እስከ ይመይጣ ለተዋስቦ ወያስተሳልም /ፍት. ነገ. አን. 9 ቁ. 5 ረስጠጅ 71/ ።



## 10 ፍቺና ሁለተኛ ጋብቻ

ሀ/ ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈቀደው ሚስት ወይም ባል በሞት ሲለዩ ብቻ ነው ። ከዚህ በቀር ሁለተኛ ጋብቻ አይፈቀድም ። ባልና ሚስት በሞት ካልሆነ በስተቀር ፈጽሞ መለያየት ከደረሰባቸው ግን ወደ ኋላ የቀረው ንጽሕናውን ጠብቆ መኖር የማይቻለው ከሆነ ሁለተኛ ማግባት ይችላል ። ሁለተኛዋም ከሞተች እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ ማግባት ይችላል።

"ሴት ባሉዋ በሕይወት ሳለ በሕግ የጸናች ናት ባሉዋ የሞተ እንደሆነ ግን ለባሉዋ ከገባችለት ቃል ኪዳን ነጻ ናት ። ባሉዋ በሕይወት ሳለ ከሌላ ወንድ ብትደርስ ዘማዊት ይሆንባታል ። ባሉዋ የሞተ እንደሆነ ግን ሌላ ብታገባ ዘማዊት አይሆንባትም ስሰነች አትባልም /ሮሜ 6፡2-3/ ።

ሚስቱ የሞተችበት ሰው የሚያገባው የሚስቱ ሙት ዓመት ከአለፈ በኋላ ነው ሴት ባሉዋ ከሞተ ከ10 ወር በኋላ ታገባለች።

"ወእመሰኬ ያፈ መንጢጥ ዘኢነባቢ ይትገሐሥ እምአውስቦ ዳግማዊ እፎ እንከ ፈድፋደ ይደሉ ለእንስሳ ነባቢ ፍሬ ነገር የማይናገር ያፈ መንጊዕ /ርግብ/ ከሁለተኛ ግቢ የሚከለከል ከሆነ ፍሬ ነገር የሚናገር ሰውማ ከሁለተኛው ግቢ መከልከል እንደምን አይገባውም" /ፍት. ነገ. አን. 24 በስ. 43/

"ወበእንተ ዝንቱ ፍና ይደሉ ዐቂበ ዛቲ ሕግ እስመ ይእቲ ታወርዶሙ ለክቡራን እምክብሮሙ ዘውእቶሙ ካህናት ወይእቲ ሎሙ ትከውን ምንንተ" /ፍት. ነገ. አን. 24/ ።

ወኢያውስብ ዘእንበለ ይንልፍ ፳ዱ ዓመት እሞተ ብእሲቱ /ፍት. ነገ. አን. 7/ ፡፡

"ወእመኒ ብእሲት አውሰበት ብእሴ እምቅድመ ይትፈጸም አሠርቱ እውራኅ እምከመ ሞተ ምታ ኢትረስ ንዋየ ምታ /ፍት. ነገ. አን. 24/ ፡፡

ለ/ ከላይ ከተጠቀሰው በሞት ምክንያት ከሚደረገው መለያየት ሌላ ወንድ ሚስቱን መፍታት የሚገባው ስታመነዝርበት ብቻ ነው ፡፡ ወይንም ሴት ባሏዋን መፍታት የሚገባት ሲያመነዝርባት ብቻ ነው ፡፡

ማንኛውም ወገን ማለት ወንድም ሆነ ሴት በዝሙት ምክንያት ከፊታ በኋላ በዝሙት ምክንያት የተፈታችውን ወገን ማግባት አልተፈቀደለትም ፡፡ማግባት የሚችለው ንጽሕናውን ጠብቆ በሥጋው በደሙ ተወስኖ የኖረውን ወገን ብቻ ነው /ማቴ. 5፡31-33፤ 19፡7-9/ ፡፡

ሐ/ በተፈጥሮ ወይም ከጊዜ በኋላ የሚከሠቱ ለፍቺ የሚያበቁ ችግሮችም ሲያጋጥሙ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፍቺ ይፈቀዳል ፡፡ እነዚህም ችግሮች /በፍት. ነገ. አን. 24 ቁጥር 940- 958 / ተዘርዝረዋል ፡፡

ለሁለተኛ ጋብቻ መጽሐፈ ተክሊል አይጸለይም ሥርዓተ ተክሊል አይደረግም ፤ የሚጸለየው ፍትሐት ዘውልድና ጸሎተ ንስሐ ብቻ ነው ፡፡

"ወኢይጸልዩ ላእለ አውስቦ ዳግማዊ ... ዘውእቱ ጸሎተ ተክሊል ወአኮ ጸሎተ ፍትሐት" ይላል /ፍት. መን. አን. 9 ክፍል 4 ሥር 8 በስ 12/ ፡፡



ውእውስቦስ ዳግሚት ተሐፅፅ እምቀዳሚት ወለዛቲስ ተሠርዐ ከመ ኢትኩን ላቲ በረከተ ተክሊል አላ ይግበሩ ጸሎተ አስተሥርዩ /ፍት. ነገ. 24 ፤ ዕንቆራ 18/ ፡፡

ወተጋብአስ ማዕከለ አውስቦ ዳግማዊ አው ዘይበዝኅ ኢይደሉ እስመ ውእቱ ዝሙት ክሡት ዘተነግረ /ፍት. ነገ. አን. 24/ ፡፡

11/ ሦስተኛ ጋብቻ

ሀ/ ሦስተኛ ጋብቻ ፈጽሞ የተናቀ ነው ፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው ሚስቱ ከሞተችበት አንድ ሰው ለሦስተኛ ጊዜ ማግባት ቢፈልግ በሕገ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የንስሐ ጸሎት ተደርጎለት በቤተ ክርስቲያን ያገባል ፡፡ ከ 3 ጊዜ በላይ ማግባት ግን ለክርስቲያን አልተፈቀደም ፡፡ ወአውስቦስ ሣልስ ምኑን ውእቱ ወአልቦ በኅቤነ እምድኅረዝ አውስቦ ሕጋዊ ይላል /ፍት. ነገ. አን. 24/ ፡፡

እንዲሁም ወለእመቦ ዘአውስበ ዘኢኮነ እምሕግነ ይትከላዕ ዓመት ወዘዐውሰበ ራብዐ ኢይቅረብ ይላል /ፍት. ነገ. 24/ አይቁረብ ማለት ነው ፡፡

ለ/ የመዓስባን ማለት አግብተው የፈቱና በንስሐ የተመለሱ ምእመናን ጋብቻቸውን በሥርዓተ ጸሎትና በቅዱስ ቁርባን ለመፈጸም ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ ቄሱ ከሁሉ አስቀድሞ ለመጋባት የተፈቃቀዱበትን የሁለቱን ሰዎች ጋብቻ የሚከለክል ምክንያት አለመኖረሩንና በእነሱም በኩል እስከ መጨረሻው መለያየትን የማያስከትል ስምምነት በመካከላቸው መኖሩን ይመረምራል ፡፡



ከመጋባት የሚከለክላቸው ምክንያት አለመኖሩን፥ ስምምነታችውም ፍጹም መሆኑን በሚገባ ከተረዳ ጸሎት ያደርስላቸዋል ፡፡ ከጸሎቱም በኋላ ሥጋውን ደሙን ያቀብላቸዋል ፡፡

ሐ/ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በሚስት ላይ ሚስት ማስቀመጥ ክልክል ነው ፡፡

"ወኢያንብር ብእሲ ክልዔተ አንስተ በምክንያተ ተድላ" ይላል /ፍት. ነገ. አን. 24/ ፡፡

መ/ ካህን ሁለተኛ ቢያገባ ከክህነቱ ይሻራል ፡፡ሦስተኛ ቢያገባ ግን አልተፈቀደለትም ፤ ርኩስ ነው ፡፡

"ወለእመ ኮኑ ዕደው ካህናተ ይደቁ እማዕርጊሆሙ ወእምድኅሬሁሰ ለእመ ደገሙ ይከውኑ ርኩሰ" /ፍት. ነገ. አን. 24 ምዕ. 5 ክፍል 3 ቁጥር 5-6 ፤ ኒቅ. 19/ ፡፡

ሠ/ ከወንድ ዝሙት ቅጣት ይልቅ የሴት ዝሙት ቅጣት ይበልጣል ፡፡

"ወይደሉ ከመ ይጽናዕ ኩነኔ ዝሙታ ለብእሲት ፈድፋደ እምብእሲ /ፍት. ነገ. አን. 24 ሥር 24 ቁጥር 35/ ፡፡

## 12/ የሥርዐተ ተክሊል አፈጻጸም

የሥርዓተ ተክሊል አፈጻጸም፥ የቀለበት ማሠሩም ሆነ የጋብቻው ሥርዓት ሚያዝያ 1 ቀን 1956 ዓ.ም በሊቃውንት ጉባኤ በታተመው መጽሐፈ ተክሊል የተገለጸ ስለሆነ በዚሁ መጽሐፍ መሠረት ሥርዓቱ ይፈጸማል ፡፡



## 13/ የሥርዐተ ተክሊል ትርጉም

ሀ/ አንድ ወንድ ማግባት የሚገባው አንዲት ሴት ነው ፤ ወይም አንዲት ሴት ማግባት የሚገባት አንድ ወንድ ነው ብዙ ብዙ ሴት ማግባት የሚገባ ቢሆን ሥላሴ ለአዳም ብዙ ሴት መፍጠር በቻሉ ነበር ብዙ ወንድ ማግባት የሚገባም ቢሆን ኑሮ ለሔዋን ሥላሴ ብዙ ወንድ በፈጠሩላት ነበር ፤ ነገር ግን አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ መኖር በደስታም በመከራም አብረው መኖር እንዲገባቸው ለሔዋን አዳምን ብቻ ለአዳምም ሄዋንን ብቻ ፈጠሩ /ዘፍ. 2፡20-25 ፤ ማቴ. 19፡3-6/ ፡፡

ለ/ ወንድ ወደ ሴት ሔዶ እንዲያጭ የተደረገበት ምክንያት ቃል የመርዓዊ፥ ትስብእት የመርዓት ምሳሌ በመሆኑ ነው ፡፡ይኸውም ቃል ሽቶ ሥጋን ተዋሐደ እንጂ ሥጋ ፈልጎ ያልተዋሐደ ስለሆነ በዚህ ምሳሌ ነው ፡፡

አዳም ሔዋንን በተጣላት ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ሲያስታርቃቸው ሄደህ ታረቅ ቢለው እሱዋ ትምጣ እንጂ እኔ አልሔድም በአለው ጊዜ አኮ መፍትው ትሑር ብእሲ ኀበ ብእሲት ኀበ ብእሴሃ አላ መፍትው ይሑር ብእሲ ኀበ ብእሲቱ ማለቱ ወንድ ወደ ሴት እንዲሔድ እንጂ ሴት እንድትመጣ ስለማያመለክት ነው ፡፡

ሐ/ ሰባት ዓመት ላልሞላው ልጅ ሚስት አይታጭለትም ፤ ምክንያቱም አዳም ከሰባት ቀን በፊት ሔዋንን ስለአላገኘ ነው /ኩፋሌ 4፡28 ፤ ፍት. ነገ. አን. 24/ ፡፡

መ/ የሙሽራውና የሙሽራዪቱ ተዋሕዶ የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ተዋሕዶ ምሳሌ ነው ። "ዐቢይ ውእቱ ዝ ነገር አንስ ዕብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላእለ ቤተ ክርስቲያን /ኤፌ. 5:32/ ።

ሠ/ ሙሽሮች በቃል ኪዳናቸው ጊዜ ቀለበት የሚያደርጉት የቃል ኪዳንና የሃይማኖት ምልክት በመሆኑ ነው ።

ረ/ ቃል ኪዳን የሚገቡበት መስቀል የመከራቸው ምክልት ነው ።

ሰ/ ዘመድና ዘመድ እንዳይጋቡ፥ ባዕድና ባዕድ እንዲጋቡ የተወሰነበት ምክንያት ባዕድ መለኮት ባዕድ ሥጋን ስለተዋሐደ የዚያ ምሳሌ በመሆኑ ነው ።

ሸ/ አብረው ያደጉ ሰዎች የማደጎና የጉድፈቻ ልጆች አሳዳጊዎቻቸው ጭምር ርስ በርሳቸው አይጋቡም ፤ ምክንያቱም አንድ ጡት ጠብተው ስለሚያድጉ፥ አሳዳጊዎችም እንደ ልጅ ይሆኑናል ብለው ስለሚያሳድጉዋቸው ነው ።

"አውስቦ አዝማድ ዘበንብረት ወለእመኒ ወጽኡ እምታሕተ ምልክናሆሙ ውእቶሙ ወለእመ ተፈልጡ ዘሐፀንዎሙ ወእሙንቱ ዘሀለው በተሳትፎ ጠቢወ ጥብ ወውሉዶሙ ወወላድያኒሆሙ ወለእመኒ እሉ ወአበዊሆሙ ወአበወ አበዊሆሙ ወአኃወ አበዊሆሙ ፤ ወአኃተ እማቲሆሙ ወብእሲተ አብ ..." /ፍት. ነገ. አን.24 ቁ. 54/ ።



ቀ/ ያመኑ ሰዎች ያላመኑትን እንዳያገቡ የተደረገበት ምክንያት በኦሪቱ ሥርዓት "ኢትሀብ ወለተከ ለአሕዛብ ወኢትንሣዕ ወለቶሙ ለአሕዛብ" በተባለው መሠረት የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑት እሥራኤል ከአሕዛብ ስለማይጋቡ በዚህ ሥርዓት ምሳሌ ነው /ዘዳ. 6:3/ ።

በ/ ባለጸጋ ድሀ አላገባም ማለት አይገባውም የተባለው ባዕል መለኮት ነዳይ ሥጋን ስለተዋሐደ ነው ።

"እንስ ዕብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላእለ ቤተ ክርስቲያን" /ኤፌ. 5:32/

እፎ ቤተ ነዳይ ኀደረ ከመ ምስኪን እምሰማያት ወረደ ላእሌሃ ፈቲዎ ስነ ዚአሃ ወተወልደ እምኔሃ /ሰዓታት/ ።

ተ/ በሥርዓተ ተክሊል ላይ ሙሽሮች የሚለብሱት ልብስ ሰማይ በከዋክብት ምድር በጽጌያት እንደሚያጌጡ ጌጣቸው፥ የደስታ፥ የድኅነት፥ የንጽሕና የሰላምና የጤንነት የልጅነት /ከእግዚአብሔር መወለድ/ ምልክት ነው ።

ቸ/ ሙሽሮች ዘይት የሚቀቡት ሰማያዊ ክብር እንዲያገኙ፥ የጽድቅና የፍርድ መሣሪያ እንዲሆናቸው፥ ንጽሕናቸውን እንዲጠብቁ፥ የማይጠወልግ መልክና የሥጋ ብርሃን እንዲሰጣቸው፥ የጌጥና የደስታ፥ የእውነተኛ ሀብት እንዲሰጣቸው፥ የድኅነት ኃይልና የጠላት መንፈስን እንዲያድላቸው፥ የድኅነት ኃይልና የጠላት ዲያብሎስን ሥራ ሁሉ ድል የሚነሣ እንዲሆናቸው፥ ነፍሳቸውና ሥጋቸውን ልቡናቸውንም እንዲያድላቸው የብልጽግናና የመልካም ሥራ ፍሬን እንዲሰጣቸው ነው።



ኀ/ ሙሽሮች የሚያደርጉት አክሊል የክብራቸው ምልክትና ምሳሌ ነው ።

ነ/ ሴት ከወንድ ሥልጣንና ትእዛዝ በታች የምትኖረው ተፈጥሮዋ ከወንድ ጎን ስለሆነ ነው /ዘፍ. 2:21-24/ ።

ኘ/ ሴት ጽንስዋ ከገፋ ሆድዋ ከሰፋ በኋላ ባሉዋ እንዳይገናኛት የተከለከለበት ምክንያት የተጸነሰው ወንድ ከሆነ ግብረ ሰዶም መሥራት ሴት ከሆነች ከልጁ መገናኘት ስለሚሆንበት ነው ።

አ/ በአራስነትና በወር አበባ ግንኙነት ክልክል ነው ምክንያቱም 1ኛ/ አባለ ዘርን ደዌ የሚያገኘው ስለሆነ 2 ኛ/ የሚጸነሱትን ሕፃናት ደዌ ሥጋ የሚያገኛቸው ስለሆነና ለምፅ ስለሚወጣባቸው ነው ።

"ወተከልያስ እምነ ሩካቤ በመዋዕለ ትክቶሃ ወኀርስ ዝኒ በእንተ ዘይረክቦ ለአባለ ዘርዕ እሙስና ወዘይዳቆሙ ለውሉድ እለ ተጸንሱ በከርሥ እምነ እንታክቲ ግብር ሕማመ ዝልጋሴ ወለምፅ" /ፍት. ነገ. አን. 24 ም. 5 ክፍል 3 ቁ. 47-49/ ።

ከ/ በጾም ሩካቤ የተከለከለበት ምክንያት ለጾም የሚገባውን ፈቃደ ነፍስ ለመፈጸም እንዲቻል ነው፥ ሁለተኛም ስውነትን በንጽሕና ለመጠበቅ ነው ።ሦስተኛም የሚወለደውን ልጅ ከመቅሰፍት ለመጠበቅና ለማዳን ነው ።

"ወተከልያስ በመዋዕለ አጽዋም ዝኒ ከመ ይትፈጸም ከዊነ ፈቃድ ዘበእንተ ጾም... በእንተ



ክብረ ነፍስ ነባቢት ወለዐ ቂበ ሥጋሁ ወለዐቂበ ወልዱ" /ፍት. ነገ. አን. 24 ም. 5 ክፍል 3 ቁ. 50-52/ ።

ኸ/ ሰውን እንስሳ ነባቢ ያሰበት ምክንያት ሰው በተፈጥሮው ነባቢት ነፍስን በመዋሐዱ መላእክትን ሲመስል ደካማ ሥጋን በመልበሱ እንስሳትን ስለሚመስል ነው ።ማለት በነፍሱ የመላእክትን ሥራ ሲሠራ በሥጋው የእንስሳትን ሥራ ስለሚሠራ ነው ።ጌታንም የአዳምን ሥጋ በመልበሱ መጽሐፍ እንስሳ ይለዋል ።

"ወኮነ እንስሳ ነባቤ" /አፈ. ወርቅ ድርሳን 1 ገጽ 22/

ወ/ ሙሴ እንደ ልቡናችሁ ክፋት መጠን ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ጻፈላችሁ ያላቸው ሙሴ አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት እንዲት ሴት ከአንድ ወንድ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በደንጊያ ተወግሮ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት ብሎ ሥርዐት ሠራ፥ ወንዱ የሞተችበት እንደሆነ ሴቷም የሞተባት እንደሆነ በፊቼው ጾር እየተናደዱ የሚሞቱ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር አመለከተ ።ሚስቱ የሞተችበት ባልዋም የሞተባት ያግቡ አለው ወንዱ የጠላት እንደሆነ በጉልበቱ እያሻሸ የሚገድላት ሴቲቱም የጠላችው እንደሆነ በጉልበት ባይሆንላት በጥበብ በሥራይ የምትገድለው ሆነ ።በዚህ ምክንያት የምትፈታበትን ነውር የሚናገር ደብዳቤ ጽፎ ይፍታት ብሎ ስለነገረውና በዚህ ምክንያት ሙሴ እንዲፈታ ስለፈቀደ ነው ።

ዐ/ ያፈ መንጢጥ /ርግብ/ ለሕጋዊ ጋብቻ ምሳሌ የሆነችበት ምክንያት ባሉዋ ስለሞተባት በጥፍሩዋ

መላስዋን ሰንጥቃ ሌላውን ወንድ ትክለክላለች ማለት የተሰነጠቀ ምላስዋን እያሳየች ስለምትመልስ ነው /ድርሳነ ሚካኤል ገጽ 79/

ዘ/ 60 ዓመት የሞላትን ሴት ማግባት ተከልክሉዋል ፤ ምክንያቱም ልጅ መውለድ ስለማትችል ሙቀት ልምላሜ ስለተለያት በማርጀቱዋ ምክንያት ባሉዋን መርዳትም ስለማትችል ነው /ፍት. ነገ. አን. 24 ቁ. 105/ ::

የ/ ለምእመናን ሦስተኛ ጋብቻ ሲፈቀድ ለካህናት የተከለከለበት ምክንያት የካህን ሁለተኛ ጋብቻ የምእመናን ሦስተኛ ጋብቻ፥ የካህን ሦስተኛ ጋብቻ እንደ ምእመናን አራተኛ ጋብቻ የሚቆጠር ስለሆነ ነው ::

ደ/ ከወንድ ዝሙት ቅጣት የሴት ዝሙት ቅጣት የሚበልጥበት ምክንያት 1ኛ/ ወንድ ከዝሙት ባይከለከል ሴት ከባሉዋ ትለያያለችና መለየት አይገባትም ለማለት ሲሆን ሴት ከዝሙት ከአልተከለከለች ባልዋን ቅንዓት ይይዘውና ሚስቱን ከእሱዋ ጋር ያመነዘረውን ሰው፥ አባቱዋን ፥ ወንድሟን፥ እናቱዋን እስከ መግደል ይደርስና ብዙ ነፍስ ያጠፋል ::ሚስቱና ዘመዶቹዋም ቢሆኑ ልጃችንን ክብታችንን ስጠን ይላሉ እንጂ እንገደል አይሉም 2ኛ/ ሴት ከአመነዘረች ዘር ይደባለቃል ::3ኛ/ ድንግል ሴት ብታመነዝር በዝሙት፥ ማኅተመ ድንግልናዋን አጠፋች ትባላለች ወንድ ግን ማኅተመ ድንግልናውን አጠፋ አይባልምና በዚህ ምክንያት ነው ከወንድ ዝሙት ቅጣት የሴት ዝሙት ቅጣት የበለጠው :: ወዝንቱስ ዘተገብረ እስመ

ዝሙትስ ለብእሲ ዝኒ በእንተ ከመ ኢመውት ትትፌለጥ ብእሲት እሞኒሁ እስመ ብዝኀ ሐሠሣሁ ለሕግ ከመ የአትት ዕፀበ ዘይመጽእ ላዕለ ስብእ በበይናቲሆሙ ወለብእሲስ ፈድፋደ ይእኅዞ ቅንዓት እስከ ይቀትል ብእሲቶ ለእሙ ዘመወት ላዕሌሁ ወዐዲ ይቀትል ብዕሴ ዘዘመወ ምስሌሃ ወዓዲ ይገብር ዘንተ በአቡሃ ወበእኁሃ አው በእማ ወብእሲትስ ወአዝማዲሃ አኮ ከማሁ ወዓዲ እስመ ዘርእ ይቀውም በእንተ ተዐቅቦተ ብእሲት ወለእመ ዘመወት ይእቲ ይማስን ርስት ወትውልደ አበው ወዐዲ እስመድንግል በዝሙት ታማስን አርአያ ድንግልና ሃ ወብእሲስ አኮ ከማሁ /ፍት. ነገ. አን. 24 ሥርዋዕ 24 ቁጥር 36-46/ ::

## ክፍል 8

## ሸ/ ሥርዓተ ቀንዲል /ቅብዐ ዘይት/

### 1/ የቀንዲል አመሠራረት

በብሉይ ኪዳን ዘይት የፈውስ ምልክት ነበር :: ሕሙማን ወይም ቁስለኞች ዘይት እየተቀቡ ይፈወሱ ነበር / ኢሳ. 1:6 ፤ ሉቃ. 10:34 ፤ ራእ. 3:18 ፤ ማር. 6:13/ በሐዲስ ኪዳን ቀንዲልን የመሰረተው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው :: ሐዋርያትም የቀንዲልን ወይም የቅብዐ ዘይትን ምሥርያትም የቀብዲልን ወይም የቅብዐ ዘይትን ምሥጢርነት አስተምረዋል :: ክርስቶስ እንደመሠረተው ምንም እንደ ሌሎች ምሥጢራት ግልፅ የሆነ ጽሑፍ እንኳን ባይገኝ ሐዋርያትን እንዳዘዛቸው እነርሱም ዘይት እየቀቡ ብዙ ድውያንን እንደ አዳኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይናገራሉ ::ይህ



ዘይት ሕሙማን ሥጋ ብቻ ሳይሆኑ ሕሙማን ነፍስ ኃጥኣንም የሚቀቡት ፥ ፈውስ የሚያገኙበት ዘይት ነው ::

በወጡም ጊዜ አስተማሩ ንስሐ ይገቡ ዘንድ አጋንም ሰይጣናትን አወጡ በዘይትም ብዙ ድውያንን ቀቡ አዳኑ ዋቸውም /ማር. 6:13/ ::

ማንም ከእናንተ ቢታመም የቤተ ክርስቲያናትን ቀሳውስት ይጥራ የወጸልዩለትም በዘይትም ይቀቡት በጌታ ስም የሃይማኖት ጸሎት ድውዩን ትፈውሰዋለች ጌታም ያስነሣዋል ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ትሠረይለታለች /ያዕ. 5:14-16/ ::

በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ደዌ ሥጋንና ደዌ ነፍስን ለመፈወስ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እየጸለየች በዚህ ቅብዐ ዘይት ምእመናንን ትቀባለች ::

### 2/ ምሥጢረ ቀንዲል

ቀንዲል ወይም ቅብዕ ቅዱስ የተባለው ምሥጢር ከንጽሕ ወይራ ዘይት የጠሠራ፥ የሥጋንም የነፍስንም በሽታ የሚያርቅ የማዳን ኃይል ያለው ምሥጢር ነው ::

ቀንዲል /ቅብዐ ዘይት/ በእግዚአብሔር ጸጋ በቄስ ሥልጣንና ጸሎት የማዳን ኃይል ስለአለው በቅዱስ ያዕቆብ መልእክት እንደ ተጻፈው ኃጢአትን ሳይቀር ያስተሠርያል (ያዕቆብ 5:14-16) ::

ምሥጢረ ቀንዲል እንደ ሌሎች ምሥጢራት የሚታይ አገልግሎትና የማይታይ ጸጋ አለው ::ማለት በሽተኛው ወድቆ ድኅነትን ደጅ ሲጠና፥ በንጹሕ ዘይት ላይ



የሃይማኖት ጸሎት ሲጸለይ፥ ቄሱ ሲባርከው ከጸሎቱም በኋላ አካሉን ሲቀባው ይታያል ::ይህ የሚታይ አገልግሎት ይባላል ::ደዌ ሥጋውና ደዌ ነፍሱ ሲለቀውና ሲፈወስ የእግዚአብሔር ጸጋ ሲሰጠው አይታይምና ብዙ ጊዜ ግን ከደዌ ሥጋው ሲፈወስ ይታያል ::ይታወቃል:: ሆኖም በሽታው ሲለቀው እንጂ እንዴት እንደዳነ ራሱ እንኳን አያውቀውም /ያዕ. 5:14-16/ ::

### 3/ የቀንዲል ዓላማና ጥቅም

ክህነ የቀንዲል ጸሎት አድርሶ የምእመኑን አካላቱን ሲቀባው ታሞ እንደሆነ በሽታው ይለቀዋል ::ኃጢአት ሠርቶ እንደ ሆነ ኃጢአቱ ይሠረይለታል ::ደዌ ሥጋ ለደዌ ነፍስ ፤ ደዌ ነፍስም ለደዌ ሥጋ ይተርፋልና :: ንጽሕናቸውን ባለመጠበቃቸው ሰውነታቻቸውን በማጎሳቆላቸው ነፍሳቸውንም አብረው ያጎሳቁላሉ ::ሥጋቸው በታመመ ጊዜ ነፍሳቸው አብራ ትታመማለች :: ግን ንስሐ ገብተው ተመልሰው ምሥጢረ ቀንዲልን የተቀበሉ እንደሆነ ድኅነተ ሥጋንም ድኅነተ ነፍስም ያገኛሉ ::አጠቃላይ በምሥጢረ ቀንዲል የሥጋን የነፍስን ድኅነት የኃጢአትን ሥርየት እናገኛለን :: ቅብዕ ቅዱስ ከጥምቀት በፊትም ሆነ በኋላ ለተሠራው ኃጢአት ማሥተሥርያ ሲሆን ከምሥጢረ ጥምቀትና ከምሥጢረ ንስሐ ጋራ ኃጢአት በማሥተሥረይ ድኅነትን በመስጠት ጸጋን በረከትን በማስገኘት ይገኛኛት ይገናኛሉ /ማር. 6:13 ያዕ. 5:14-16/ ::

### 4/ ሥርዐተ ቀንዲል

ያዕቆብ እንደ አስተማረው ይህን ቀንዲል የሚቀቡ ሰዎች አስቀድመው በንስሐ የተዘጋጁ መሆን ይገባቸዋል ::ለጸሎተ ቀንዲል ቦታና ጊዜ አይለይም ::

በቤተ ክርስቲያን ወይም በሽተኛው በተኛበት አል.ጋ ዙሪያ ይፈጸማል ::በዕድሜ ወይም በሁኔታ ልዩነት አይደረግም ማንኛውም ምእመን ንስሐ ገብቶ ኃጢአቱን ተናዝዞ ቀኖና ተቀብሎ የተንዲል ምሥጢር ይፈጸምለታል ::የተንዲልን ምሥጢር የሚፈጽሙት ሰባት ኤጲስ ቆጶሳት ወይም ሰባት ቀሳውስት ናቸው :: እነዚህም ዮሐንስ በራእዩ ያያቸው ሰባት ብርሃናት ምሳሌ ናቸው /ራእ. 1:13/ ::ምሥጥረ ቀንዲል የሚፈጽሙበት ካህናት ንጽሕ ዘይት አቅርበው ለዚህ የተወሰነውን ጸሎት ያደርሳሉ :: ሰባቱም በየተራ በምእመናኑ ራስ ላይ ወንጌል ያነብባሉ :: ይህም የጌታ አንብሮተ እድ ምሳሌ ነው :: ወንጌል ከተነበበ በኋላ ሰባቱም እጃቸውን በራሱ ላይ ጭነው ይጸልዩለታል ::በመጨረሻም በጫፋቸው ጥጥ የተጠመጠመባቸው ሰባት ዕንጨቶች ይይዛሉ ፤ያንን በየተራ ወደ ተጸለየበት ዘይት እየነከሩ በትእምርተ መስቀል ይቀቡታል ::ስለዚህ፦

ሀ/ ምሥጢረ ቀንዲል እንደ ሌሎች ምሥጢራት በካህን ብቻ የሚሠራ ምሥጢር ነው ::

ለ/ ካህኑ መጽሐፈ ቀንዲል ደግሞ የበሽተኛውን አካል በመስቀል ምልክት ይቀባዋል ::

ሐ/ የሚቀቡት የአካል ክፍሎች ግንባሩን ከሁለት ቦታ፥ ፊቱን ከሁለት ቦታ፥ ሸንጎበቱን /አገጩን/ ቀኝና ግራ እጁን በውስም በውጭም፥ ሁለት እግሩን፥ ቢቻል ታላላቅ ሕዋሳቱን ሁሉ ያለዚያም ለጊዜው በሚያመው አካሉ ላይ ይቀባዋል ::

እነሣሣቶ ላስጀመረኝ አስጀምሮ ላስፈጸመኝ
ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀርባለሁ ::



## ጥቅሶችና ትርጉማቸው

| ጥቅስ | ትርጉም |
|---|---|
| ማቴ. | የማቴዎስ ወንጌል |
| ዮሐ. | የዮሐንስ ወንጌል |
| ፩ጴጥ | መጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት |
| ዘፀ. | .ኦሪት ዘፀአት |
| ማር. | .የማርቆስ ወንጌል |
| ሉቃ. | .የሉቃስ ወንጌል |
| ፍት. ነገ. | ፍትሐ ነገሥት |
| ዕብራ. | የዕብራውያን መልእክት |
| ዘዳ. | ኦሪት ዘዳግም |
| በደስ. | አቡሊዲስ |
| ዶቅ. | የሎዶቅያ ሲኖዶስ |
| ረስጣ. | አንደኛ ቀሌምንጦስ |
| ድስቅ. | ዲድስቅልያ |
| ፩ቆሮ. | መጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት |
| ዘሌዋ. | ኦሪት ዘሌዋውያን |
| ዘኒቅያ. | የኒቅያ ሲኖዶስ |
| መዝ. | መዝሙረ ዳዊት |
| ዮሐ. አፈ. | ዮሐንስ አፈ ወርቅ |
| በስ. | ባስልዩስ |
| ዘፍ. | ኦሪት ዘፍጥረት |
| ኤፌ. | የኤፌሶን መልእክት |
| ረስጠብ. | ሁለተኛ ቀሲምንጦስ |
| ጴጥ. | ጴጥሮስ |
| ግንር. | የጋንግራ ሲኖዶስ |
| ሕዝ. | ትንቢተ ሕዝቅኤል |



| ጥቅስ | ትርጉም |
|---|---|
| የሐ. ሥ. | የሐዋርያት ሥራ |
| ገላ. | የገላትያ መልእክት |
| ቲቶ. | የቲቶ መልእክት |
| ፩ዮሐ | የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት |
| ኩፋ. | መጽሐፈ ኩፋሌ |
| ፩ነገ | መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ |
| ረስጠጅ. | ሦስተኛ ቀሲምንጠስ |
| ሥር ቅዳ. | ሥርዐተ ቅዳሴ |
| ዕንቆራ. | የዕንቆራ ሲኖዶስ |
| ጢሞ. | ጢሞቴዎስ |
| ፩ጢሞ. | መጽሐፈ ክርስቶዶሉ |
| ፪ጢሞ. | መጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልእክት |
| ጠስ. | ሁለተኛው የጢሞቴዎስ መልእክት |
| ጾክ. | ፩ኛ ፍትሐ ነገሥት |
| መጅ. | የአንጾኪያ ሲኖዶስ |
| ሚል. | ሦስተኛ ፍትሐ ነገሥት |
| ሮሜ. | ትንቢተ ሚልክያስ |
| ያዕ. | የሮሜ መልእክት |
| መክ. | መልእክተ ያዕቆብ |
| | ሁለተኛ ፍትሐ ነገሥት |



ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሊቃውንት ጉባኤ ዐባል

ዋጋው ብር 60